# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሐሙስ

83ኛ ዓመት ቁጥር 311 ሐምሌ 11 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









## "ደቡብ ሱዳን የናይል ተፋሰስ የትብብር ማዕቀፍ ስምምነትን ማፅደቋ ለኢትዮጵያ ታሪካዊ ነው"

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

ደቡብ ሱዳን የናይል ተፋሰስ የትብብር ማዕቀፍ ስምምነትን ማፅደቋ ለኢትዮጵያ ታሪካዊ ክስተት ነው ሲሉ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) አስታወቁ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በትዊተር ገጻቸው ላይ ዛሬ ማለዳ ባስተላለፉት መልዕክት፤ ደቡብ ሱዳን ስምምነቱን ተቀብላ ማፅደቋ ለኢትዮጵያ ብሎም ለአካባቢው ሀገራት ትልቅ ጠቀሜታ አለው።

እንደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ ይህ ዲፕሎማሲያዊ እመርታ በተፋሰሱ ሀገራት መካከል ቀጣናዊ ትብብርን ለማሳደግ ላለው ፍላጎት ጉልህ እርምጃ ነው።

"የደቡብ ሱዳን ስምምነቱን ተቀብላ ማፅደቅ የናይል ተፋሰስ ኮሚሽንን በማቋቋም የሕዝባችንን የጋራ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ መነቃቃትን ይፈጥራል" ብለዋል ጠቅላይ ሚኒስትሩ በዚሁ መልዕክታቸው።

የናይል ተፋሰስ ሀገራት የትብብር ማዕቀፍ 10 ሀገራትን ያቀፈ አካባቢያዊ ድርጅት ሲሆን የሀገራቱ የጋራ የውሃ ሀብት የሆነውን የናይል ተፋሰስ በእኩልነትና በዘላቂነት ለማልማት እና ለማስተዳደር ያለመ ነው፡፡ ስምምነቱንም ኢትዮጵያ፣ ኬንያ፣ ሩዋንዳ ፣ ብሩንዲ፣ ታዛኒያ፣ ዑጋንዳ አሁን ደግሞ ደቡብ ሱዳን የምክር ቤቶቻቸው አፅድቀውታል፡፡






## ደቡብ ሱዳን የትብብር ማዕቀፍ ስምምነቱን ማፅደቋ ለኢትዮጵያ ትልቅ የዲፕሎማሲ ስኬት ማረጋገጫ ነው

አዲሱ ገረመው



አዲስ አበባ፡- ደቡብ ሱዳን የናይል ተፋሰስ የትብብር ማዕቀፍ ስምምነትን ማፅደቋ ለኢትዮጵያ ትልቅ የዲፕሎማሲ ስኬት ማረጋገጫ ነው ሲሉ ፕሮፌሰር ያዕቆብ አርሳኖ ገለጹ፡፡

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካ ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምህርና የዓባይ ውሃ ጉዳይ ተመራማሪ ፕሮፌሰር ያዕቆብ አርሳኖ ደቡብ ሱዳን የናይል ተፋሰስ የትብብር ማዕቀፍ ስምምነት ማፅደቋን አስመልክቶ ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር በነበራቸው ቆይታ፤ ኢትዮጵያ ከአሁን በፊት የናይል ተፋሰስ ሀገራትን በማስተባበር፤ ሙግትና ሀሳብ ከማመንጨት ጀምሮ በርካታ ሥራዎችን ስትሠራ መቆየቷን ተናግረዋል፡፡ ከ14 ዓመታት በፊት የፀደቀውና ለ11 ዓመታት ድርድር የተካሄደበት የትብብር ማዕቀፍ አሁን ያለበት ደረጃ ላይ መድረሱ ለኢትዮጵያ ዲፕሎማሲያዊ ስኬትን ያሳያል ብለዋል፡፡

እንደ ፕሮፌሰር ያዕቆብ ገለጻ፤ ኢትዮጵያ ለረጅም ዓመታት የናይል ተፋሰስ የትብብር ማዕቀፍ ለማዘጋጀትም ሆነ የትብብር ማዕቀፉ በናይል ተፋሰስ ሀገራት እንዲፈረም ትልቅ ጥረት፣ አስተዋፅዖና ተጋድሎ አድርጋለች፡፡ አሁን ላይ


ደቡብ ሱዳን ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል




ወይዘሮ አዳነች አቤቤ

## አዲስ አበባ ከተማ በተጠናቀቀው በጀት ዓመት

- 146 ነጥብ 84 ቢሊዮን ብር ገቢ ተሰብስቧል
- ከ291 ሺህ በላይ ዜጎች ቋሚ የሥራ ዕድል ተፈጥሯል
- ከውጭ ሀገር ቱሪስቶች 59 ነጥብ 73 ቢሊዮን ብር ገቢ ተገኝቷል


ገጽ 6


## በአብዛኛዎቹ ክልሎች የአጀንዳ ማሰባሰብ ሥራውን እስከ ነሐሴ መጨረሻ ለማጠናቀቅ ታቅዷል

- በምክክር ሂደቱ ላልተሳተፉ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጥሪ ቀርቧል

ሄለን ወንድምነው

አዲስ አበባ፡- በአብዛኛዎቹ ክልሎች የአጀንዳ ማሰባሰብ ሥራውን እስከ ነሐሴ መጨረሻ ለማጠናቀቅ መታቀዱን የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን አስታወቀ፡፡ በምክክር ሂደቱ ላልተሳተፉ የፖለቲካ ፓርቲዎች በቀጣዩ የምክክር ሂደት እንዲሳተፉ ጥሪ ቀርቧል፡፡


በአብዛኛዎቹ ክልሎች... ወደ ገጽ 4 ዞሯል





# ተሽከርካሪዎች ላይ የሚደረገው ድንገተኛ የቴክኒክ ፍተሻ ተጠናክሮ ይቀጥላል

- 20ሺ. ተሽከርካሪዎች ድንገተኛ ፍተሻ ተደርጎባቸዋል
- 4ሺ. ያህል ተሽከርካሪዎች ጉድለታቸውን እንዲያስተካክሉ ተደርጓል

**ዮርዳኖስ ፍቅሩ**



አዲስ አበባ፡- ተሽከርካሪዎች ላይ የሚደረገውን ድንገተኛ የቴክኒክ ፍተሻ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል የአዲስ አበባ አሽከርካሪ ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን አስታወቀ።

የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር፣ ደሳለኝ ተረፈ (ኢንጂነር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ በተሽከርካሪዎች ውጫዊና ውስጣዊ አካል ላይ የሚታዩ ጉድለቶችን ለማስተካከል በአሽከርካሪዎች ላይ የሚደረገውን ድንገተኛ ፍተሻ ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል።

በተጠናቀቀው የ2016 ዓ.ም በጀት ዓመት ከ500ሺ. በላይ ተሽከርካሪዎች የቦሎ ምርመራ ማድረጋቸውን የጠቀሱት ዳይሬክተሩ፤ በ20ሺ. መኪኖች ላይ ድንገተኛ ፍተሻ መደረጉን አስታውቀዋል።

ተሽከርካሪዎች በዓመት አንድ ጊዜ የቦሎ ምርመራ ስላደረጉ ብቻ ዓመቱን ሙሉ ጤናማ ሆነው ይዘልቃሉ ማለት አይደለም ያሉት ዳይሬክተሩ፣ በተሽከርካሪዎች ላይ የሚደረገውን ድንገተኛ ፍተሻ ተጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል።

በበጀት ዓመቱ ድንገተኛ ፍተሻ የተደረገባቸው ተሽከርካሪዎች ቁጥር በመዲናዋ ካለው የተሽከርካሪ ቁጥር አንጻር እጅግ አነስተኛ መሆኑንም አንስተዋል።

ዳይሬክተሩ እንደተናገሩት፣ ተሽከርካሪዎች ዓመታዊ የቦሎ ምርመራ ለማድረግ ወደ ምርመራ ተቋማት ሲሄዱ አስቀድመው ጋራዥ ገብተው ተሽከርካሪዎቻቸው ያለበትን ችግር ስለሚያስተካክሉ ብዙ ችግር አይገኝባቸውም።

ተሽከርካሪዎቹ በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ ምርመራ አድርገው ቦሎ ስለታደሰላቸው ብቻ ዓመቱን ሙሉ ብቁ ሆነው ይዘልቃሉ ማለት አይደለም ያሉት ደሳለኝ (ኢንጂነር)፣ በየመናኸሪያው የሚደረገው ድንገተኛ ምርመራ በቴክኒክ ብልሽት ሳቢያ የሚደርሱ የትራፊክ አደጋዎችን በመቀነስ ረገድ ከፍተኛ ሚና እንዳለው ተናግረዋል።

በባለሥልጣኑ የተሽከርካሪ ድንገተኛ ምርመራ እና ተቋማት ብቃት ማረጋገጥ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ትግሌ ኩንቶ በበኩላቸው በበጀት ዓመቱ ድንገተኛ ፍተሻ ከተደረገባቸው ተሽከርካሪዎች መካከል አራት ሺህ ያህሉ ጉድለት ተገኝቶባቸው በድጋሚ ጋራዥ ገብተው ችግራቸውን እንዲያስተካክሉና ወደ አገልግሎት እንዲመለሱ የማድረግ ሥራ ተሠርቷል።

ፍሬናቸው፣ የትዕይንት መከታተያ መሣሪያዎቻቸው፣ የዝናብ መጥረጊያና ሌሎችም ውጫዊና ውስጣዊ አካላቸው በአግባቡ የማይሠሩና ለአደጋ የተጋለጡ ተሽከርካሪዎች በድጋሚ ችግራቸውን እንዲያስተካክሉ ከተደረጉ መካከል እንደሚገኙበት አቶ ትግሌ አስታውቀዋል።

አንድ ተሽከርካሪ የቦሎ ምርመራ አድርጎ ሰርተፊኬት ከተሰጠው በኋላ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሊበላሽ ይችላል ያሉት አቶ ትግሌ በድንገተኛ ፍተሻ እያየን ያለነው ግኝት ይህንን እያረጋገጠልን ነው ብለዋል።

በበጀት ዓመቱ የተደረገው ድንገተኛ ፍተሻ አነስተኛ መሆኑን አንስተው፣ ድንገተኛ ፍተሻ የሚደረግባቸውን ተሽከርካሪዎች ቁጥር ወደ 100ሺዎች ለማሳደግ ቋሚ የታክሲ መናኸሪያዎች ቢዘጋጁ ለሥራው ምቹ እንደሚሆን አመላክተዋል።

ከድንገተኛ ፍተሻ ጋር ተያይዞ የተቀመጠው መመሪያ ተሽከርካሪዎች ሰው ጭነው በሚንቀሳቀሱበት ጊዜ ፍተሻ ማድረግን እንደማይደግፍ ያነሱት፣ ዳይሬክተሩ መመሪያው ማስተካከያ ተደርጎበት ለሥራው ምቹ በሆነ መልኩ ቢቀረጽ መልካም እንደሚሆን ተናግረዋል።

የቴክኒክ ብልሽት ለትራፊክ አደጋ ቁጥር መጨመር ከፍተኛ አስተዋፅዖ እንደሚያደርግ ያነሱት አቶ ትግሌ፣ ተሽከርካሪዎች የቴክኒክ ብልሽት እያላቸው ሰው ጭነው እንዳይንቀሳቀሱ በማድረግ በኩል አሽከርካሪዎችና የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ ትኩረት ሰጥተው እንዲከታተሉም አሳስበዋል።



አቶ ሻፌ ዑመር

## ባለሥልጣኑ ከኮንትሮባንድ ቁጥጥርና ከቅጣት 190 ሚሊዮን ብር የሚጠጋ ገቢ አገኘ

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- በ2016 በጀት ዓመት ከኮንትሮባንድ መከላከልና ከተለያዩ ቅጣቶች 190 ሚሊዮን ብር የሚጠጋ ገቢ ማግኘቱን የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለሥልጣን አስታወቀ።ባለሥልጣኑ በቡና ንግድ የገበያ ሰንሰለት ላይ የሚታየውን ኮንትሮባንድ ለመቀነስ በሶፍትዌር የታገዘ የቁጥጥር ዘዴ መጠቀሙን ገልጿል።

የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለሥልጣን ምክትል ዳሬክተር አቶ ሻፌ ዑመር ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ባለሥልጣኑ የቡና ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ከሚሠራቸው ሥራዎች ጎን ለጎን ሕገወጥ የቡና ዝውውር ላይ የሚያከናውነውን ቁጥጥሩ አጠናክሯል።

የጭነት መኪኖች በሚያልፉባቸው ኬላዎች ላይ ጥብቅ ቁጥጥርና ርምጃዎችን እየተወሰደ መሆኑን ጠቁመው፤ የሚጠበቅባቸውን ቀነ ገደብና መስፈርት ማሟላት ካልቻሉ የምርት አቅራቢዎችና ላኪዎች ቅጣት እንዲሁም ከኮንትሮባንድ ቁጥጥር 190 ሚሊዮን ብር የሚጠጋ ገንዘብ መገኘቱን አስረድተዋል።

ከአጠቃላይ ገቢው ከ92 ሚሊዮን 500 ሺህ ብር በላዩ በኮንትሮባንድ ከተያዙ ምርቶች የተገኘ መሆኑን አንስተው፤ ይህም ከ2015 ዓ.ም ጋር ሲነጻጸር የስምንት ሚሊዮን ብር ብልጫ እንዳለው አቶ ሻፌ ገልጸዋል።

ባለሥልጣኑ በቡና ምርት ላይ ያሉ ሕገወጥ አሠራሮችን ለመቆጣጠር ሶፍትዌሮችን ማልማቱን ገልጸው፤ በዚህ ሶፍትዌርም ከምርት ሽኝት ጣቢያ እስከ መዳረሻው ባሉ ሂደቶች ላይ ቁጥጥር እየተደረገ ነው ብለዋል።

በተጨማሪ በእያንዳንዱ ኬላ ላይ ከተለያዩ የሕግ አካላትና የጉምሩክ ሠራተኞች ጋር በመተባበር ሕገወጦችን ለመያዝ ፍተሻ እንደሚደረግ አመላክተዋል።

አቶ ሻፌ በሕገ ወጥ ቡና ዝውውር ቁጥጥር ሂደት ላይ የፀጥታ አካላት ሚና ከፍተኛ መሆኑን ገልጸው፤ ባለፉት ሦስት ወራት ብቻ በፌደራል ፖሊስ፣ በአዲስ አበባ ፖሊስና በኦሮሚያ ፖሊስ ትብብር 10 የጭነት ተሽከርካሪ ሙሉ ቡና መያዙን እንዲሁም ሐሰተኛ ሰነድ እያሠሩ ሕጋዊ አስመስለው ለማለፍ የሚሞክሩ ሕገወጥ አካላት መያዛቸውን አስታውቀዋል።

ምክትል ዳሬክተሩ እንደተናገሩት፤ የኮንትሮባንድ ንግድ በክትትል ብቻ ሊፈታ የሚቻል ጉዳይ ባለመሆኑ ሕጋዊ ሆኖ በትክክለኛው መስመር መሥራት ያለውን ፋይዳ በተመለከለተ የግንዛቤ ፈጠራ ሥራዎች በትኩረት ይሠራሉ።

ባለሥልጣኑ የገበያ መዳረሻዎችን የማስፋት እንዲሁም ባለልዩ ጣዕም ቡናን በዓለም አቀፍ የገበያ እሴት ሰንሰለት በማስተዋወቅ አቅራቢዎች የተሻለ ገቢ እንዲያገኙ ድጋፍ እያደረገ መሆኑን አስረድተዋል።

# የጨረቃው ድምቀት - ኢቫንጋዲ ጭፈራ

**ማርቆስ በላይ**



ፎቶ፡- ኢዮብ ተፈሪ

ስለ ሐመሮች ደራሲ ፍቅረማርቆስ ደስታ ከቡስካ በስተጀርባና በሌሎች መጽሐፍቱ በርካታ ነገሮችን ከትቦላቸዋል። ሐመሮች በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል በደቡብ ኦሞ ዞን ውስጥ ከሚገኙ ብሔረሰቦች አንዱ ናቸው። «ሐመር» በተራራና በድንጋይ መካከል የሚኖሩ፣ የተዋሓዱና የተቀላቀሉ ሕዝቦች መሆናቸው ይነገራል ሐመሮች ከብት እርባታ፣ ንብ ማነብና በቆሎና ማሽላ ምርት እንደሚተዳደሩ ይታወቃል።

ታዲያ በሐመሮች ኢቫንጋዲ የሚባል በጨረቃ ብርሃን የሚጨፈር የጭፈራ ሥርዓት አላቸው። በኢቫንጋዲ ከ5 አይነት በላይ የጭፈራ ስልቶች አሉ። በጭፈራው በዘፈቀደ መወዛወዝ ሳይሆን መጀመሪያ ወንዶች ብቻ እየዘለሉ ሰውነታቸውን ያሟሙቃሉ ቀጥሎ ወንዶች አባራሪ ሴቶች አቅጣጫ ቀያሪ እየሆኑ ሲዞሩ ይስተዋላል።

አቶ ኤልያስ ኮሮቶ የቱርሜ ከተማ ምክትል ከንቲባ ናቸው፡-«ኢቫንጋዲ» ዕድሜቸው ከ18 ዓመት በላይ የሆኑ የሐመር ወጣት ወንዶችና ልጃገረዶች የሚሳተፉበት ባሕላዊ ጭፈራ ነው ይላሉ።

ጭፈራው በየሦስት ቀን አንዴ በሐመር መንደሮች ምሽት በጨረቃ ይካሄዳል። «ኢቫንጋዲ» በአዝመራ ወቅት አካባቢው ሠላም ሆኖ ጨረቃ ሲሆንና ሰብል ሲደርስ ወጣቶች ከአካባቢ ወደ ሌላ አካባቢ እየተዘዋወሩ አብረው የሚጨፍሩበት የደስታ መግለጫ ባሕላዊ ጭፈራ እንደሆነም ይገልጻሉ።

ማታ ላይ በጨረቃ በሚካሄደው የኢቫንጋዲ የሠላምና የፍቅር ጭፈራ ላይ በርካታ የሀገር ውስጥና የውጭ ጎብኚዎች ይታደማሉ። ጎብኚዎች ጭፈራውን በማየት፣ አብረው ጨፍረው በጋራ ደስታቸውን እንደሚካፈሉም ይናገራሉ።

የኢቫንጋዲ ጭፈራ ባሕላዊ እሴቱንና ሥርዓቱን ጠብቆ ሳይበረዝ እንዲቀጥል የአካባቢው አስጎብኚ ማኅበራት እየሠሩ ነው። ማንኛውም ጎብኚ ብቻውን ወደ ጉብኝት መግባት የማይችል በመሆኑ እንግዶች ከአስጎብኚ ማኅበራት ጋር በመሆን ጎብኚታቸውን እንዲያካሂዱ እየተደረገ መሆኑን ያስረዳሉ።

ወጣቶች በየመንደሩ የሚደረጉ የኢቫንጋዲ ጭፈራ ቦታዎችን በመጠበቅ እያስቀጠሉ ነው። በአካባቢው የሠላም ሁኔታ አስተማማኝ በመሆኑ የቱሪዝም ፍሰቱ እየጨመረ መምጣቱንና ለጎብኚዎች አገልግሎት የሚሰጡ በርካታ ሎጆች ተገንብተው ወደ ሥራ መግባታቸውን ጠቁመዋል።

እንግዶች ለጉብኝት በሚመጡበት ወቅት የአካባቢው ማኅበረሰብ በእንግዳ ተቀባይነት ባሕሉ በፍቅር ያስተናግዳል። ከውጭ ሀገር ጎብኚዎች በተጨማሪ የሀገር ውስጥ ጎብኚዎች ቁጥር እየጨመረ መቷል ሲሉ አክለዋል።

ወጣት አርጊ በጀቱም እንደምትገልጸው፡-ልጃገረዶች በጊዜ እራት ሠርተው ለኢቫንጋዲ ጭፈራ ይወጣሉ። ወጣቶች ሲሰባሰቡ ኢቫንጋዲ እንሂድ ተባብለን፣ ተጠራርተን ቆዳ በማሰር ወደ ጭፈራ እንመጣለን ስትል ትገልጻለች።

ልጃገረዶች ወደ ጭፈራ ከመምጣታቸው በፊት ጨሌ አጥበው ገላቸውን ታጥበው ለጭፈራ ይመጣሉ። ቆዳ፣ ጨሌና አስፈላጊው ጌጣጌጥ ለብሰን ቅባት ተቀብተን ካልመጣን ወንዶች ይስቁብናል ስትል ትናገራለች።

ወጣት ቡኩ አርጎ እንደሚናገረው፡-በኢቫንጋዲ ምርት ሳይደርስና ሳይሰበሰብ መጨፈር የለም። ሰብል ሲደርስ ተሰባስበን ደስታችንን በምሽት የምንገልጽበት ባሕላዊ ጭፈራ ነው ሲል ይገልጻል።

ወንድ ልጅ ሰነፍ ከሆነ ልጃገረዶች አይፈልጉትም ምርጫቸውም መሆን አይችልም። ልጃገረዶች ጠንካራ፣ ታታሪ ወንድን ምርጫቸው እንደሚያደርጉ ይገልጻል።

ጭፈራውን በሳምንት ሦስት ጊዜ በተለያዩ መንደሮች ላይ ይጨፈራል። በጭፈራው ወቅት ሠላም ይምጣ፣ መልካም ነገር ይግጠመን፣ ዝናብ ይዝነብ፣ ሰብሎች ያሽቱ፣ ለጓደኞቻችን መልካም ነገር ይግጠማቸው እያልን እናዜማለን ሲል ይናገራል።

ከጭፈራው በኋላ በጭፈራው የተሳተፉ ሴቶች ወደ ቤተሰቦቻቸው የሚሄዱ ሲሆን ወንድ ወጣቶች አንድ ቦታ ላይ እናድራለን። በነገታው ፍየሎችን በመያዝ ወደ መጡበት እንደሚሄዱ ይገልጻል።

ሀሳቡን ሲያጠቃልልም የኢቫንጋዲ ጭፈራን በእጃችን እያጨበጨብን እየተጠቀምን ያለነው። ይህ ደግሞ ድካም ያመጣል፣ አንድ ወንድ ደካማ ከሆነ ደግሞ በልጃገረዶች ዘንድ ተመራጭ አይሆንም። በመሆኑም ለጭፈራው የሚያስፈልጉ ባሕላዊ መሣሪያዎች እንደሚያስፈልጋቸው ነው የጠቆመው።

# ስሱዳኑ ጦርነት ዘላቂ መፍትሔ ለማምጣት የተደረገው ጉዞ

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

ሀገራት በሁለንተናዊ የለውጥ ጎዳና ለመጓዝና ለጋራ ችግሮቻቸው መፍትሔ ለማበጀት እርስ በእርስ የትብብር ግንኙነት ሲፈጥሩ ማየት አዲስ ነገር አይደለም። ተፈጥሯዊ ሀብት ለመጠቀም እንዲሁም የሰው ልጆችን እውቀትና ጥበብ ተጠቅሞ ዓለምን ለመለወጥ ሀገራት በጋራ ይመክራሉ፣ በትብብር ይሠራሉ። ለችግሮችን መፍትሔ ለማበጀት ይጥራሉ።

ምክንያቱም በራስ ፍላጎት ብቻ ተሸብቦ ትብብርን መግፋት ደግሞ ዓለምን ከድጡ ወደ ማጡ ከማውረድ ውጪ የሚፈይደው አንዳች ረብ ስለሌለው ነው። ትብብርና መልካም ግንኙነት በማደግ ላይ ላሉ ሀገራት ይበልጥ የሚያስፈልግ ሆኖ ቢታይም ኃያላንም በራሳቸው የቆሙ ለማስመሰል ብዙ ይጣሩ እንጂ አንዳቸው ካለአንዳቸው ድጋፍ ሙሉ የሆኑ እንዳልሆኑ የዘርፉ ምሑራን ያስገነዝባሉ።

የራሳቸው ጥቅም ብቻ የሚያሳድዱና የሌላውን ከሌላው ድርሻ ካልቀመሱ የእግር እሳት የሚሆንባቸው አካላት በማደግ ላይ ባሉ ሀገራት ጫና ሲፈጥሩ ይስተዋላል። አፍሪካም የዚህ ገፈት ቀማሽ ናት። በየጊዜው የሚጎነጎኑ ሴራዎች በእጅጉ ጎድተዋታል።

ለዚህም ይመስላል ለአፍሪካዊ ችግር አፍሪካዊ መፍትሔ ያሻል የሚባለው። አሁን አሁን መርሕ ተደርጎ እየተሠራበት ቢሆንም ለአፍሪካዊ ችግር አፍሪካዊ መፍትሔ የሚለው መርሕ ገና ከመፀነሱ ኢትዮጵያ በተግባር ኖራዋለች። ኢትዮጵያ በትብብር ለመሥራት ሁሌም ፊት አውራሪ ናት ቢባልም ማጋነን አይሆንም። ለዚህም ደግሞ ጥንታዊና የዘመናዊ ዲፕሎማሲ ጉዞዎች ሕያው ምስክሮች ናቸው።

ጎረቤት ተረብሾ ሀገር ሠላም የማትሆን መሆኑን የሚገነዘቡት የኢትዮጵያ መንግሥታት ከሀገራቸው እኩል ለጎረቤቶቻቸው ሲጨነቁና ፖሊሲያቸው ለጎረቤት ሠላምና አብሮ የማደግ እሴቶች እንዲጎለብቱ አድርገው ይቀርጻሉ።

የአሁኑ መንግሥትም የጎረቤት ችግር የእኛም ነው በማለት በግምባር ቀደምትነት የጎረቤት ሀገራት ጋር



በፍቃዱ ቦጋለ(ረ/ፕ)

አብሮ ለማደግና ሠላምን ለማረጋገጥ የሚጥር ነው። የሱዳኑ የእርስ በእርስ ጦርነት ከተጀመረ ወዲህ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እስከ ሱዳን ድረስ ሂደው የጎበኙ የመጀመሪያው መሪ መሆናቸው ለዚህ ጥሩ ማሳያ ነው።

የጠቅላይ ሚኒስትሩ የሱዳን ጉዞ በሱዳን ሠላምን ከማረጋገጥ በሻገር ለኢትዮጵያም ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ትሩፋት ይዞ እንደሚመጣ የዘርፉ ምሑራን ይናገራሉ።

ለኢፕድ አስተያየታቸውን የሰጡት በውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት የአፍሪካ ቀንድ ተመራማሪ በፍቃዱ ቦጋለ (ረ/ፕ) በቀጣናው ትብብርን ማሳደግና በንግግር መርሕ መጓዝ ከኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ጠቀሜታው ባሻገር በቀጣናው አሸባሪነትን ለመዋጋት እንዲሁም የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ ችግሮች ለመቀነስ ትልቅ አስተዋፅዖ ያለው መሆኑን ይብራራሉ።

በተለይ የጠቅላይ ሚኒስትሩ የሱዳን ጉዞ በሌሎች ጦርነቶች ምክንያት ትኩረት የተነፈገውን የሱዳኑን የእርስ በእርስ ጦርነት ትኩረት እንዲያገኝ የሚያደርግ ስለመሆኑንም ይጠቅሳሉ።

የእርስ በእርስ ጦርነቱ ለቀጠናው የሚጎዳ በመሆኑ ቅድሚያ ሰጥቶ ሱዳን እንድትረጋጋ ማድረግ አስፈላጊ ጉዳይ ነው የሚሉት ረዳት ፕሮፌሰሩ፤ ለአብነትም



አደም ካሚል(ፕ/ር)

የኢትዮጵያውያንም ሆነ የሱዳን ሕዝቦችን ከጉስቁልና ለማውጣትና በጦርነቱ ተቋርጠው የቆዩ የሁለቱ ሀገራት የኢኮኖሚ ማዕቀፎች ተግባራዊ ለማድረግ ከፍተኛ ሚና እንደሚኖረው ያስረዳሉ።

ኢትዮጵያ ዛሬም የሕዝቦች ለሕዝቦች ግንኙነት ከማጠናከር ጎን ለጎን በኢኮኖሚው ረገድ አብሮ የማደግን እሴትን ለማጎልበት የተለያዩ መሠረተ ልማት ትስስር እያደረገች እንደምትገኝ ይገልጻሉ።

የመንገድ፣ የውሃና የመብራት መሠረተ ልማት በዓበይትነት ሊጠቀሱ ከሚችሉ ጉዳዮች መካከል ናቸው የሚሉት በፍቃዱ (ረ/ፕ)፤ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ጉዞ በቀጣይ ሁለቱ ሀገራት ለሚኖራቸው ግንኙነት መንገድ የሚከፍትና የጋራ ችግሮችን በትብብር ለማስወገድ መሠረት የሚጥል መሆኑንም ያክላሉ።

የጠቅላይ ሚኒስትሩ ጉዞ እንደ ሀገር የታሰቡ የልማት ግቦች ለማሳካትና የቀጠናው ሠላም ማረጋገጥ ተገቢ መሆኑን ጠቅሰው፤ ጦርነቱ ብዙ እጆችና የተለያዩ አካላት ፍላጎት ያለበት በመሆኑ ለአፍሪካዊ ችግር አፍሪካዊ መፍትሔ መርሕ አስፈላጊነት የሚያመላክት ነው ይላሉ።

የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ለጎረቤት ሀገራት ቅድሚያ መስጠቱና መሪዎችም ለጋራ ጥቅም ቅድሚያ መስጠታቸው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅም እንዳይነካ ከማድረግ ጎን ለጎን የተለያዩ ጠቀሜታዎች ማግኘት እንደቻለች ይጠቁማሉ።

በቀጣይም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅም ላለማስነካትና ዘላቂ ልማት ግቦች ለማረጋገጥ ከጎረቤት ጋር አብሮ የማደግ መርህ ተግባራዊ ከማድረግና የበለጠ ማጠናከር እንደሚያስፈልግ ነው የተናገሩት።

ኢትዮጵያ ለአፍሪካዊ ችግር አፍሪካዊ መፍትሔ መርሕ አድርጋ መሥራት ብቻ ሳይሆን በቀደሙ ጊዜያትም የጋራ እሳቤን ከሚያጎለብቱ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትና የአፍሪካ ኅብረት መሥራች ሀገር መሆኗን ያስታውሳሉ።

የጠቅላይ ሚኒስትሩ የሱዳን ጉዞ ኢትዮጵያ ከሁለቱ ተፋላሚ ኃይሎች ገለልተኛ ሆና ለሀገሪቱ መረጋጋት እንዲሁም ለቀጣናው ሁለንተናዊ ሠላም ያላትን ቁርጠኝነት ያሳየችበት ነው የሚሉት ደግሞ የታሪክ ምሑርና የኢትዮ-ዓረብ የፖለቲካ ጉዳዮች ተንታኝ አደም ካሚል (ፕ/ር) ናቸው።

ኢትዮጵያና ሱዳን የሚጋሯቸው በርካታ ጉዳዮች በመኖራቸው የሱዳን ጉዳት በቀጥታ ኢትዮጵያን ይጎዳል የሚሉት አደም (ፕ/ር)፤ ሱዳን በውስብስብ ችግር ውስጥ ሆና ጠቅላይ ሚኒስትሩ ወደ ሱዳን መጓዛቸው ኢትዮጵያ ለዘመናት የአብሮነትና የትብብር እሴት እንደ አዲስ ያደሱበት መሆኑን ይናገራሉ።

ትብብርና በጋራ የማደግ እሳቤ ያለው ጠቀሜታ እንዲሁ በቀላሉ የሚታይ ባይሆንም በተለይ አፍሪካን ለመሰሉ አሕጉራትም ሆኑ ሀገራት ትብብርና ቅንጅትን ለሁለንተናዊ እድገት ዋነኛ መሣሪያ መሆኑን ይገልጻሉ።

የሱዳን ሠላም ማግኘት ለኢትዮጵያ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው የሚሉት አደም (ፕ/ር)፤ ሱዳንና ኢትዮጵያ ከታሪክም ሆነ የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት ያላቸው ቀረቤታ ከፍተኛ በመሆኑ ሁለቱ ተፋላሚ ኃይሎች ለማደራደር የሚደረገው ጥረት ፍሬያማ ያደርገዋል ባይ ናቸው።

በሱዳን ሁለቱ ኃይሎች ልዩነቶቻቸውን በንግግር የማይቋጩ ከሆነ አሸባሪነት፣ ስደት እንዲሁም የኢኮኖሚ ቀውስ በአፍሪካ ቀንድ የሚያባብስ በመሆኑ በኢትዮጵያ በኩል ሱዳን ሰላም የሚደረገው ጥረት ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት ያሳስባሉ።

---

# በየአካባቢያችን ላሉ ድጋፍ ለሚሹ የኅብረተሰብ ክፍሎች እጃችንን ልንዘረጋ ይገባል

**ዮርዳኖስ ፍቅሩ**

አዲስ አበባ፡- በየአካባቢያችን ላሉ ድጋፍ ለሚሹ የኅብረተሰብ ክፍሎች እጃችንን ልንዘረጋ እንደሚገባ ተገለጸ።

የተባበሩት ዓረብ ኢምሬት ኤምባሲ ለአራት የተለያዩ መረዳጃ ማኅበራት የ3 ነጥብ አንድ ሚሊዮን ብር የአልባሳትና ቁሳቁስ ድጋፍ አበርክቷል።

በድጋፍ ሥነ ሥርዓቱ የተገኙት በሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የሕዝብ ግንኙነት ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ወይዘሮ ሐረጓ ማሞ፣ ኤምባሲው ከዚህ ቀደምም ከሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ጋር በመተባበር ድጋፍ ለሚሹ የኅብረተሰብ ክፍሎች ልዩ ልዩ ድጋፍ ማድረጉን አስታውሰዋል።

ሁላችንም በየአካባቢያችን ላሉ ድጋፍ ለሚሹ የኅብረተሰብ ክፍሎች እጃችንን ልንዘረጋ ይገባልም ብለዋል።

ኃላፊዋ እንዳሉት፣ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ “በጎነትና አብሮነት ለኢትዮጵያ ከፍታ” በሚል መሪ ሐሳብ ከተለያዩ አካላት ጋር በመሆን በሁሉም የሀገራችን ክፍሎች በርካታ የበጎ አድራጎት ተግባራት እያከናወነ መሆኑን አንስተዋል።

ኤምባሲው ድጋፍ ያደረገላቸው የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ለበርካታ ድጋፍ ለሌላቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች መጠለያ መሆን የቻሉ ናቸው ብለዋል።

ወቅቱ ልዩ ልዩ የበጎ አድራጎት ሥራዎች የሚሠሩበት መሆኑን ያነሱት ወይዘሮ ሐረግ ባለሀብቶችና በተለያየ ሙያና እድሜ ላይ ያሉ ዜጎች የክረምቱን ወራት ድጋፍ ለሚሹ የኅብረተሰብ ክፍሎች ድጋፍ በማድረግ እንዲያሳልፉም ጥሪ አስተላልፈዋል።

እርስ በእርስ መደጋገፍ የኢትዮጵያውያን መገለጫ ነው ያሉት ኃላፊዋ፣ ድጋፍ ማድረግን በአቅራቢያችን ከሚገኙ ድጋፍ ከሚሹ አረጋውያን፣ ሴቶችና ሕጻናት በመጀመር ይህን እሴት ማጠናከር ይገባናል ብለዋል።

ኤምባሲው ድጋፍ ካደረገላቸው የበጎ አድራጎት



ወይዘሮ ሐረጓ ማሞ

ድርጅቶች መካከል የ “የወደቁትን አንሱ የነዳያን የበጎ አድራጎት ማኅበር” ዋና ሥራ አስፈጻሚ ቀሲስ ሳምሶን በቀለ ለተደረገላቸው ድጋፍ ኤምባሲውን አመስግነው፣ ማኅበሩ ለዛሬ የደረሰው ከተለያዩ አካላት በሚደረግለት ድጋፍ መሆኑን ተናግረዋል።

ማኅበሩ ከተመሠረተበት ከ1990 ዓ.ም ጀምሮ በርካታ ደጋፊና ተመልካች ያልነበራቸው አረጋውያንንና ሕሙማንን በመጠለያ ልብስና በምግብ ሲያግዝ መቆየቱንም አንስተዋል።

በአሁኑ ወቅትም 300 ያህል አረጋውያንና ሕሙማንን በቋሚነት እየደገፈ እንደሚገኝም አስታውቀዋል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሌላውን በመደገፍና የወደቀውን በማንሳት ረገድ ያለው ልምድ ትልቅ ነው ያሉት የማኅበሩ ሥራ አስፈጻሚ፣ በየአካባቢው ያሉ ደጋፊና ጠያቂ የሌላቸው የኅብረተሰብ ክፍሎችን ለማገዝ ከዚህ ቀደም ከነበረው በበለጠ ሁኔታ ድጋፉን እንዲያጠናክር ጠይቀዋል።

---

# የእንሰት ምርትን ለማግኘት የሚወስደውን ጊዜ ወደ አንድ ዓመት ተኩል ዝቅ ማድረግ ተችሏል

## - በዞኑ ዘንድሮ 43 ሚሊዮን የእንሰት ችግኝ ተተክሏል

**ማርቆስ በላይ**

ዲላ፡-እንሰት ምርት ለማግኘት ይወስድ የነበረውን ጊዜ ወደ አንድ ዓመት ተኩል ዝቅ ማድረግ መቻሉን የጌዲኦ ዞን አስታወቀ። በዘንድሮው ዓመት 43 ሚሊዮን የእንሰት ችግኝ መተከላቸውም ተገልጿል።

የጌዲኦ ዞን አስተዳዳሪ ዝናቡ ወልዴ (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፡- የእንሰት ምርትን ለማግኘት ይወስድ የነበረውን ከአምስት ዓመት በላይ ጊዜ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ወደ አንድ ዓመት ተኩል ዝቅ ማድረግ ተችሏል።

እስከ ሰባት ዓመት ይወስድ የነበረውን የእንሰት ምርት የተለያዩ አካባቢውን መሠረት ያደረጉ ቴክኖሎጂን በመጠቀም በአንድ ዓመት ከስድስት ወር ማድረስ ተችሏል።

በዞኑ በባለፈው ዓመት ከአርሶ አደሮች ጋር በመሆን ከ32 ሚሊዮን የእንሰት ችግኝ ተተክሏል ያሉት አስተዳዳሪው፣ ዘንድሮው ዓመት 43 ሚሊዮን የእንሰት ችግኝ ተተክሏል ብለዋል።

የምግብ ዋስትናን በማረጋገጥ ከችግር ለመውጣት በሚደረገው ጥረት የእንሰት ምርት ትልቅ ድርሻ እንዳለው ጠቅሰው፣ ዞኑ የእንሰትና ቡና ተክል በስፋት የሚገኝበት በመሆኑ ምርታማነትን ሊያረጋግጥ በሚችል ደረጃ ሰፋፊ ሥራዎች መሠራታቸውን ገልጸዋል።

እንሰት አምራች የሆነ አካባቢዎች ተለይተው በቴክኖሎጂ የተደገፈ ድጋፍ እየተደረገ መሆኑን ገልጸው፣ ከአምስት እስከ ሰባት ዓመት እየጠበቀ ምርት ይሰጥ የነበረውን እንሰት ቴክኖሎጂን በመጠቀም በአንድ ዓመት ከስድስት ወር ምርት መስጠት መጀመሩን ተናግረዋል።

በዞን ደረጃ እንሰትን በስፋት አምራች አካባቢዎች ተለይተው ሲሠራ መቆየቱን የገለጹት ዝናቡ (ዶ/ር)፣ ከለውጡ በፊት አካባቢውን መሠረት ያደረገ የግብርና



ዝናቡ ወልዴ(ዶ/ር)

ድጋፍ ተደርጎ አያውቅም ብለዋል።

በጌዲኦ ከጭላንጭል ወደ የሚጨበጥ ብርሃን ለመሸጋገር የተያዘውን ሀገራዊ እቅድ ለማሳካት የሚያስችል ሥራ እየተሠራ መሆኑን በመግለጽ፣ የእንሰት ምርትና ምርታማነትን ሊያረጋግጥ በሚችል ደረጃ ሰፋፊ ሥራዎች መሠራታቸውን ገልጸዋል።

በሌላ በኩል በቡና ልማት ሥራ 75 ሺህ ሄክታር መሬት በላይ በቡና መሸፈኑን ጠቅሰው፣ ከዞኑም በየዓመቱ እስከ 27 ሺህ ቶን ቡና ምርት ለማዕከላዊ ገበያ እንደሚቀርብ ተናግረዋል።

በለውጡ መንግሥት ለአርሶ አደሮች ትኩረት በመስጠት የቡናን ምርት ለማሳደግ መሠራቱን ጠቅሰው፣ ቡናን በሞዴል አርሶ አደሮች ደረጃ በሄክታር 19 ኩንታል ምርት ማግኘት መቻሉን ጠቁመዋል።

በዞኑ ከ780 በላይ ቡና አምራች አርሶ አደሮች ወደ ገበያ እያቀረቡ እንደሚገኝ በመግለጽ፣ 350 በላይ የእሸት ቡና ኢንዱስትሪዎች በሥራ ላይ እንደሚገኙ ገልጸዋል።

# የግል ድርጅቶች ወደ ሥራ ከመግባታቸው በፊት በመመሪያና ደንቦች ዙሪያ ግንዛቤ ሊፈጠርላቸው ይገባል

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- የግል ድርጅቶች ወደ ሥራ ከመግባታቸው በፊት በመንግሥት በመመሪያና ደንቦች ዙሪያ ላይ ግንዛቤ መፍጠር እንደሚገባ የኢትዮጵያ አሠሪ ፌደሬሽኖች ኮንፌዴሬሽን ገለጸ።

የግል ድርጅቶች ሠራተኞች ማኅበራዊ ዋስትና አስተዳደር የግል ድርጅት ሠራተኞች የጡረታ መዋጮ አዋጅን አስመልክቶ ለኢትዮጵያ አሠሪ ፌዴሬሽኖች ኮንፌዴሬሽን ባለድርሻ አካላት የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ በትናንትናው እለት አካሂዷል።

የኢትዮጵያ አሠሪ ፌዴሬሽኖች ኮንፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት ጌታሁን ሁሴን (ኢ/ር) እንደገለጹት፤ የግል ድርጅቶች በሚሰማሩበት ዘርፍ ያሉ የመንግሥት ደንብና መመሪያዎችን አውቀው ማኅበራዊ ኃላፊነቶቻቸውን የመወጣት ግዴታ አለባቸው።

ይህንን አስመልክቶ በግሉ ዘርፍ በርካታ ችግሮች መኖራቸውን የገለጹ ሲሆን መመሪያዎቹን የሚያወጡ ተቋማት የአተገባበር ላይ ግንዘቤ እየፈጠሩ አለመሆናቸውን ተናግረዋል።

ለአብነትም የግል ድርጅቶች ሠራተኞች ማኅበራዊ ዋስትና አስተዳደር አሠሪዎች የሚተገብሯቸው በርካታ አዋጆች ቢኖሩትም በቂ የግንዛቤ ማስጨበጫ ባለመስጠቱ በርካታ የግል አሠሪዎች ለተለያ ችግሮች እየተጋለጡ እንደሚገኝ አንስተዋል።

ፕሬዚዳንቱ እነዚህን ችግሮች ለመፍታት የሀገር ውስጥም ሆነ የውጭ ኢንቨስተሮች ወደ ሥራ ከመግባታቸው በፊት መንግሥት የሀገሪቱን የኢንቨስትመንት መመሪያዎችን ማሳወቅ እንደሚገባ አሳስበዋል።

የግል ድርጅት ሠራተኞች ማኅበራዊ ዋስትና አስተዳደር ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚ መሠረት ዘለቀ ከዚህ ቀደም የጡረታ ገቢ የሚያገኙት የመንግሥት ሠራተኞች ብቻ የነበረ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ ግን ማንኛውም ከአንድ በላይ ሠራተኛ ቀጥሮ የሚያሠራ አሠሪ ከሠራተኛው ላይ የጡረታ መዋጮ እንዲቆርጥና እንዲያስገባ የሚያስገድድ አዋጅ መኖሩን ገልጸዋል።

ይህም በግል ድርጅት ተቀጥረው የሚሠሩ ሠራተኞችን እፎይ የሚያስብል መሆኑን ገልጸው፤ ነገር ግን በርካታ አሠሪዎች አዋጁን ባለመገንዘብ ለቅጣት እየተዳረጉ እንደሚገኝ ተናግረዋል።

አስተዳደሩ ይህንን ችግር ለመፍታትም ከተለያዩ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ግንዛቤ የመፍጠር ሥራ እየሠራ እንደሚገኝ ተናግረዋል፡፡

አቶ መሠረት በአሁኑ ጊዜ የጡረታ መዋጮ የመክፈል አስገዳጅ አሠራሮች በመፈጠሩ ምክንያት በርካታ መሻሻሎች መኖራቸውንና አብዛኛው የሚባለው የግል ድርጅት የጡረታ መዋጮን እየከፈለ እንደሚገኝ ገልጸዋል።

# በአብዛኛዎቹ ክልሎች...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ኢትዮጵያ ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር ፕሮፌሰር መስፍን አርዓያ ለመገናኛ ብዙኃን በሰጡት መግለጫ እንደገለጹት፤ በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ በጋምቤላ እና በሐረሪ ክልሎች የአጀንዳ ማሰባሰብ ሥራን ለማከናወን ከሐምሌ 10 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ ኮሚሽነሮችንና ባለሙያዎችን በማሠማራት የዝግጅት ሥራ እየተሠራ ይገኛል።

የክረምቱ ወቅት እንቅፋት በማይሆንባቸው ክልሎች እስከ ነሐሴ መጨረሻ ድረስ አጀንዳ የማሰባሰብ ሥራውን ለማጠናቀቅ መታቀዱን ገልጸው፤ በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር እና በሦስቱ ክልሎች አጀንዳ የማሰባሰብ ሥራው ከሚቀጥለው ሳምንት ጀምሮ ወደ ተግባር እንደሚገባ ተናግረዋል።

በአፋር ክልል ያለው ወቅታዊ የአየር ሁኔታ ከባድ ሙቀት ያለበት በመሆኑ በክልል ደረጃ የሚከናወነው አጀንዳ ማሰባሰብ ሥራ ጥቅምት 2017 ዓ.ም መጀመሪያ ላይ እንደሚከናወን አስታውቀዋል።

በአማራ ክልል ከ230 የሚሆኑ ተባባሪ አካላትን የማሠልጠን ሥራ መሠራቱን ገልጸው፤ ቀጣይ ሂደቶችን ለማከናወን አንጻራዊ ሠላም የሚያስፈልግ በመሆኑ ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር የተለያዩ ሥራዎችን እየሠራን ነው ብለዋል፡፡

በትግራይ ክልልን በሚመለከት ኮሚሽነሮች ተደጋጋሚ ጉብኝት የማድረግ እና ከጊዜያዊ አስተዳደሩ ጋር ውይይት መደረጉን ገልጸው፤ በቀጣይም ዞኖችና ወረዳዎች ዝግጅት አድርገው እስከሚጠሩን እየተጠባበቅን ነው ሲሉ ተናግረዋል።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አጀንዳ የማሰባሰብ ሥራው መጠናቀቁን አስታውሰው፤ ከአጀንዳ ማሰባሰቡ የተገኙትን ተሞክሮዎች መነሻ በማድረግ የነበሩት ችግሮች በሌሎች ክልሎች ላይ እንዳይደገሙ ጥረት ይደረጋል ብለዋል፡፡

ምክክሩ ሂደቱ ሁሉንም አካታች ሊሆን እንደሚገባ ገልጸው፤ አንሳተፍም የሚሉ አካላት ምን መሆን እንዳለባቸው ሕዝብ ይወስናል ብለዋል፡፡

በሚቀጥሉት ሦስት ወራት የምክክሩ አጀንዳዎች በተገቢው ሁኔታ ተሰብስበው ወደ ኮሚሽኑ እንዲቀርቡ የማድረግ እና ለጠቅላላ ጉባኤ የሚቀርቡትን አጀንዳዎች የመለየት ሥራ እንደሚከናወን አመላክተዋል፡፡

ለጠቅላላ ጉባኤው የሚሳተፉ አካላት ከሁሉም የኅብረተሰብ ክፍሎች የተውጣጡ መሆን አለባቸው ያሉት ኮሚሽነሩ፤ ምክክሩ በክርክርና በድምፅ ብልጫ የሚወሰን ሳይሆን በመግባባት ሁሉም አሸናፊ የሚሆንበት ነው ሲሉ አስረድተዋል።

በሌላ በኩል የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የሃይማኖት ተቋማት፣ ሴቶች፣ ሲቪክ ማኅበራት፣ አካል ጉዳተኞች እና ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍሎች የሚወክሉ አካላት በትክክል ተወክለው በሀገራዊ ምክክሩ ሊሳተፉ ይገባል ያሉት ፕሮፌሰር መስፍን፤ በዚህ ሂደትም 50 የሚሆኑ ፖለቲካ ፓርቲዎች ከኮሚሽኑ ጋር አብረው ቢሆንም የተወሰኑ ፓርቲዎች እየተሳተፉ አይደለም ብለዋል፡፡

የሚያስቆጡና የማያግባቡ አጀንዳዎችን ወደ ምክክር ማቅረብ ተገቢ በመሆኑ ተሳታፊ ያልሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎችና ታጣቂ ኃይሎች ቀጣይ ባለው የምክክር ሂደት በንቃት እንዲሳተፉ ጥሪ አቅርበዋል።

ከሸገር ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጋር
በመተባበር በየወሩ የሚታተም

# ፍርድ ቤቱ የመሬት ወረራ እና ሙስና ለማስቀረት የጀመረው የፍትሕ መንገድ

**ክፍለዮሐንስ አንበርብር**

የሸገር ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሥራውን ‹‹ሀ›› ብሎ ከጀመረ ወዲህ የበርካቶችን እንባ በማበስ እና እውነተኛ ፍትሕ እንዲሰፍን በማድረግ ትልቅ ሚና በመወጣት ላይ መሆኑ ይታወቃል። በተለይም በሸገር ከተማ አስተዳደር ለሚኖሩ አርሶ አደሮች የዓመታት የፍትሕ ጥማትን ለመቁረጥ ዓይነተኛ ሚና በመጫወት ላይ ይገኛል። በዚህ አካባቢ ፍትሕን ለማስፈን እና ሁሉንም በፍትሐዊነት ለማገልገል የተቋቋመው ይህ ፍርድ ቤት በርካታ አኩሪ ተግባራትን በማከናወን ላይ ይገኛል።

በቁጥር 233/2015 የተመሠረተው የሸገር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለዜጎቹ ፍትሐዊ የሕግ አገልግሎት በመስጠት ፍትሕን እውነተኛ ፍትሕ ለሚሹ ሰዎች ለመመለስ ይሠራል። ፍርድ ቤቱ ከመቋቋሙ በፊት የተለያዩ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች ባሉበት በሸገር ከተማ ሕገ-ወጥነት ተስፋፍቶ ነበር። ይህ ደግሞ በርካቶች ቅር እንዲሰኙ ያደረገ ሲሆን፤ የፍትሕ ሥርዓቱንም የሚፈትን ነበር።

ነገር ግን የሸገር ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከተቋቋመ በኋላ ፍትሕ ለመመለስ በቅድሚያ እና በሙያ የተደገፈ የሕግ አገልግሎት ሲሰጥ ቆይቷል። ሐጋዊ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው እና እንደ ሸገር ከተማ በተደጋጋሚ የሚነሱ ጉዳዮች ከመሬት ጉዳዮች እና ከሙስና ጋር የተያያዙ ናቸው። በዚህ ላይ አርሶ አደር ዘመናትን የተሻገሩ ጥያቄዎችም ነበሩት።

የሸገር ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት አቶ ኩመላ ቡሳ እንደሚሉት፤ በከተማዋ የሚታየው የግጭት እና የወንጀል ዋና መንስዔ ከመሬት ወረራ እና ሙስና ጋር የተያያዘ በመሆኑም ማኅበራዊ ቀውሶችን ያስከተለ ነበር። በዚህም መሠረት ፍትሕን ለእውነተኛ ፍትሕ ፈላጊዎች ለመስጠት እና ከመሬት ጋር የተያያዙ ሙስናዎችን ከሕግ አንፃር በመገምገም ለመፍታት የመሬት እና የሙስና ጉዳዮችን የሚመለከት ፍርድ ቤት ብቻ ተቋቁሟል። እነዚህ ጉዳዮች በሸገር ከተማ የተስፋፉበትን ምክንያት ማየት አስፈላጊ ስለመሆኑ ይናገራሉ።

መሬት እና ሙስና ብቻ የተመለከተ ችሎት የተቋቋመው በተደጋጋሚ ከኅብረተሰቡ ከመሬት ጋር የተያያዙ ችግሮችንና ሙስናዎችን መሠረት አድርጎ ነው። ይህም የተንዛዛ እና ዓመታትን ይወስዱ የነበሩ ቅሬታዎችን በአጭር ጊዜ ለመፍታት እና እርካታን መፍጠር ያስቻለ ነው።

እንደ አቶ ኩመላ ገለፃ፤ የመሬትና የሙስና ወንጀል ችሎት መቋቋሙን ተከትሎ በዚህ ዘርፍ የሚሠሩ የሕግ ባለሙያዎች ሥነ-ምግባር በጥልቀት ተመርምሮ ለሙያቸው ከፍጠኛ ዋጋ የሚሰጠ እና በእውቀትም በጣም የተሻለ ደረጃ ላይ አሉ የተባሉት እንዲሠሩ ተመርጠዋል። የሸገር ከተማ አስተዳደር ከፍተኛ ፍርድ ቤትን በተመለከተ አብዛኛው ጊዜ የሚነሱት ከመሬትና ከመሬት ጋር የተያያዘ ሙስና ነው። በእነዚህ ሂደት ውስጥ ውስጥ የሚሠሩ ጠበቆች ተመርጠው በመሬት ጉዳዮች ላይ ብቻ ትኩረት አድርገው ለሕዝብ እንዲያገለግሉ



**አቶ ኩመላ ቡሳ፤**

የተደረገበት ምቹ ሁኔታም ተፈጥሯል።

በአሁኑ ወቅት የሸገር ከተማ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ለሕግ የበላይነት እና ለፍትሕ የበላይነት በትጋት እየሠራ ነው። እነዚህን በመሬት እና በሙስና ላይ የሚሠሩ ፍርድ ቤቶች ላይ በመመሥረት ሰዎች በመሬት ሙስና ጉዳዮች ላይ ሕጋዊ ውሳኔ እየሰጡ እና የሕግ የበላይነት እንዲከበር በማድረግ ላይ ናቸው። በዚህ ረገድ የተሰጡ የሕግ አገልግሎቶች በተለያዩ አቅጣጫዎች በሕገ ወጥ መንገድ የተወረሩ እና ያለ አግባቡ የተያዙ የወል መሬት ማስረጃዎችን በማሰባሰብ እና በማጣራት ወደ መሬት ባንክ እንዲመለሱ ተደርጓል። በዚህም የበርካቶች የዓመታት ጥያቄ ምላሽ እያገኘ ነው።

እንደ ፕሬዚዳንቱ ማብራሪያ፤ የሸገር ከፍተኛ ፍርድ ቤት መቋቋምን ተከትሎ ከመሬት ጋር በተያያዘ የመሬት ወረራ እና ሙስና እየቀነሰ ነው። ይህም ብቻ ሳይሆን ለከተማው ነዋሪዎች በተለይም በራሳቸው መኖሪያ ቤታቸው ባለቤትነት እያጡ ለነበሩ አርሶ አደሮች እፎይታ የሰጠ ሲሆን በሌላ መንገድ ደግሞ አዲስ ገቢ እየፈጠረ መሆኑ ሌላኛው ጥሩ አጋጣሚ ነው። በእነዚህ ጉዳዮች ላይ በትኩረት በመሠራቱም በሕገ-ወጥ የመሬት ወረራ ምክንያት ንብረታቸውን ተነጥቀው የነበሩ አርሶ አደሮች የባለቤትነት መብታቸው እየተረጋገጠ ነው። በሕጉ መሠረት ሕገ-ወጥ ግንባታን በማፍረስ ፍትሕን ለማስፈን እየተሠራ ነው።

ፍርድ ቤቶች በመሬት ላይ እና በሙስና ላይ የተመሠረተ የሕግ አገልግሎት መስጠት በመጀመራቸው ከነዚህ ጉዳዮች ጋር ተያይዞ የሚፈጠረው ጫና እየቀነሰ መጥቷል የሚሉት አቶ ኩመላ፤ በዚህ ላይ የሚሠሩት የሕግ ባለሙያዎች በእነዚህ ጉዳዮች ላይ በተደጋጋሚ እንዲሠሩ በመደረጉ በጥበብ እና ፍትሕን ለመስጠት እና ለአረዳድ አመቺ የሆነ እይታ ፈጥሯል። ከዚህም በተጨማሪ በቀላሉ ጥፋት ምንድን ነው የሚለውን ለማወቅ ረድቷቸዋል። ፍርድ ቤቱ እንደ ፍርድ ቤት የሕግ አገልግሎቶችን ለማፋጠን የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን ተግባራዊ ለማድረግ ያሳየው ቁርጠኝነት ትልቅ ቦታ የሚሰጠው መሆኑን አቶ ኩመላ አረጋግጠዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## አረንጓዴ ዐሻራ ለወጪ ምርቶች ዕድገት ትልቅ አቅም ሆኗል!

ከ2010ሩ ሀገራዊ ለውጥ ማግስት እንደ መንግሥት በተለይም በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) አነሳሽነት በትኩረት እየተሠሩ ከፍ ያለ ውጤት እየተመዘገበባቸው ካሉ ተግባራት መካከል የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር አንዱ ነው:: ይሄ መርሐ ግብር እንደ ሀገር ብቻ ሳይሆን ዓለምን ከፍ ያለ ዋጋ እያስከፈላት ላለው የአየር ንብረት ለውጥ ችግር መፍትሔ ከመሆን ባለፈ፤ ለኢትዮጵያውያን የበዛ ፋይዳ ያለው ነው::

ምክንያቱም የአየር ንብረት ለውጥ በዓለም አቀፍ ደረጃ ለሚታዩ የድርቅ፣ የጎርፍ፣ የአውሎ ነፋስ፣ ወጀብና ሱናሚ እንዲሁም ሰደድ እሳት እና መሰል አደጋዎች መከሰት መንስኤ ነው:: ኢትዮጵያም የዓለም አንድ አካል እንደመሆኗ የከፋ ድርቅ፣ ጎርፍና ሌሎችም ተያያዥ ችግሮች ደጋግመው ጎብኝተዋታል:: በዚህም ከፍ ያለ ኢኮኖሚያዊም ሰብዓዊም ጉዳትን አስተናግዳለች::

ከዚህ አኳያ የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብሯ ይሄንን ችግር ለማቃለል የሚያስችል አንድ አቅም ሲሆን፤ ከዚህ ባሻገር የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ለምታደርገው ጥረት፣ ለሥራ ዕድል ፈጠራ፤ ለአከባቢ ውበት፣ ለመድኃኒት እና መሰል ጉዳዮች አገልግሎት የሚውሉም ናቸው:: መርሐ ግብሩ ከተጀመረ ወዲህ የሚከናወኑ የችግኝ ተከላ ሂደቶችም እነዚህም ማዕከል አድርገው የሚካሄዱ እና ለሀገር በቀል ዕፅዋትም ትኩረት የሰጡ ናቸው::

በዚህ ረገድ በመቶ ሺዎች ለሚቆጠሩ ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር ተችሏል፤ መድኃኒትነት ያላቸውን ዕፅዋት ማብዛት ተችሏል፤ ለምግብነት የሚውሉ እንዲሆም ለገንዘብ ማግኛ (ለገበያ) የሚውሉ እንደ አትክልትና ፍራፍሬ አይነት ችግኞችን በመትከል ውጤታቸውን ማየት ተችሏል:: በተለይ ለምግብነት የሚውሉ እና ለገበያ የሚሆኑ እንደ አቮካዶ፣ አፕል፣ ፓፓያ፣ ማንጎ እና ቡናን የመሳሰሉት ላይ በሰፊው ተሠርቶባቸዋል፤ ከፍ ያለ ውጤትም አስገኝተዋል::

ለአብነት፣ በአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር አማካኝነት የተተከሉ የአቮካዶ እና ፓፓያ ችግኞች ዛሬ ላይ ለሀገር ውስጥም፣ ለውጪ ገበያም መቅረብ ችለዋል:: በዚህም የሀገር ውስጥ ገበያን ማረጋጋት፤ በወጪ ንግዱም የውጪ ምንዛሪ ማስገኘት ተችሏል:: በቡና በኩልም ቢሆን ከዓመት ዓመት የቡና ችግኞችን በማብዛት በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ የቡና ዛፎችን መትከል ተችሏል::

በተለይ ቡና የሀገሪቱ የወጪ ንግድ የጀርባ አጥንት ሆኖ ከመዝለቁ ጋር በተያያዘ፣ በአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብሩ እየተከናወነ ያለው ተግባር ይሄን አቅምነቱን ከፍ እያደረገው ይገኛል:: ለዚህም ነው ዘንድሮ በቡና የወጪ ንግድ ከወትሮው ከፍ ያለ ቡና በመላክም ሪከርድ የሆነ ገቢ ማግኘትም የተቻለው:: ለዚህ ዐብይ ማሳያ የሚሆነው፤ ከሰሞኑ የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለሥልጣን የሰጠው መግለጫ ነው::

እንደ ባለሥልጣኑ መግለጫ፣ በ2016 በጀት ዓመት 298 ሺህ 500 ቶን ቡና ወደ ውጭ በመላክ አንድ ነጥብ 43 ቢሊዮን ዶላር ገቢ ተገኝቷል:: ይሄም ከአምናው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር የ50 ሺህ ቶን ብልጫ ያለው ሲሆን፤ በዚህ መልኩ እያደገ ከመጣው የቡና ወጪ ገበያ የሚገኘውን ገቢ ለማላቅ፣ እንዲሁም ምርታማነትን በማሳደግ ሌሎች ሀገሮች ከሚያገኙት ገቢ ጋር ለማስተካከል በትኩረት እየሠራ ስለመሆኑም ነው ባለሥልጣኑ ያብራራው::

ይሄን ገለጻ የሚያጠናክረው ደግሞ በአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር ለቡና ችግኝ የተሰጠው ትኩረት ሲሆን፤ ይሄም ከዓመት ዓመት እያደገ በመምጣት ዘንድሮ በመቶ ሚሊዮን የሚቆጠር የቡና ችግኝ ለዚህ መርሐ ግብር ተዘጋጅቶ እየተተከለ ይገኛል:: ይሄ ደግሞ በአንድ በኩል የደን ሽፋንን የማሳደግ እና የሥራ ዕድል የመፍጠር ግብ ያለው ሲሆን፤ በዋናነት ግን ቡና ለሀገር ኢኮኖሚ ያለውን ፋይዳ በመረዳት ጥራትም ብዛትም ያለው ቡና ለዓለም ገበያ በማቅረብ የውጭ ምንዛሪ ግኝትን የሚያሳድግ ነው::

የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብሩ፣ እንደ ሀገር ካሉት ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች መካከል የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ እና የወጪ ንግድ ምርቶችን በመጠንም በዓይነትም ማሳደግ ነው:: በዚህ ረገድ በአትክልትና ፍራፍሬ ላይ የታየው ውጤት ለሀገር ውስጥ የምግብ ፍጆታን መሸፈን የሚቻልበትን አቅም ፈጥሯል:: እንደ አቮካዶ ባሉ ምርቶችም ለኢንዱስትሪዎች ግብዓት ማዋልም፣ ለወጪ ገበያ ማቅረብም ተችሏል:: በቡና እና ሌሎች ለወጪ ንግድ አቅም የሚሆኑ ምርቶችን መጠንና ዓይነትንም ማሳደግ አስችሏል::

ከዚህ አኳያ የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብሩ የውጪ ምንዛሪ ግኝትን ማስገኘት የሚያስችሉ ምርቶችን በብዛትና በዓይነት ከፍ በማድረግ የወጪ ምርቶች ዕድገት አቅም መሆኑን በመገንዘብ፤ በዘንድሮው የችግኝ ተከላ መርሐ ግብር ለእነዚሁ ጉዳዮች ከፍ ያለ ትኩረት ሰጥቶ መከወን ይገባል!


**አዲስ ዘመን**

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል :- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው::በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

## የመመረቂያ ጥናቶች የት ናቸው?

ሚሊዮን ሺበሺ

ወቅቱ የተማሪዎች የምርቃት ወቅት ነው:: ከዋናዎቹ መገናኛ ብዙኃን እስከ ማኅበራዊ ገጾች በምርቃት ምስሎች ተጥለቅልቋል:: የዩኒቨርሲቲዎችና ኮሌጆች አካባቢዎች እና የትራንስፖርት መጠበቂያ ቦታዎች በተመራቂዎችና አስመራቂዎች ደምቀዋል:: መንደሮች በምርቃት ድግስ ደምቀዋል:: ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ደግሞ የመዋዕለ ሕጻናት ምርቃት ድግስ ሌላኛው ፋሽን ሆኗል:: ለዛሬው ግን ትኩረታችን ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚመረቁት ላይ ነው::

በመገናኛ ብዙኃን፣ በማኅበራዊ ገጾችና በየአካባቢው የደመቀው ይህ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች ምርቃት ይህን ያህል ሲደምቅ፤ ዋናው ቁም ነገሩ ግን ተዘንግቷል:: የሠሩት ጥናት የድግሱን ያህል አይደምቅም:: እንኳን የሠሩት ጥናት ይቅርና የተመረቁበት የትምህርት ክፍል ራሱ የምርቃቱን ድግስ ያህል አይታወቅም:: የመጀመሪያ ዲግሪውን እንተወውና ሁለተኛና ሦስተኛ ዲግሪ የሚመረቁት ላይ እናተኩር::

> **ስለምርቃት ስናስብ ስለሚሠሩ ጥናቶችም እናስብ:: የሁለተኛና ሦስተኛ ዲግሪ ጥናቶች ትኩረት ይሰጣቸው:: ጥናቶች ከድግሱ በላይ ይሁኑ!**

የመጀመሪያ ዲግሪ ለተማሪዎች ብርቅ ነው:: ከ15 ዓመታት በላይ በትምህርት የቆዩ ናቸው፤ በዚያ ላይ ልጆች ናቸው:: ለልጆችም ለወላጆችም ከፍተኛ የሆነ መጓጓት አለው:: በተለይ ልጆች ከ15 ዓመታት በላይ ትምህርት ላይ ቆይተው ሀገር የመረከብ ኃላፊነት ሊወስዱ ነው:: ከሥራ ዓለም ጋር ሊገናኙ ነው:: ስለዚህ የመጀመሪያ ዲግሪ ተመራቂዎች የቱንም ያህል ብርቅ ቢሆንባቸው ምንም አይገርምም! እንዲያውም ሊሆንባቸው ይገባል!

ከመጀመሪያ ዲግሪ በላይ ያለው የትምህርት ደረጃ ግን በአንድ ጉዳይ ላይ ልዩ ጥናት የሚደረግበት ነው:: ተማሪውም በአብዛኛው በሥራ ላይ ያለ እና ከሥራው ጋር በተያያዘ የምርምር አቅሙን ለማሳደግ የሚማረው ነው:: በአንድ ልዩ መስክ ላይ ትኩረት አድርጎ አንድ ችግር ፈቺ ምርምር እንዲሠራ ነው:: ምርምር የሚለው ቃል ከበድ ቢል እንኳን፤ ቢያንስ በሆነ ልዩ ዘርፍ ላይ ተጨማሪ ግንዛቤ የሚይዝበት ነው:: በዋናነት ከክፍል ውስጥ ትምህርት በላይ ጥናት ላይ የሚያተኩር ነው::

የምናየው ነገር ግን ከጥናቱ በላይ ትኩረት የሚሰጠው ልብሱ ነው:: በሁለተኛ ዲግሪ (ማስተርስ) የሚመረቁ ሰዎች የመላዕክትና የቅዱሳን ስም እየጠሩ ሲጸልዩና ሲያመሰግኑ ከሱናሚ አደጋ የተረፉ እንጂ ለሁለተኛ ጊዜ የሚመረቁ አይመስሉም:: ማመስገኑ ምንም ችግር አልነበረውም፤ ችግሩ ግን የምስጋናው ትኩረት ዋናው ነጥብ ላይ አለመሆኑ ነው:: «በዚህ ዘርፍ ይህን ጥናት ሠራሁ» ከማለት ይልቅ ልብሱን በመልበሱ መሆኑ ነው:: በነገራችን ላይ እንዲህ የሚያደርጉት በሁለት ምክንያት ነው::

አንደኛው፤ ያንኑም ቢሆን ለማግኘት ካለው አሰልቺና ተስፋ አስቆራጭ ውጣ ውረድ አንፃር ነው:: በአማካሪና በተማሪ መካከል ያለው ግንኙነት የጌታና የባሪያ የሚመስል ኋላቀር ግንኙነት ስለሆነ ነው:: አማካሪዎችን ማግኘት ራሱን የቻለ ጸሎት ስለሆነ ነው:: በስንት ጸሎት ከተገኙ በኋላም በእርጋታና በትሕትና ከማማከር ይልቅ ማመናጨቅና መቆጣት ስለሚቀናቸው ተመራቂው «ከዚህ ጉድ አውጣኝ!» እያለ ፈጣሪውን መማጸኑ አይቀርም:: ጨርሰው ሲመረቁ ከሱናሚ አደጋ የተረፉ የሚያስመስሉበት አንዱና ዋናው ምክንያት ይህ ነው::

ሁለተኛው ምክንያት ግን፤ የሚፈለገው ወረቀቱ እንጂ ጥናቱ ስላልሆነ ነው:: ዲግሪ አለው፣ ማስተርስ አለው፣ ፒ ኤች ዲ አለው... እንጂ «በምን?» የሚለው ትኩረት አይሰጠውም:: አንድ በሥራ ዓለም ላይ ያለ ሰው፤ ከሙያው ጋር የሚገናኝ ምን ጥናት ሠራ ከማለት ይልቅ «ማስተርስ አለው» የሚለው ይቀድማል:: «አለው» የሚለው እንጂ «በምን?» የሚለው ዋና ጉዳይ አይደለም:: ቀላል ምሳሌዎችን እንይ::

ለምሳሌ፤ በአገራችን ልማድ «ዶክተር» የሚለው ቃል በጣም ይካበዳል:: በዚህም ምክንያት «ዶክተር» መባሉን እንጂ «የምን ዶክተር?» የሚለውን ልብ አንለውም:: ገጠር ያሉ ቤተሰቦቻችን ለአካዳሚያዊ ጉዳዮች ሩቅ ናቸው:: የሚያውቋቸው የሙያ ዘርፎች በአካባቢያቸው የሚያውቋቸውን ብቻ ነው:: ለምሳሌ፤ አስተማሪ፣ ሐኪም፣ ዳኛ ዋና ዋናዎቹ ናቸው:: «ዶክተር» ሲባል ለእነርሱ የሕክምና ዶክተር ብቻ ነው:: እነዚህ ሰዎች ለአካዳሚያዊ ጉዳዮች ሩቅ ስለሆኑ እንዲህ ማሰባቸው አይገርምም:: የሚያስገርመው የተማረ የሚባለውም ከእነርሱ ያልተሻለ መሆኑ ነው:: «ዶክተር» የሚል ቃል ሲሰማ ክባድ ይሰጠዋል:: «የምን ዶክተር?» ከማለት ይልቅ የሁሉም ነገር አዋቂ አድርጎ «እሱ እኮ ዶክተር ነው!» ይላል::

አንድ በቆሎ ላይ ልዩ ምርምር (ስፔሻላይዝድ) ያደረገ ሰው አለ እንበል:: ይህን ሰው እንኳን ጠቅላላ ዶክተር «የግብርና ዶክተር» እንኳን ለማለት ይከብዳል:: ምክንያቱም ግብርና ራሱ በውስጡ ብዙ ንዑስ ዘርፎች ያሉት ሰፊ ዘርፍ ስለሆነ:: ይህ ሰው የተዋጣለት የበቆሎ ምርምር ዶክተር ልንለው እንችላለን:: ስለበቆሎ የሚናገረውን ሁሉ ልናምነው እንችላለን:: በቆሎን በተመለከተ መረጃ ሲያስፈልገን መጠየቅ ያለብን ይህን ሰው ነው::

ይህ ሰው ግን አትሌቲክስን በተመለከተ ከአንድ የመጀመሪያ ዲግሪ ካለው ሰው በምንም አይለይም:: የመንገድ ግንባታን በተመለከተ አንድ የመጀመሪያ ዲግሪ ኢንጂነር ይበልጠዋል:: በአገራችን ልማድ ግን «ዶክተር» የሚል ማዕረግ ያለውን ሁሉ የሁሉ ነገር አዋቂ አድርጎ ማየት የተለመደ ነው:: በዚያ ነገር ላይ «አላውቅም» ካለ «እንዴት ዶክተር ሆኖ አያውቅም?» ሊባል ነው ማለት ነው::

ይህ ችግር ማኅበረሰባዊ ልማድ ብቻ ቢሆን ቢያንስ ይሻል ነበር:: ችግሩ ተቋማዊ ባሕሪም እየተላበሰ መሆኑ ነው:: ለአንድ የሙያ ዘርፍ ባለሙያ ሲቀጠር በዚያ ሙያ ላይ ያደረገው ምርምር፣ ያለውን የሥራ ልምድና ቅርበት ከማየት ይልቅ በሌላ ዘርፍ የያዘው ተደራራቢ የትምህርት ደረጃ እንደ ክብደት ይታያል:: «እገሌ ፒ ኤች ዲ» ያለው ነው ከማለት ይልቅ፤ የያዘው ፒ ኤች ዲ ወይም ሁለተኛ ዲግሪ ለዚያ ለሚፈለገው የሥራ መደብ (ሙያ) ምን የሚጨምረው ነገር አለው? በዚያ ሙያ ላይ ምን ጥናት ሠርቷል የሚለው ነው መታየት ያለበት::

ብዙ ጊዜ «እገሌ እኮ ይህን ያህል ዲግሪ አለው!» ሲባል እንሰማለን:: ይህን የተናገረው ሰው ግን «በምን? በምን?» ቢባል «እኔ እንጃ!» ሊል ይችላል፤ ምክንያቱም ዋናው ጉዳይ ቁጥሩ እንጂ በምን ጉዳይ ላይ የሚለው አይደለም ማለት ነው:: «ምን ችግር ፈቱበት?» የሚለውን እንተወውና ቢያንስ ግን በምን ጉዳይ ላይ የሚለው እንኳን መታወቅ ነበረበት::

ሌላኛው ችግር የመመረቂያ ጥናቶች የት እንዳሉ አይታወቅም:: ለሕዝብ ተደራሽ የሚሆኑበት ዘመናዊ የዲጂታል አማራጭ የለም:: በእርግጥ ጥናቶቹም ወረቀቱን ለመያዝ ተብሎ የሚሠሩ ስለሆነ ያን ያህል ተፈላጊ ላይሆኑ ይችላሉ:: ቀደም ሲል እንዳልነው፤ በተማሪው ችግር ብቻ ሳይሆን አማካሪዎች በጸሎት የሚገኙ ናቸው:: ከአሠራር መመሪያ ይልቅ በግል ስሜት የሚጠቀሙና የሚጎዱ ናቸው:: ይህ ሁሉንም እንደማይወክል ግልጽ ነው:: አንዳንድ ተማሪዎች ደግሞ ዋና ዓላማቸው ወረቀቱን ማግኘት ላይ ብቻ ነው:: በእነዚህ ምክንያቶች የሚሠራው ጥናት ለሕዝብ ይፋ ለማድረግ የማያጓጓ ይሆናል ማለት ነው:: ቢሆንም ግን ጥናቶች በዲጂታል አማራጭ በቀላል መንገድ የሚገኙ መሆን አለባቸው:: ለሌሎች ሰዎች የጥናት መነሻ ይሆናሉ::

ስለምርቃት ስናስብ ስለሚሠሩ ጥናቶችም እናስብ:: የሁለተኛና ሦስተኛ ዲግሪ ጥናቶች ትኩረት ይሰጣቸው:: ጥናቶች ከድግሱ በላይ ይሁኑ!

# አዲስ አበባ ከተማ በተጠናቀቀው በጀት ዓመት

- 146 ነጥብ 84 ቢሊዮን ብር ገቢ ተሰብስቧል
- ከ291 ሺህ በላይ ዜጎች ቋሚ የሥራ ዕድል ተፈጥሯል
- ከውጭ ሀገር ቱሪስቶች 59 ነጥብ 73 ቢሊዮን ብር ገቢ ተገኝቷል

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ በተጠናቀቀው የ2016 በጀት ዓመት 146 ነጥብ 84 ቢሊዮን ብር ገቢ መሰብሰቡን፣ ከ291 ሺህ በላይ ዜጎች ቋሚ የሥራ ዕድል መፈጠሩን ከንቲባ አዳነች አቤቤ ገለጹ። ከውጭ ሀገር ቱሪስቶች 59 ነጥብ 73 ቢሊዮን ብር ገቢ መገኘቱንም ተገልጿል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት 3ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 4ኛ መደበኛ ጉባኤውን ትላንት ማካሄድ ጀምሯል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አዳነች አቤቤ የበጀት ዓመቱን አፈጻጸም ባቀረቡበት ወቅት እንደገለጹት፣ በተጠናቀቀው በጀት ዓመት 146 ነጥብ 84 ቢሊዮን ብር ገቢ መሰብሰብ የተቻለ ሲሆን ከ291 ሺህ በላይ ዜጎች ቋሚ የሥራ ዕድል ተፈጥሯል።

በትምህርት ለትውልድ ንቅናቄ በገንዘብ፣ በጉልበትና በዓይነት ከ6 ነጥብ 4 ቢሊዮን ብር በላይ ሀብት ማሰባሰብ መቻሉን በመግለጽ፣ በተማሪዎች ምገባ ከ779 ሺህ በላይ ተማሪዎች በቀን ሁለት ጊዜ እንዲመገቡ መደረጉን ተናግረዋል።

በከተማዋ በሚገኙ 21 የተስፋ ብርሃን የምገባ ማዕከላት በቀን አንድ ጊዜ ምግብ ማግኘት የማይችሉ 35 ሺህ 600 ዜጎች እየተመገቡ እንደሚገኝ ገልጸዋል።

በጤናው ዘርፍ ከ13 ሚሊዮን በላይ ተጠቃሚዎች የተመላላሽ ሕክምና ተሰጥቷል ያሉት ከንቲባዋ፣ ከሁለት ሚሊዮን በላይ የከተማዋ ነዋሪዎች ጤና መድኅን ፕሮግራም ተጠቃሚ ሆነዋል ብለዋል።

በተጠናቀቀው በጀት ዓመት 151 ቢሊዮን ብር ገቢ ለመሰብሰብ ታቅዶ 146 ነጥብ 84 ቢሊዮን ብር መሰብሰብ መቻሉን ጠቅሰው፣ ከባለፈው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር የ44 ነጥብ 16 በመቶ ብልጫ እንዳለው ገልፀዋል።

በመዲናዋ ለሚገኙ ከ291 ሺህ በላይ ለሚሆኑ ዜጎች ቋሚ የሥራ ዕድል መፍጠሩን በመግለጽ፣ የሥራ ዕድል ፈጠራው በአገልግሎት ዘርፉ 49 ነጥብ 3፣ ንግድ 19 ነጥብ 1፣ ማኑፋክቸሪንግ 17 ነጥብ 5፣ ከተማ ግብርና 9 በመቶ፣ እንዲሁም ኮንስትራክሽን 5 በመቶ ድርሻ መያዛቸውን ገልጸዋል፡፡

ከውጭ ሀገር ቱሪስቶች ብቻ 42 ነጥብ 59 ቢሊዮን ብር ገቢ ለማግኘት ታቅዶ 59 ነጥብ 73 ቢሊዮን ብር ማግኘት መቻሉን ጠቅሰው፣ 928 ሺህ የውጭና 9 ነጥብ 1 ሚሊዮን የሀገር ውስጥ ጎብኚዎች ጎብኝተዋል ብለዋል።

በኪነ ጥበብ ዘርፉ የከተማዋን ልማት የሚያፋጥኑ 349 የኪነ ጥበብ ሥራዎችን በማዘጋጀት ለሕዝቡ ተደራሽ መደረጉን ጠቅሰው፣ በአጠቃላይ ከተማዋን የቱሪስት መዳረሻ ለማድረግ የተሠራው ሥራ አበረታች መሆኑን ተናግረዋል።

የወሳኝ ኩነት ምዝገባን ለ364 ሺህ 894 የልደት ምዝገባ ለ38 ሺህ 23 ተገልጋዮች የጋብቻ ምዝገባና ማስረጃ አገልግሎት መሰጠቱን በመግለጽ ለ8 ሺህ 949 ተገልጋዮች የፍቺ ምዝገባና ማስረጃ አገልግሎት መስጠት ተችሏል ብለዋል።

በዓመቱ በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት 77 ሺህ 994 አዳዲስ የንግድ ሥራ ፈቃድ አገልግሎት ተሰጥቷል ያሉት ከንቲባዋ፣ 330 ሺህ 419 የንግድ ሥራ ፈቃድ ዕድሳት አገልግሎት መስጠት መቻሉንም አብራርተዋል።

የዳቦ አቅርቦት በቀን ስድስት ሚሊዮን ዳቦ ማምረት የሚያስችል አቅም መፈጠሩን በመግለጽ በቂ ምርት በተመጣጣኝ ዋጋ ሊያቀርብ የሚችል የንግድ ድርጅት ተቋቁሞ ወደ ሥራ መግባቱን ተናግረዋል።

በከተማዋ ኢንቨስትመንትን ለማሳለጥ በተደረገው እንቅስቃሴ ለ2 ሺህ 619 ባለሀብቶች አዲስ የኢንቨስትመንት ፈቃድ መሰጠቱን ጠቅሰው፣ ለአንድ ሺህ 919 የዕድሳት ፈቃድ መሰጠቱንም ገልጸዋል።

በመንገድ ግንባታ ሽፋንን ለማሳደግ 40 ነጥብ 8 ኪሎ ሜትር አስፋልት፣ 8 ነጥብ 10 የኮብል ስቶን ኪሎ ሜትር፣ 55 ነጥብ 19 ኪሎ ሜትር የጠጠር መንገድ መሠራታቸውን በመግለጽ፣ 20 ሺህ 595 የመንገድ መብራት መስመርና ፖል ጥገና እንዲሁም የመንገድ መብራት አምፖል ቅየራ ሥራ መሠራቱን አስረድተዋል።

በሕዝብ ትራንስፖርት አቅርቦትና ፍላጎት ከማጣጣም አንጻር 67 ተጨማሪ አዳዲስ አውቶብሶች ግዢ መፈጸሙን ጠቅሰው፣ በቀን 12 ሺህ 502 የሕዝብ ትራንስፖርት በማሰማራት በየቀኑ ከ3 ነጥብ 3 ሚሊዮን በላይ ተሳፋሪዎች አገልግሎት ተሰጥቷል ብለዋል።

በኮሪደር ልማት የመንገድ ፕሮጀክቶች የልማት ተነሺዎች 6 ነጥብ 2 ቢሊዮን ብር ካሳ መከፈሉን አውስተው፣ ለልማት ተነሺዎች 33 ነጥብ 4 ሄክታር መሬት ማስተላለፍ መቻሉን ተናግረዋል።

## ደቡብ ሱዳን የትብብር ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ደቡብ ሱዳን የናይል ተፋሰስ የትብብር ማዕቀፍ ስምምነት ማፅደቋም ለኢትዮጵያ ትልቅ የዲፕሎማሲ ርምጃ ነው፡፡

ኢትዮጵያ የናይልን ሀብት በፍትሐና በእኩልነት ለመጠቀም ትልቅ የሕግ ማዕቀፍና የፖለቲካ አካሄድ እንዲሁም የዲፕሎማሲ መስመር አድርጋ ተጠቅማበታለች ብለዋል፡፡ ይሄ ደግሞ በሌሎች ውሃ አመንጪ ሀገራት ተቀባይነት አግኝቶ በእነርሱም ተደግፎ ጥሩ ቅንጅት ተካሂዶ የማዕቀፍ ስምምነቱ ከ14 ዓመታት በፊት መፈረሙን አስታውሰዋል፡፡

ከፈረሙት ሀገራት መካከል አብዛኞቹ የሕግ አካል አድርገው ሰነዱም በአፍሪካ ኅብረት ዘንድ ተመዝግቦ ኮሚሽን እንዲቋቋም ይፈልግ እንደነበር ጠቅሰዋል፡፡ የኢትዮጵያ ጥረትና በዚህ ዙሪያ ያደረገችው ጉዞ ቢዘገይም የተሳካ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

አሁን ላይ ደቡብ ሱዳን ስምምነቱን ማፅደቋ ለኢትዮጵያ ትልቅ የዲፕሎማሲ ስኬት ማረጋገጫ ነው ያሉት ፕሮፌሰር ያዕቆብ፣ ይህ የሁሉም ውጤት መቋጫ በመሆኑ ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ስምምነቱን በፈረሙ በሌሎች ውሃ አመንጪ ሀገራት መካከልም ትልቅ ስኬት መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

የናይል ተፋሰስ የትብብር ማዕቀፍ መስመር የተቃና እንዲሆን ኢትዮጵያ ያደረገችው ጥረት በመንግሥትም ሆነ በምሑራን እንዲሁም በተደራዳሪዎችም ዘንድ በአዎንታዊ የሚታይ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

እንዲህ አይነቱ ስምምነት ኢትዮጵያ ልማቶቿን እንድታስቀጥል እንደሚረዳትና ይህንን ዲፕሎማሲያዊ ስኬት በመጠቀም ሀብቷንና እውቀቷን አቀናጅታ የውሃ ደኅንነቷን አስጠብቃ እንድትቀጥል ይረዳታልም ነው ያሉት፡፡

የናይል ተፋሰስ የትብብር ማዕቀፍ ስምምነት በደቡብ ሱዳን በኩል መፅደቁ ለኢትዮጵያ የስኬት ማመላከቻ ነው በማለት፣ ይህ የጥረት ውጤት ለወደፊት የበለጠ ለመሥራት መሠረት መሆኑንም ነው የገለጹት፡፡ ይህንን ኅብረተሰቡም እንዲገነዘበው ማድረግ እንደሚገባና ተመራማሪዎችና ምሑራንም ይህንን ተቀብለው በቀጣይ የበለጠ ሀገሪቱ እንዲትጠቀም ማገዝ እንዳለባቸው ተናግረዋል፡፡

## ከኢትዮጵያ ባዮና ኢመርጂንግ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ጋር በመተባበር በየ15 ቀን የሚታተም

# መቀንጨርና መፍትሔው

**ሀብቴ ጀቤሳ ደበሳ (ዶ/ር) ፡- ዋና ተመራማሪ**

የሰው ልጅ ከተፈጠረ ጊዜ ጀምሮ የተፈጥሮ ሀብትን ለመጠቀም እና የተሻለ ኑሮ ለመኖር ከጊዜ ወደ ጊዜ ወደ ሥልጣኔ በመረማመድ ላይ ይገኛል። ምንም እንኳ እድገት የማይቆም ቢሆንም፣ ታሪክ የመዘገባቸው ዋና ዋና የሰው ልጅ እድገቶች እስካሁን ሶስት ናቸው። እነሱም፡- የኢንዱስትሪ፣ የአረንጓዴና የሰማያዊው አብዮቶች ናቸው። ይሁን እንጂ አፍሪካ የኢንዱስትሪም ሆነ የአረንጓዴው አብዮት ተቋዳሽ አልሆነችም።

ወደ ሀገራችን ኢትዮጵያ ስንመጣ እስካለፉት አራት አስርት ዓመታት ድረስ ሀገሪቱ እዚህ ግባ የሚባል የኢንዱስትሪ ልማት ስታንቀሳቅስ አልተስተዋለም። ታዲያ በሀገራችን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ጥቂት ኢንዱስትሪዎች ማቆጥቆጥ ጀምረዋል። ባለፉት ዓመታት በተከታታይ ባለ ሁለት አሃዝ እድገት ያስመዘገበችው፣ የኢንዱስትሪዎች ብቅ ብቅ ማለትን ተከትሎ ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም።

ሆኖም ሀገሪቱ ገጠርን ያማከለ የእድገት ፖሊሲ ብታወጣም የእርሻው ክፍለ ኢኮኖሚ በሚፈለገው ልክ በዘመናዊ ቴክኖሎጂና ግብዓት ባለመደገፉ የህብረተሰቡ በቀን ሶስት ጊዜ በልቶ የማደር የዘመናት ጥያቄ ዛሬም አልተመለሰም። በለውጡ መንግሥት በምግብ እህል ራስን ለመቻል እየተደረገ ያለው ጥረት "ይበል" የሚያስብል ቢሆንም፣ ዛሬም በድርቅ... በተለያዩ ተፈጥሯዊና ሰው ሠራሽ ችግሮች ሕዝቡን ከረሃብ መታደግም ሆነ ምርትና ምርታማነትን ማረጋገጥ አልተቻለም።

ከዚህ አኳያ መገንዘብ የሚቻለው በሀገሪቱ የአረንጓዴውም ሆነ የኢንዱስትሪው አብዮት እስካሁን አልተረጋገጡም ማለት ነው። ይህ ደግሞ ማስተዋል ለሚችል ኢትዮጵያዊ ሁሉ የሚያስቆጭ ክስተት ነው።

> **በኢትዮጵያ በመቀንጨር ምክንያት በዓመት 55 ነጥብ 5 ቢሊዮን ብር ወይም 16 ነጥብ 5 በመቶ ዓመታዊ ገቢ ታጣለች**

"ዓለም ላይ የመጡ እድገቶች ለምን አለፉን? ለምን አላደግንም?" ብሎ ከመጠየቅ ይልቅ ለእድገት የመጡ እድሎችን መጠቀም ግድና ተገቢ እንደሆነ መገንዘብ ያሻል።

የዚህ መጣጥፍ ዓላማም ስላለፉን የምርትና እድገት አብዮቶች ራሳችንን እንድንኮንን ሳይሆን፣ ባለፈው በመቆጨት ስህተቶችን አርመንና ለይተን አሁን ዓለም ያለችበትን የምርትና የእድገት አብዮት በመቀላቀል ከትሩፋቱ እንድንቋደስ ነው።

በአጭሩ ሰማያዊው አብዮት ማለት ማናቸውም በውሃ ውስጥ የሚኖሩ በዓይን ከሚታዩት እስከ ደቂቅ ዘ-አካላት ያሉ ሕይወት ያላቸው ፍጡራንን ለሰው ልጅ ምግብነትና ሌሎች ጥቅሞች ማዋልን ያካትታል። ይህ ሲባል በባህር፣ በሃይቆች፣ በወንዞች እና በውቅያኖሶች ሥነ-ምህዳሮች ውስጥ የሚኖሩትን ሕይወት ያላቸው ፍጥረታትን ሁሉ ይጨምራል።

ከእነዚህም ውስጥ 'አልጌ' የሚባሉት ይገኙበታል። አልጌ ለሰው ልጅ ምግብነት መዋል ከጀመረ 3000 ዓመታት እንደተቆጠረ የታሪክ ድርሳናት ያስረዳሉ። በአፍሪካ የቻድ ሕዝብ ስፓሩሊና (Spirulina) የተባለችውን በአልሚ ንጥረ ነገሮች የበለጸገች አልጌ ስለምመገብ መቀንጨርና በምግብ መጎዳት የለም።

በአንጻሩ ግን በሀገራችን አሁን ላይ በጎልማሳ እድሜ ክልል ውስጥ ካሉት 67 በመቶ ያህሉ እንዲሁም በታዳጊ ወይም በህጻንነት እድሜ ክልል ውስጥ ካሉት ደግሞ 38 በመቶ የመቀንጨር ችግር እንዳለባቸው ጥናቶች ያመላክታሉ። መቀንጨር የሚከሰተው ህጻናት ከተጸነሱበት ቀን ጀምሮ እስከ አንድ ሺህ ቀናት ወይም ሁለት ዓመት ድረስ በቂ አልሚ ምግብ ሳያገኙ ሲቀሩ ነው።

መቀንጨር ህጻናትን በእድሜያቸው ሊደርሱበት ከሚችሉት የቁመት መጠን እንዳይደርሱ፣ እንዲቀጭጩ፣ ነግሮችን በቀላሉ መረዳትና መማር እንዳይችሉ ያደርጋቸዋል። በዚህም ምክንያት የመሞት እድላቸውም ከፍተኛ ይሆናል። በሕይወት ቢኖሩም ለተለያዩ በሽታዎች የመጋለጥ እድላቸው መቀንጨር ከሌለባቸው ሰዎች በላይ የከፋ ይሆናል።

በኢትዮጵያ በመቀንጨር ምክንያት በዓመት 55 ነጥብ 5 ቢሊዮን ብር ወይም 16 ነጥብ 5 በመቶ ዓመታዊ ገቢ ታጣለች። ይህንን ችግር ለመቅረፍ የባዮና ኢመርጂንግ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት የብሔራዊ ማይክሮ አልጌ ምርምር ላቦራቶሪ በመገንባት ወደ ሥራ ገብቷል። ኢንስቲቲዩቱ የስፓይሩሊናን ከፍተኛ የአልሚ ይዘት ያላቸው አልጌዎችን ባሕሪ በተረዱ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የተመራማሪዎች ቡድን ጋር በመሆን፣ ከኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር በ2009 ዓ.ም በተገኘ የምርምር ገንዘብ ድጋፍ ዘር የማምረትና የጥራት ቁጥጥር ሥራውን ጀመረ።

የደረቀ ስፓይሩሊና በእንክብል ወይም በተለያየ መልኩ ከምግቦች ጋር በመቀላቀል አንድ እናት ከጸነሰች ጊዜ ጀምሮ ልጁ አንድ ሺህ ቀናት ወይም ሁለት ዓመት እስኪሞላው ድረስ በየቀኑ 2 ግራም ቢመገብ በተመጣጠነ ምግብ እጥረት ከሚደርስ የጤና መታወክ ሊድን እንደሚችል ይታወቃል።

የኢትዮጵያ መንግሥት መቀንጨርና የህጻናት ምግብ እጦትን እ.ኤ.አ በ2030 ከሀገሪቱ ለማጥፋት ግብ አስቀምጧል። ይሁን እንጂ ይህንን ግብ ለማሳካት ግልጽ ስትራቴጂ አልተቀየሰም። ከዚህ አንጻር ኢንስቲትዩቱ የጀመረው የብሔራዊ ማይክሮ አልጌ ምርምር ፕሮጀክት የመፍትሄ ቁልፍ እንደሆነ ታምኖበታል። ነገር ግን ከተቋሙ በተጨማሪ የመንግሥትና የባለሀብቶች ተሳትፎ ካልታከለበት ፕሮጀክቱ ብቻውን በቂ አይደለም።

በዚህ መስክ ባለሀብቶች እንዲገቡበትም መንግሥት በኢንቨስትመንት ሕግ መሠረት የበኩሉን አስተዋጽኦ እንደሚያደርግ በተደጋጋሚ በተለያዩ መድረኮች ላይ አረጋግጧል። ነገር ግን የመሬት እጦት ለእንቨስተሮች ማነቆ ሆኗል። መቀንጨርን ማጥፋት እንዳለ ሆኖ የስፓይሩሊና ምርት ለንግድም አዋጭ እንደሆነ ታውቋል።


ዓለም አቀፍ የስፓይሩሊና ገበያ አሁን ካለበት 485 ሚሊዮን ዶላር በ2030 ወደ 808 ሚሊዮን ዶላር እንደሚደርስ ይጠበቃል። በየዓመቱም በ9 ነጥብ 4 በመቶ በማደግ ላይ ይገኛል። ስፓይሩሊና ከሕጻናት ምግብ ባሻገር ለልዩ ልዩ ግብዓቶች ይውላል። ኢትዮጵያ በስፓየሩሊና የበለጸገችና አመቺ የተፈጥሮ ሀብት ያላት ሀገር በመሆኗ፣ የጊዜ ጉዳይ እንጂ መስፋፋቱ አይቀሬ ነው።

# ወቅታዊ

# “ለውጡ ለሲዳማ ሕዝብ ከፍተኛ ትሩፋት ይዞለት መጥቷል”

- አቶ ደስታ ሌዳሞ

የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ርዕሰ መስተዳድር



ፎቶ፡- ሀዱሽ አብርሃ

ሶሎሞን በየነ

የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት እና ሕዝብ ከለውጡ በፊት ከሌሎች ብሔር፣ ብሔረሰቦች ጋር ተጨፍልቆ ማንነቱ ተደብቆና ራስን በራስ የማስተዳደር መብቱን ተነፍጎ ኖሯል፡፡ ይህ በመሆኑም ሲዳማ ተገቢው ትኩረት ተነፍጎት፣ ሰላምና መረጋጋት እርቆት፣ ልማት ጠምቶት ቆይቷል። ሆኖም ከስድስት ዓመታት በፊት በሀገሪቱ የመጣውን ፖለቲካዊ ለውጥ ተከትሎ ተቀይዶ የተያዘበት ገመድ በመበጠሱ፤ የሲዳማ ሕዝብ የዘመናት ጥያቄው ምላሽ ማግኘት ችሏል፡፡ ዛሬ ላይ እንደሌሎች ክልሎች ሁሉ ራሱን በራሱ የማስተዳደር መብቱ ተከብሮለት፤ የራሱን ምቹ አስተዳደራዊ መዋቅር ዘርግቶ ወደ ልማት ገብቷል፡፡

ሲዳማ ይህን እድል አግኝቶ እንደ ክልል ከተዋቀረ በአጭር ጊዜ ውስጥ በመንገድ፣ በውሃ፣ በግብርና፣ በትምህርት፣ በጤና፣ በኢንቨስትመንት እና በሌሎችም ዘርፎች ስኬታማ የልማት ውጤቶችን እያስመዘገበ እንደሚገኝ ከሰሞኑ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የጋዜጠኞች ቡድን በክልሉ ባደረግነው የመስክ ምልከታ ታዝበናል። እውነት ለመናገር የኢትዮጵያ ብልጽግና ቢዘገይ እንጂ አይቀሬ መሆኑን፤ ሲዳማ እንደ ክልል ከተዋቀረ በጥቂት ዓመታት ውስጥ ያስመዘገባቸው ሁለንተናዊ የልማት ስኬቶች ማሳያ ናቸው።

ከዚህ አኳያ በዋናነት በ2013 ዓ.ም ሲዳማ እንደ ክልል ከተዋቀረ ወዲህ በክልሉ የተመዘገቡ የልማት ስኬቶች እንዴት ተመሩ? ምን ግብ ታሳቢ ተደርጎ ምን ውጤት ተገኘ? በሲዳማ ሰማይ ሥር ሠላም የሰፈነበት ሚስጥሩ ምንድን ነው? የሲዳማ ሕዝብ ራሱን በራሱ ለማስተዳደር የታገለለት አጀንዳ ግቡን መቷል ወይ? ... ወዘተ በሚሉት አጠቃላይ ስለክልሉ ሠላምና መረጋጋት፣ ልማት እንዲሁም ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ዙሪያ ከሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ርዕሰ መስተዳድር አቶ ደስታ ሌዳሞ ጋር አዲስ ዘመን ጋዜጣ ቃለ ምልልስ አድርጎ ተከታዩን አጠናቅሯል፡፡ ሰናይ ንባብ!

**አዲስ ዘመን፡- የሲዳማ ሕዝብ ለረጅም ዘመናት ራሱን በራሱ ለማስተዳደር የታገለበት ዋና ዓላማ ምን ነበር? የታገለለት አጀንዳስ ተሳክቷል ማለት ይቻላል?**

**አቶ ደስታ ፡-** የሲዳማ ሕዝብ ክልል ሆኖ ለመደራጀት ረጅም ጊዜ የፈጀ ትግል አድርጓል። ትግል ያደርግ የነበረውም በሁለት መሠረታዊ ምክንያቶች ነው። የመጀመሪያው ሲዳማ ቀድሞም ራሱን በራሱ የሚያስተዳድርበት መዋቅር፣ ሥርዓትና ልምድ ነበረው። ስለዚህ ይህ መዋቅር ተመልሶለት በሀገሪቱ ፖለቲካ በንቃት የሚሳተፍበት አደረጃጀት ይፈልግ ነበር። ሁለተኛው ደግሞ ክልል ሆኖ መደራጀቱ የሲዳማ ሕዝብ ይበልጥ እንዲታወቅና ማንነቱ እንዲጠበቅ ስለሚረዳው ነው።

ከዚህ አንጻር ቀደም ሲል የደቡብ ክልል ሳይከፋፈል በነበረው አደረጃጀት፤ የሲዳማ ሕዝብ ተደብቆ ነበር። ሕዝቡም በአካባቢው ያለውን ሀብት ራሱ በራሱ ወስኖ ለማልማት፣ ለማስተዳደርና ውሳኔ ለመስጠት ተጽኖ ነበረው። በመሆኑም ሕዝቡ የታገለው ሕግና ደንብ አበጅቶ እንዲሁ ሥርዓት ዘርግቶ እጁ ላይ ያለውን ሀብት ማስተዳደር፣ መወሰንና መጠቀም እንዲችል ነው። እንደሀገር በጋራ ውሳኔ በሚሰጥባቸው ጉዳዮችም ሲዳማ ሚዛናዊ ውክልና ኖሮት የጋራ ውሳኔ ማሳረፍ እንዲችል፤ በኢትዮጵያ ውስጥ ካሉት ሌሎች ብሔር ብሔረሰቦች እኩል ወይም ተገቢ ምልከታና ትኩረት እንዲኖረው ለማስቻል ነው።

በሀገሪቱ የመጣውን ፖለቲካዊ ለውጥ ተከትሎ የሲዳማ ሕዝብ የዘመናት ራስን በራስ የማስተዳደር ፖለቲካዊ ጥያቄ ምላሽ አግኝቷል። ይህንን ተከትሎ የሲዳማ ሕዝብ ለዘመናት ከታገለለት አጀንዳ ቱርፋት እየተቋደሰ ነው። ይህም ሲባል ክልል በመሆኑ በተፈጠረለት ምቹ ሁኔታ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ሲዳማ ጎልቶ እየታየ ነው። በሀገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ሲዳማ ሚዛኑን የጠበቀ የውሳኔ ሰጭነት ሚናና ውክልና አግኝቷል። ከዚህ አንጻር በሚፈለግ ደረጃ ደርሷል የሚል እምነት ባይኖርም ጅማሮው ጥሩ ነው።

ሌላው የሲዳማን ማንነት የሚያንጸባርቁ ባህላዊ እሴቶቹ፣ ቋንቋው ...ወዘተ ይበልጥ የመታወቅ፣ የመልማት እድል አግኝተዋል። ከኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ገጽታ አንጻር ሲታይ ደግሞ፤ ሲዳማ ራሱን በራሱ ማስተዳደር ከጀመረ በኋላ በእጁና በአካባቢው ያሉ ጸጋዎች በአግባቡ ተለይተዋል። ያለውን ጸጋ በከፍተኛ ደረጃ ወደ ኢኮኖሚ ጠቀሜታ ሊቀይር የሚችል ስትራቴጂካዊ እቅድ ተዘጋጅቶ ሕዝብና መንግሥት እጅና ጓንት ሆኖ እየተገበረ ይገኛል። በዚህም የክልሉ ሕዝብ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ መጥቷል።

በድምሩ የሲዳማ ሕዝብ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጥያቄዎቹና ፍላጎቶቹ እየተመለሱለት ነው። በጤና፣ በትምህርት፣ በመንገድ፣ በንጹህ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ... ወዘተ መሠረተ ልማቶች በስፋት እየተጠቀመ ይገኛል። ከዚህ በላይ ተጠቃሚነቱን ለማስፋት መንግሥትና ሕዝብ በቅንጅት እየሠራን ነው። በመሆኑም ከጊዜ ወደ ጊዜ የበለጠ ተጠቃሚነቱ እያደገ እንደሚሄድ ጥርጥር የለውም። ስለዚህ ሲዳማ ክልል ለመሆን፤ በውስጡ አንግቧቸው ሲታገልባቸው የነበሩ አጀንዳዎች ከሞላ ጎደል ተሳክቷል ብሎ መውሰድ ይቻላል። በመሆኑም የሲዳማ ሕዝብ በጣም ደስተኛ ነው።

እንደሀገር ደግሞ “እህትና አጋር ድርጅት” በሚል አንዱ ውሳኔ ሰጪ፤ ሌላው ውሳኔ ተቀባይ የነበረበት ሥርዓትና አስተሳሰብ አክትሞ፤ ዛሬ ላይ መላው ኢትዮጵያውያን የሀገራቸው ባለቤት የሆኑበት ሥርዓት እየተገነባ ነው። እውነተኛ ፌዴራሊዝም ተግባራዊ እየተደረገ ነው። በዚህ ማዕቀፍ የሲዳማ ሕዝብ የዘመናት ራስን በራስ የማስተዳደር ጥያቄው ተመልሶለት፤ ሲዳማ በሁለንተናዊ ሀገራዊ ጉዳዮች ጥሩና ሚዛናዊ ተሳትፎ እያደረገ ይገኛል።

**አዲስ ዘመን፡- ሲዳማ እንደክልል ከመቋቋሙ በፊትና ከተቋቋመ በኋላ የተከናወኑ መሠረተ ልማቶችን እያነጻጸሩ በአጭሩ ቢነግሩን? የሕዝቡን ከፍተኛ የመሠረተ ልማት ፍላጎትና የበጀት እጥረት ለማጣጣም የክልሉ አመራር የተጓዘበትን ጥበብ ለሌሎች ትምህርት እንዲሆን ቢገልጹልን?**

**አቶ ደስታ፡-** ሲዳማ ራሱን በራስ የማስተዳደር የዘመናት ፖለቲካዊ ጥያቄው ተመልሶለታል። ይህ አጀንዳ አሁን ላይ ተቋጭቷል። አሁን ላይ የሲዳማ ሕዝብ የትግል አጀንዳ ልማት ነው። ክልሉም ከተደራጀ በኋላ በትኩረት እየሠራ ያለው ልማት ላይ ነው።

ከዚህ አኳያ የሕዝቡን የልማት ፍላጎት መሠረት በማድረግ ቅድሚያ ጥያቄውን ለመመለስና ለማስደሰት፤ ልክ ክልል ከሆንን በኋላ ከሕዝቡ ጋር ሰፊ የምክክር መድረክ አካሂደናል። በዚህም መሠረት የህብረተሰቡን የልማት ፍላጎት ለመዳሰስ ተሞክሯል። የሕዝቡም አንገብጋቢ የልማት ጥያቄ የነበረው አንደኛ መንገድ ነው። ሕዝቡም “የቅድሚያ ቅድሚያ ሰጥታችሁ መንገድ ሥሩልኝ” ነው ያለው። እውነትም ሲዳማ ክልል ውስጥ የመንገድ መሠረተ ልማት አልነበረም ማለት ይቻላል። በሁለተኛና ሦስተኛ ደረጃ ያነሳው ንጹህ የመጠጥ ውሃ አቅርቦትና የመብራት አገልግሎት ነው። እነዚህ መሠረተ ልማቶች ለማህበረሰቡ ተደራሽ ባለመሆናቸው በውሃ ወለድ በሽታ በተለይ እናቶችና ህፃናት ይጠቃሉ። ሴቶች ረጅም ኪሎ ሜትር አቆራርጠው ውሃ ለመቅዳት ሲሄዱ ለጾታዊ ጥቃት ይጋለጣሉ። እንዲሁም መንገድ ባለመኖሩ ወላድን ወደ ሃኪምቤት የሚያደርስ የአምቡላንስ መሄጃ መንገድ እንኳን የለም ነበር። አርሶ አደሩ ያመረተውን ምርት ለገበያ የሚያቀርበው በጋማ ከብትና በሸክም ነበር።

ስለዚህ እነዚህን አንገብጋቢ የልማት ጥያቄ ለመመለስ የረጅም ጊዜ ወይም 10 ዓመት እቅድ አዘጋጀን። ከዚህ ደግሞ የመካከለኛ ጊዜ ማለትም የአምስት ዓመት እቅድ፤ ከዚያም የአጭር ጊዜ ማለትም የሦስትና የአንድ ዓመት እቅድ ነደፍን። በዚህ እቅድ መሠረት ቢያንስ በአምስት ዓመት ውስጥ የአስፓልት መንገድ ማቅረብ ቢያቅተን ክረምት ከበጋ ዓመቱን ሙሉ ሊያገለግሉ የሚችሉ ደረጃቸውን የጠበቁ የጠጠር መንገዶችን በከፍተኛ ትኩረት ለመሥራትና የንጹህ መጠጥ ውሃ ተደራሽነትን ለማስፋት አቅደን ተነሳን። ሕዝቡም ይህንን እንድናሳካለት ነው ፍላጎቱ። ይህንን አደራ ከሕዝቡ ተቀብለን ፊታችን ወደ ልማት አዞርን።

ነገር ግን ሲዳማ እንደክልል ሲቋቋም ተጨማሪ ወጪዎች መጥተውበታል። ያለችውን ጭማሪ በጀትም አስተዳደራዊ ወጪው ወስዷታል። በመሆኑም ሕዝቡ ያሳየውን የልማት ፍላጎት መልስ ለመስጠት በጀት ማነቆ ሆነ። የሕዝቡን የልማት ጥያቄ ለመመለስ ሀብት ያስፈልጋል። ሀብት ለማሰባሰብ ደግሞ ሲዳማ ክልል ሆኖ ከተዋቀረ በኋላ የዞን መዋቅር ሳይደራጅ ለሦስት ዓመት እንዲቆይ አደረግን። ዞን አደራጅተን ቢሆን ይወጣ የነበረውን ሀብት፤ ሕዝቡ ለጠየቀው ለልማት አጀንዳ አዋልነው።

ለአብነት ሲዳማ ክልል ከሆነ በአራተኛ ዓመቱ በጥናት አስደግፈን ወጪና የሰው ኃይል በሚቆጥብ መልኩ አራት የዞን መስተዳድሮችን ከፍተናል። ዞኖቹን ለማደራጀት የተገደድነው አንዳንድ የፌዴራል ተቋማት ተልዕኳቸውን ለማስፈጸም ከክልል ጀምሮ እስከ ዞንና ወረዳ አደረጃጀት የሚጠይቁ በመሆናቸው እንዲሁም ህብረተሰቡ የዞን ከተሞች ሲመሠረቱ ሊያገኘው ከሚችለው ኢኮኖሚያዊና አስተዳደራዊ ተጠቃሚነት አንፃር ነው። ህብረተሰቡም ይህንን ሲጠይቅ ስለነበረ ነው። ስለዚህ እነዚህን ዞኖች ካደራጀን በኋላ በመጀመሪያው ዓመት ለዞኖቹ “ትንሽ ገንዘብ” ብለን ለሥራ ማስኬጃ የሠጠነው 240 ሚሊዮን ብር ነው። አሁን ደግሞ ለመኪና ግዥ ብቻ 200 ሚሊዮን ብር የክልሉን መንግሥት ጠይቀዋል። ክልሉ ሲቋቋም ጀምሮ ዞኖቹ ቢደራጁ ወጪው ምን ያህል ሊሆን እንደሚችል ልብ ሊባል ይገባል። በትንሹ በአንድ ዓመት ውስጥ ለዞን መዋቅሮች 300 ሚሊዮን ብር ወጪ ቢደረግ፤ በሦስት ዓመት ውስጥ በጥቂቱ እስከ አንድ ቢሊዮን ብር ይወጣ ነበር።

በተመሳሳይ ሲዳማ እንደ ክልል ከተዋቀረ በኋላ ለክልል ቢሮዎች የሚያስፈልገው የሰው ኃይል ምን ያህል እንደሆነ መዋቅር ተሠርቷል። ለአብነት አንድ የዞን ትምህርት መምሪያ ጽዳትና ጥበቃውን ጨምሮ በድምሩ 50 ሠራተኞችን ያቅፋል። ክልል ሲሆን ይህ የዞን ትምህርት መምሪያ ወደ ክልል ቢሮ ሲያድግ፤ በመዋቅሩ መሠረት 280 ሠራተኞች ያስፈልጉታል። ይህ ደግሞ አንድ ቢሮ ላይ ብቻ ከ50 ሠራተኞች ተጨማሪ 230 ሠራተኞች የሚቀጠሩ ከሆነ፤ ሁሉም ቢሮ ላይ የሰው ኃይሉ በተመሳሳይ ሲሰፋ ለሠራተኞች የሚወጣው ደመወዝ እጅግ ከፍተኛ ነው። መዋቅሩ ተግባራዊ ተደርጎ ሠራተኞች ቢቀጠሩ አዲስ ለሚቀጠሩ ሠራተኞች ብቻ በዓመት ከግማሽ ቢሊዮን ብር በላይ ለደመወዝ ይወጣ ነበር። እውነት ለመናገር የተቋማቱን የሰው ኃይል መዋቅር የሚያጠና ኮሚቴ ተቋቁሞ፤ ኮሚቴው ጥናቱን በሦስት ወር ውስጥ አጠናቆ አቅርቦ ነበር። ነገር ግን ወጪ ለመቆጠብ በመዋቅሩ መሠረት የሰው ኃይል ሳይቀጠር፤ ባለው የሰው ኃይል ሥራዎችን ተግቶ በመሥራት በአንድ ዓመት ውስጥ እስከ 300 ሚሊዮን ብር ለደመወዝ ይወጣ የነበረን ወጪ ማዳን ተችሏል።

ታዲያ የበጀት እጥረት እንኳን ቢያጋጥም እነዚህን ወጪዎች በማስቀረት የሕዝቡን የልማት ጥያቄ መመለስ ተችሏል። ለአብነት በአሃዝ ለመግለጽ ያህል ሲዳማ እራሱን ችሎ ክልል ሆኖ ከተቋቋመ ከ2013 ዓ.ም ጀምሮ በሦስት ዓመት ውስጥ የመንገድ ተደራሽነት ባልነበረባቸው አቅጣጫ ጫካ መንጥረን፣ ገደላ ገደሉን ሰንጥቀን፣ ወንዞች ላይ ድልድዮችን ገንብተን አዳዲስ መንገዶችን ሠርተናል። እንዲሁም ለረጅም ጊዜ ሳይጠገኑ ቆይተው ከአገልግሎት ውጭ የሆኑ መንገዶችን እንዳዲስ ገንብተናል። በዚህም ህብረተሰቡ መግቢያ መውጫ አጥቶ ይቸገር በነበረበት አካባቢዎች ላይ የህብረተሰቡን የዘመናት ችግር ያቀለሉ 2 ሺ 170 ኪሎ ሜትር ደረጃውን የጠበቀ የጠጠር መንገድ በክልሉ መንግሥት ተሠርቷል። ከዚህ በተጨማሪ በፌዴራል መንግሥት የሚሠሩ 210 ኪሎ ሜትር የሚሸፍኑ ሦስት የአስፓልት መንገድ ፕሮጀክቶች አሉ። እነዚህ ተደምረው ሲዳማ ውስጥ በአሁኑ ጊዜ የመንገድ ችግር በከፍተኛ ደረጃ ተቀርፏል። ዛሬ ላይ የመንገድ መሠረተ ልማት ጥያቄ በሲዳማ ውስጥ ጥያቄ አይደለም። ሲዳም ክልል ከሆነ በኋላ በሦስትና አራት ዓመት ውስጥ የተሠራው የመንገድ መሠረተ ልማት በ30 ዓመት እንኳን አልተሠራም። ስለዚህ ለውጡ ለሲዳማ ሕዝብ ከፍተኛ ትሩፋት ይዞለት መጥቷል

ወደ ገጽ 8 ዞሯል

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ

# “ለውጡ ለሲዳማ ሕዝብ ከፍተኛ ትሩፋት ...

ከገጽ 7 የዞረ

ማለት ነው። ክልል መሆኑ ደግሞ በዚህ ትኩረት ልማቱን እንዲያከናውን አስችሎታል። ሌላው እንደ ብልጽግና ፓርቲ አንዱ ትኩረት የሚሰጠው የሕዝብ ደስተኝነት ነው። ከዚህ አንጻር ሕዝቡ ቀደም ብሎ ከነበረው ጋር አነጻጽሮ ሲያየው፤ በተሠራው የመንገድ ሥራ በጣም ደስተኛ ነው። ይህንን ደስታውን ባገኘው አጋጣሚ ይገልጽልናል።

ሌላኛው በከፍተኛ ትኩረት ከተሠሩ መሠረተ ልማቶች ውስጥ አንደኛው ንጹህ የመጠጥ ውሃ የማስፋፋትና ተደራሽ የማድረግ ጉዳይ ነው። ከዚህ አኳያ የንጹህ መጠጥ ውሃ አቅርቦትን ከማሳደግ አንጻር ብዙ ተዋናዮች አሉ። እነዚህን አካላት በማቀናጀትና በማስተባበር ቅድሚያ ችግሩ በጥልቀት የሚስተዋልባቸው ቦታዎች ላይ የውሃ ፕሮጀክቶች በስፋት ተሠርተዋል። ከጥቃቅኖቹ ውጭ በከፍተኛ መጠን የህብረተሰቡን የንጹህ መጠጥ ውሃ ጥያቄ የሚመልሱ 38 አንኳር የንጹህ መጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች ዘንድሮን ጨምሮ በአራት ዓመት ውስጥ ተከናውነዋል። እነዚህ የውሃ ፕሮጀክቶች ወጪያቸው በጣም ከፍተኛ ነው። እያንዳንዳቸው ከ376 እስከ 25 ሚሊዮን ብር ድረስ ዋጋ ያላቸው ናቸው። ከ38ቱ ውስጥ 28ቱ ተጠናቀው አገልግሎት እየሰጡ ነው። ወደ ሚቀጥለው ዓመት ግንባታቸው የሚዞረው 10 ፕሮጀክት ብቻ ናቸው። በድምሩ የ38ቱ ፕሮጀክቶች የግንባታ ውል ሁለት ቢሊዮን ብር ነው። ከዚህ ውስጥ አንድ ነጥብ ሦስት ቢሊዮን ብር ግንባታውን ለሚያከናውኑ ተቋራጮች ተከፍሏል። ቀሪው ክፍያ ፕሮጀክቶቹ ሙሉ ለሙሉ እስኪጠናቀቁ ድረስ ይፈጸማል።

ስለዚህ በተመሳሳይ ክልሉ ከተመሠረተ በኋላ ዘንድሮን ጨምሮ በአራት ዓመት ውስጥ ከንጹህ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት አንጻርም አመርቂ (አኩሪ) ውጤት ተገኝቷል። ሲዳማ እንደክልል ሲቋቋም የንጹህ መጠጥ ውሃ ሽፋኑ 38 በመቶ ነበር። ይህም ለ40 ዓመት ተሠርቶ የተገኘ ውጤት ነበር። ሆኖም ከክልል ምስረታ በኋላ በተሠራው ሥራ አሁን ላይ የንጹህ መጠጥ ውሃ ሽፋኑን ወደ 60 በመቶ ማድረስ ተችሏል። በአጭር ጊዜ ውስጥ ሽፋኑን በእጥፍ ማሳደግ ተችሏል። በተጨማሪም በግንባታ ላይ ያሉት ፕሮጀክቶች ሲጠናቀቁ እንዲሁም በቀጣይ ለመሥራት በዕቅድ የተያዙት ፕሮጀክቶች ወደ ትግበራ ሲገቡ፤ በክልሉ የንጹህ ውሃ መጠጥ ሽፋን 75 እና 80 በመቶ ይደርሳል።

እንዲሁ የህብረተሰቡን አንገብጋቢ የልማት ጥያቄ የሆነውን የመብራት አገልግሎት ተደራሽ ለማድረግ ያላሰለሰ ጥረት እየተደረገ ነው። ይሁን እንጂ የኤሌክትሪክ አገልግሎት ጥያቄ በክልሉ አቅም ብቻ የሚፈታና የሚወሰን አይደለም። ይህንን አገልግሎት የሚያቀርቡ ተቋማት አደረጃጀታቸውና ተጠሪነታቸው ለፌዴራል መንግሥት ነው። የህብረተሰቡ አሰፋፈርም የተበታተነ ስለሆነ በየመንደሩ የመብራት አገልግሎት ተደራሽ ማድረግ ከባድ ነው። ሆኖም በተቻለ መጠን በአካባቢው ካሉት የፌዴራል ተቋማት ጋር በመቀናጀት፤ ክልሉም ተጨማሪ በጀት በመመደብ የህብረተሰቡን የመብራት ጥያቄ ለመመለስ ጥረት እያደረግን ነው።

ሕዝቡ በ4ኛና በ5ኛ ደረጃ ያነሳቸው የልማት ጥያቄዎች ትምህርትና ጤና ናቸው። “ለምን እነዚህ የልማት ጥያቄዎች ወደ 4ኛና 5ኛ ደረጃ ሄዱ?” የሚል ጥያቄ ከተነሳ በኢህአዴግም ሆነ ከዛ በፊት የትምህርት ጥራትና የጤና አገልግሎት ጥራት ላይ እንጂ ሽፋንና ተደራሽነት ላይ የጎላ ችግር ስላልነበረ፤ ሕዝቡ የትምህርትና የጤና መሠረተ ልማት ጥያቄዎችን ወደ ኋላ አስቀምጧቸዋል። ነገር ግን ክልሉ እንደክልል ከተቋቋመ በኋላ በትምህርትና ጤናው ዘርፍ በተመሳሳይ በትኩረት እየተሠራ ነው።

ለአብነት በጤናው ዘርፍ በሽታን ቀድሞ ከመከላከል አኳያ ግንዛቤ ከመፍጠር ባሻገር በፓኬጅ ደረጃ ተቀርጾ በተናጠል እንዲሁም በቤተሰብ ወይም በጎረቤት ደረጃ በቡድን በሽታን ቀድሞ የመከላከል ተግባራት በጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም በትኩረት እየተመራ ነው። በአንጻሩ በሽታው ገፍቶ ሲመጣ ደግሞ አክሞ ማዳን ያስፈልጋል። ከዚህ አኳያ የሕክምና አገልግሎት የሚሰጡ 138 ጤና ጣቢያዎች ቀደም ብሎ የተገነቡ አሉ። ክልል ከተሆነ በኋላ ደግሞ



አገልግሎቱ ተደራሽ ያልሆነባቸው አካባቢዎች ላይ 15 ጤና ተቋማት ገንብተናል። ከነዚህ ውስጥ ስምንቱ ተጠናቀው አገልግሎት እየሰጡ ሲሆን፤ ሰባቱ በግንባታ ሂደት ላይ ይገኛሉ።

ከዚህ በተጨማሪ ዳዬ ሆስፒታል በዙሪያው ላሉ የጤና ተቋማት እንደሪፈራል አገልግሎት መስጫ ሆኖ እንዲያገለግል፤ ግብዓት በማሟላትና የማስፋፊያ ግንባታ በማከናወን ሆስፒታሉን ወደ ጠቅላላ ሆስፒታልነት በማሳደግ የአገልግሎት ደረጃውን ከፍ ማድረግ ተችሏል። እንዲሁም ሆስፒታል ባልተዳረሰባቸው ወረዳዎች አማካኝ ቦታ ላይ ክላስተር ሆነው እንዲያገለግሉ ሦስት አዳዲስ ሆስፒታሎች ተገንብተዋል። እነዚህ ሁሉ የጤና ተቋማት ተዳምረው የጤና አገልግሎት ሽፋኑ ተደራሽ ሆኗል ብሎ መናገር ይቻላል። በቀጣይ የጤና አገልግሎት አሰጣጡን ከማንዋል አሠራር አላቆ ወደ ዲጂታል በመቀየር እጅግ ዘመናዊ የጤና ሥርዓት ለመዘርጋትና ጥራት ያለው አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ እየተሠራ ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ የመድኃኒት አቅርቦት ችግርን ለመቅረፍ ሁለት መሠረታዊ ሥራዎች ተሠርተዋል። አንደኛው የመድኃኒት እጥረቱን ለመቅረፍ ክልሉ በየዓመቱ 30 ሚሊዮን ብር ለመድኃኒት ግዥ ፈንድ ያደርጋል። በዚህም ዘንድሮን ጨምሮ ወደ 110 ሚሊዮን ብር ለመድኃኒት ግዥ ወጪ ተደርጓል። በዚህም በጤና ተቋማት ከጊዜ ወደ ጊዜ የመድኃኒት አቅርቦት ችግር እየተፈታ ነው። ሁለተኛው ደግሞ የጤና ተቋማት የበጀት እጥረት ሲገጥማቸው ለመድኃኒት ግዥ የተመደበውን ገንዘብ በሌላ ሥራ ላይ ያውሉታል። በጀቱ ከታለመለት ዓላማ ውጭ እንዳይውል ለመቆጣጠር እንዲሁም መድኃኒትና የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎችን የማቅረብ አቅምን ከፍ ለማድረግ ከሆስፒታሎችና ከጤና ጣቢያዎች በጥቅሉ ከጤና ተቋማት ባለፈ መድኃኒት አቅራቢ የሕዝብ መድኃኒት ቤቶችን እያደራጀን ነው። እስካሁንም ከ36 የገጠር አስተዳደር ወረዳዎች ውስጥ በ15ቱ የወረዳ ማዕከላት ላይ የሕዝብ መድኃኒት ቤት ተደራጅቷል። መድኃኒት ቤቶቹ በተመጣጣኝ ዋጋ የመድኃኒት አቅርቦት አገልግሎት ከመስጠት ባሻገር ትርፍ እያስገኙ ነው። በዚህም የመድኃኒት ዋጋን ነጋዴው እንደፈለገ የማይዘውርበትና የማይበዘብዝበት፤ በአንጻሩ ደግሞ ሕዝቡ በተመጣጣኝ ዋጋ በቅርበት መድኃኒት የሚያገኝበት ሥርዓት በጤና ተቋማት ውስጥና ውጭ የመዘርጋት ሥራ እየሠራን ነው። አስተማማኝ የመድኃኒት አቅርቦት እንዲኖር የሚያስችል ሥራ ተሠርቷል ብሎ መናገር ይቻላል።

ከትምህርት ሽፋን አኳያ ደግሞ ሁሉም ቀበሌ ላይ ትምህርት ቤት አለ። ነገር ግን ከፍተኛ የትምህርት ጥራት ጉድለት አለ። ጥራቱ የተጓደለበት የራሱ በርካታ ምክንያቶች አሉት። ይሄንን በጥናት የመለየት ሥራ ተሠርቷል። ከምክንያቶቹ አንዱ፤ ከክልሉ የሕዝብ ቁጥር 80 በመቶ የሚሆነው የገጠሩ ማኅበረሰብ ልጆቹ ወደ ትምህርት ቤት የሚሄዱት ቅድመ ዝግጅት ሳያደርጉ ማለትም ፊደል ሳይለዩ፣ ማስላት፣ ማንበብ፣ መጻፍ ሳይለማመዱ ነው። ቅድመ ዝግጅት ሳያደርጉ ቀጥታ ጥሬ እንደሆኑ 1ኛ ክፍል ሲገቡ ደግሞ፤ ሥርዓተ ትምህርቱ የሚያዘው "አንብቡ፣ አስሉ፣ ጻፉ" ብሎ ነው። በዚህ ምክንያት ይቸገራሉ። ውጤታማ አይሆኑም። ይህንን ችግር በመሠረታዊነት ለመቅረፍ “በገጠሩ የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ማስፋፋት የትምህርት ጥራትን ለመጠበቅና ለማስጠበቅ አንደኛው መፍትሔ ነው” በሚል እንደ ክልል በትኩረት እየተሠራ ነው። በዚህም ከክልልነት በኋላ 100 ቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤቶችን በመገንባት በመቶ ቀበሌዎች ተደራሽ ማድረግ ተችሏል። የተገነቡ ትምህርት ቤቶች ደረጃቸውን የጠበቁ ሲሆኑ፤ እያንዳንዱ ትምህርት ቤቶች ስድስትና ሰባት ሚሊዮን ብር ወጪ ተደርጎባቸዋል። በክልሉ 500 ቀበሌዎች ያሉ ሲሆን፤ በሚቀጥሉት ጊዜያት በሁሉም ቀበሌዎች ላይ የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤቶችን ደረጃቸውን በጠበቀ መልኩ ተደራሽ እናደርጋለን።

ከዚህ በተጨማሪ የቅድመ መደበኛ መምህራንን በስፋት እያሠለጠንን ነው። የሠለጠኑ ቅድመ መደበኛ መምህራን አመችና ደረጃውን በጠበቀ ቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ሲገናኙ፤ ብዙ በገጠር አካባቢ የተወለዱና የሚወለዱ ልጆች ልክ በከተማ እንደሚወለዱ ልጆች እኩል ትምህርት ቀስመው የሚያድጉበት ዕድል ያገኛሉ። ይህም የትምህርት ጥራት ላይ የራሱ አስተዋፅዖ ይኖረዋል።

ከዚህ ባሻገር የትምህርት ጥራቱን ለማስጠበቅና የትምህርት ቤቶችን ደረጃ ለማሻሻል በርካታ ፓኬጆች ተነድፈው ወደ መሬት ወርደዋል። በዚህም በሕዝብ ተሳትፎ ትምህርት ቤቶችን የማደስና ደረጃቸውን የማሻሻል፣ አዳሪ ትምህርት ቤቶችን የመገንባት፣ የመምህራንን ተነሳሽነት የማሳደግና የሙያ ብቃታቸውን በሥልጠና የማጎልበት እንዲሁም ተማሪዎች ለትምህርታቸው ትኩረት እንዲሰጡ የሥነ-ልቦና ምክር አገልግሎት መስጠት ... ወዘተ የመሳሰሉ የትምህርት ጥራት ጉድለቱን ሊሞሉ የሚችል ሥራዎች በትኩረት እየተሠሩ ይገኛል። በጥቅሉ ክልል ከተሆነ በኋላ የመጣውን ልማት ስንመዝነው፤ ሕዝቡ ለዘመናት ሲታገልለት የነበረው አጀንዳ በደንብ ተሳክቷል ማለት ይቻላል። ይህም የለውጡ መንግሥት ትሩፋት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የአርሶ አደሩን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ እንዲሁም የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል የተከናወኑ ተግባራትን ቢነግሩን?**

**አቶ ደስታ፡-** ሲዳማ እንደ ክልል ከተመሠረተ በኋላ የጋራ ብልጽግናን ሊያረጋግጡ የሚችሉ መሠረተ ልማቶች ላይ ተጨባጭ ለውጥ መጥቷል። በዚህ ፍጥነት ከቀጠልን በአጠረ ጊዜ ብልጽግናን ማረጋገጥ፤ ሲዳማን ማበልጸግ ይቻላል። ነገር ግን የእያንዳንዱ ሕይወትና ጎጆ ምን ይመስላል የሚለውን ወረድ ብለን ስንገመግም፤ ኑሮው ተቀይሮ የተሻለ በልቶ፣ ለብሶ፣ መኖሪያውን አዘምኖ፣ ልጆቹን በጥሩ ሁኔታ የሚያስተምርበት አቅም ፈጥሮ አላገኘነውም።

ኑሮው ለምን እንዳልተሻሻለ ኮሚቴ ተቋቁሞ ወደ ጥናት ሲገባ፤ 80 በመቶ የክልሉ ሕዝብ የሚኖረው በገጠር ነው። ይህ ሰፊ ሕዝብ የኑሮ መሠረቱ ደግሞ ግብርና ነው። አርሶ አደሩ ያለው የመሬት ስሪቱ ምን ይመስላል የሚለውን ኮሚቴው ሲያጠና፤ ከጠቅላላ የክልሉ ሕዝብ 27 በመቶ የሚሆነው አርሶ አደር 0 ነጥብ 25 ወይም ሩብ ሄክታር መሬት ነው ያለው። እንዲሁም 0 ነጥብ 5 ወይም የሄክታር ግማሽና ከዛ በታች ያለው በድምሩ 49 በመቶ ሕዝብ ከግማሽ ሄክታር በታች ነው መሬት ያለው። በዚች ስንዝር መሬት ላይ ደግሞ ቤት ሠርቶበት፣ የመውጫ መግቢያ ሥፍራ አስቀርቶ... ወዘተ ለግብርና ሥራ የሚተርፈው መሬት እዚህ ግባ የሚባል አይደለም። ስለዚህ እያንዳንዱ አርሶ አደር ያለው የመሬት ሥሪት ጠባብ ነው። አርሶ አደሩ በዚህ የመሬት ሥሪት ላይ በቆሎ፣ ስንዴ፣ ቡና ... ወዘተ ለማምረት እየሠራ ውሎ ቢያደር ትርጉም ያለው ምርትና ሀብት ሊያፈራ አይችልም።

ስለዚህ በእርሻ ላይ የሚሠራው ሥራ በትኩረት ይሠራል። ነገር ግን ካለው የመሬት ጥበት አኳያ በእርሻ ብቻ የአርሶ አደሩ ሕይወት አይለወጥም። በመሆኑም በትንሽ ቦታ የህብረተሰቡን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት የሚያረጋግጡ፤ ሰፋፊ መሬት የማይጠይቁ የአመራረት ዘይቤ ውስጥ እንግባ ብለን ዘርፎችን ለይተናል። ከዚህ አንጻር የሲዳማ ሕዝብ ካለበት የመሬት ጥበት አኳያ ለምርትና ምርታማነቱ ፍቱን መድሃኒት አንደኛው የእንስሳት ሀብት ልማት ነው። በ2014 ዓ.ም የእንስሳት ሀብት ልማት ሥራው የሚመራበት ልዩ ስትራቴጂ በመንደፍ፤ አደረጃጀቱን አጠናክረን፣ ብቁ የሆኑ አመራር መደብን፤ በስፋት ሙያተኞችን ቀጥረን፣ በጀት መድበን፣ ግብዓት አሟልተን እንዲሁም ስትራቴጂውን ለማህበረሰቡ ካስገነዘብን በኋላ ፊሽካ ነፍተን በቅንጅት ስትራቴጂውን ወደ መተግበር ገባን።

የመጀመሪያው ርምጃ ቀደም ሲል የተጀመረ ቢሆንም ቁጥራቸው ያልበዙ፤ ነገር ግን ምርታማነታቸው ከፍተኛ የሆኑ የተሻሻሉ የላሞች ዝርያ የማባዛት ሥራ በስፋት ተሠርቷል። በዚህም አሁን ላይ በእያንዳንዱ በአርሶ አደር ቤት ሀገር በቀል ላሞች ቁጥራቸው እየተመናመነ፤ በአንጻሩ ዝርያቸው የተሻሻሉ ላሞች ደግሞ እየተስፋፉ መጥተዋል። በሂደት ሙሉ ለሙሉ በሚባል ደረጃ ዝርያ የማሻሻል ሥራ ተጠናክሮ ይቀጥላል።

ዝርያቸው የተሻሻሉ ላሞችን ከሀገር በቀል ላሞች ጋር በማዳቀል ዝርያቸውን በማሻሻል አንጻራዊ የወተት ምርት የማሳደግ ተልዕኮ ይዘን ሠርተናል። በዚህም አርሶ አደሩ ከሀገር በቀል/ ሀገረሰብ ላሞች ከሁለት ሊትር በታች ወተት ያገኝ ከነበረበት፤ ዝርያቸው በተሻሻሉ ላሞች አራትና አምስት ሊትር ወደሚያገኝበት ተሸጋግሯል። በክልሉ ከፍተኛ የወተት ምርት ዕድገት ታይቷል። አስተማማኝ የገበያ እድልም አለ። ከዚህ በላይ ምርት ለማግኘት አሁንም ቀሪ የቤት ሥራዎች በትኩረት ይሠራሉ።

እንዲሁም እያንዳንዱ ቤተሰብ በትንሽ ቦታ በዶሮ ርባታ ልማት ላይ እንዲሠማራ አድርገናል። በኋላም ይህ አጀንዳ እንደሀገር “የሌማት ቱርፋት” በሚል ሲመጣ፤ በሀገር አቀፍ ደረጃ በተቀመጠው አቅጣጫ መሠረት በተደራጀ ሁኔታ እየሠራንበት እንገኛለን። በመሆኑም የማር፣ የዓሳ፣ የሀር ምርት ... ወዘተ ሰፋፊ ቦታዎችን የማይፈልጉ ልማቶች በስፋት እየተከናወኑ ነው። ክልሉም የዶሮና የእንስሳት ዝርያ በማሻሻል፤ እንደማህበረሰብ እና ቤተሰብ “በሌማት ቱሩፋት” ፕሮጀክት ተጠቃሚነትና ምርታማነት አንጿር በሀገር አቀፍ ደረጃ ተምሳሌት ለመሆን በቅቷል። የተማሩ ወጣቶች ጭምር በዘርፉ የሥራ ዕድል እየተፈጠረላቸው ነው። በመሆኑም ዛሬ ላይ የመሬት ጥበትና ስፋት ለምርትና ምርታማነት ተጽኖ የማይፈጥርበት ሁኔታ ተፈጥሯል። የመሬት ጥበት አጀንዳ ወደማይሆንበት የአስተሳሰብ ደረጃ ተደርሷል። የመሬት ጥበት ማነቆን በዚህ ደረጃ ተሻግረናል። የእያንዳንዱን ቤተሰብ ገቢ የማሳደግ ሥራ ተጠናክሮ ይቀጥላል።

በአጠቃላይ ሲዳማ የመሬት ስሪቱ ጠባብ ቢሆንም ምርታማነቱ ከፍተኛ ነው። ስለዚህ እርሻን በሚመለከት ዘመናዊ ቴክኖሎጂና የኤክስቴንሽን ግብዓቶችን ተጠቅሞ ከትንሽ መሬት ከፍተኛ ምርት በሚገኝበት አግባብ ላይ በትኩረት እየተሠራ ይገኛል። ይህም በምግብ ዋስትና እራስን ከመቻል አልፎ ገበያን በማረጋጋት፣ የውጭ ምንዛሪ ገቢ በማስገኘት ግብርናው ከፍተኛ ሚና እየተጫወተ ይገኛል። ለአብነት ክልሉ ከ30 ሺ ቶን በላይ ቡና በዓመት ለውጭ ገበያ በማቅረብ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ገቢ ያስገኛል። በአሁኑ ጊዜ የቡና ምርታማነት በአማካኝ 10 ኩንታል በሄክታር ሲሆን፤ እንደ ሀገርም ከፍተኛው 20 እና 21 ኩንታል በሄክታር ምርታማነት እየተመዘገበ ያለው በክልሉ ነው።

እንዲሁም ለይርጋዓለም የግብርና ምርት ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ ፓርክ እና በሀዋሳ ከተማ ዙሪያ ለሚገኙ ሁለት የአቮካዶ ዘይት ጨምቀው ለውጭ ገበያ ለሚያቀርቡ ፋብሪካዎች፤ አርሶ አደሩ የአቮካዶ ፍራፍሬ ምርት በማቅረብ በተመሳሳይ ለሀገር የውጭ ምንዛሪ ገቢያ ያስገኛል። በሌላ በኩል ከሰብል ልማት አኳያ ደግሞ በዘንድሮው የበልግ ወቅት ከ65 ሺ በላይ ሄክታር መሬት በበቆሎ ሰብል ብቻ ተሸፍኗል። ሙሉ የኤክስቴንሽን ፓኳጆችን ተጠቅሞ የበቆሎ ምርታማነትን ለማሳደግ እየተሠራ ሲሆን፤ በአማካኝ 50 ኩንታል በሄክታር ይገኛል ተብሎ ይጠበቃል። ስለዚህ ከግብርና አኳያ በእርሻምና በእንስሳት ሀብት ልማት በትኩረት እየተሠራበት ነው።

ወደ ገጽ 14 ዞሯል

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

## የቡልቡላ አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርክ- በባለሀብቶቹ እይታ

አንተነህ ቸሬ



የኢትዮጵያን መዋቅራዊ የምጣኔ ሀብት ሽግግር እውን ለማድረግ አስተዋፅዖ ይኖራቸዋል ተብለው ትኩረት ከተሰጣቸው ተግባራት መካከል የኢንዱስትሪ ፓርኮች (Industrial Parks) ልማት አንዱ ነው:: የኢንዱስትሪ ፓርኮች የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት የመሳብ፣ የሥራ እድል ፈጠራን የማስፋት እና የቴክኖሎጂ ሽግግርን እውን የማድረግ ዋና ዋና መሠረታዊ ተልዕኮዎች አሏቸው:: ፓርኮቹ በሚገነቡባቸው አካባቢዎች ለሚኖረው የኅብረተሰብ ክፍል ሥራ በመፍጠርና ከአካባቢ ጋር ተስማሚ የሆነ የሥራ ከባቢ እውን በማድረግ ለሀገራዊ የምጣኔ ሀብት እድገት ትልቅ አስተዋፅኦ ይኖራቸዋል::

የኢንዱስትሪ ፓርኮችን ተመራጭ ከሚያደርጓቸው ነገሮች መካከል በርካታ አገልግሎቶችን አንድ ሥፍራ ላይ ሰብሰብ አድርገው የሚያቀርቡ መሆናቸው፣ ተገቢ መሠረተ ልማት የሚገነባላቸው እንዲሁም ከሌሎች አምራቾች ጋርም የሚያገናኙ መሆናቸው ይጠቀሳሉ:: ከዚህ አንፃር በኢትዮጵያም ብዙ የኢንዱስትሪ ፓርኮችን በማቋቋም እንዲሁም በአንፃራዊነት ዝቅተኛ ዋጋ የሚከፈልባቸውን የሰውና የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦትን፣ ማሽኖችን ከቀረጥ ነፃ ማስገባትን፣ የብድር አቅርቦትን፣ የአንድ ማዕከል አገልግሎትን እና የመሠረተ ልማት ግንባታዎችን እንደማበረታቻ በማቅረብ ትልልቅ ዓለም አቀፍ ኩባንያዎች ፋብሪካዎቻቸውን ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲከፍቱ ጥረቶች ተደርገዋል::

በእርግጥም ኢትዮጵያ የአፍሪካ የማምረቻ መናኸሪያ (Manufacturing Hub) እንድትሆን የሚደረገውን ጥረት ለማቀላጠፍ እንዲሁም ሥራ አጥነትን ለመቀነስ ላቅ ያለ ሚና ይጫወታል ተብሎ የተጣለበት የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ውጤቶች ተገኝተውበታል:: በተለይም ኢንዱስትሪ ፓርኮቹ ለበርካታ ዜጎች የሥራ እድሎችን በመፍጠር ቀላል የማይባል አስተዋፅኦ አበርክተዋል:: በአሁኑ ወቅት በመላ ሀገሪቱ 13 የኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚገኙ ሲሆን በሥራ እድል ፈጠራ፣ በውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትና በቴክኖሎጂ ሽግግር ለሀገራዊ ምጣኔ ሀብት እድገት ቀላል የማይባል አስተዋፅኦ እያበረከቱ ይገኛሉ::

በተለይም የግብርና ውጤቶችን እሴት በመጨመር በብዛትና በጥራት ተወዳዳሪ የማድረግ አቅም እንዳላቸው የታመነባቸው የተቀናጁ የግብርና ምርቶች ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ ፓርኮች (Integrated Agro-Industry Parks)፣ የግብርናውን ዘርፍ በማዘመን መዋቅራዊ የምጣኔ ሀብት ሽግግርን ያሳካሉ ከተባሉ የኢንዱስትሪ ፓርክ ዘርፎች መካከል በቀዳሚነት ይጠቀሳሉ:: እነዚህ የአግሮ-ኢንዱስትሪ ፓርኮች ለአርሶ አደሮች ከፍተኛ ፋይዳ እንዳላቸው ይታመናል፤ በተለይ የግብይት ሰንሰለቱን በማቅለል ተጠቃሚ የሚያደርጋቸውን የገበያ ትስስር እንደሚፈጥሩም የሚጠበቅ ነው::

ባለሀብቶችም የግብርና ግብዓቶችን ከአርሶ አደሮች እንዲቀበሉ በማድረግ አርሶ አደሮች የልፋታቸውን ያህል እንዲጠቀሙ አወንታዊ አስተዋፅኦ ያበረክታሉ:: መንግሥት በሀገሪቱ ሶስት የአግሮ-ኢንዱስትሪ ፓርኮችን ገንብቶ ወደ ሥራ ማስገባቱ ይታወቃል:: ለግንባታቸውም እስካሁን ድረስ ከ30 ቢሊዮን ብር በላይ ወጪ ማድረጉንም መረጃዎች ያመለክታሉ:: ይህ ወጪ ባለሀብቶች በፓርኮቹ ውስጥ ገብተው በምርት ሥራዎች ላይ እንዲሰማሩ ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር ታልሞ የተደረገ መሆኑን የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር መረጃዎች ያሳያሉ::

በኦሮሚያ ክልል፣ ምስራቅ ሸዋ ዞን፣ አዳሚ ቱሉ ጂዶ ኮምቦልቻ ወረዳ፣ ከባቱ ከተማ በ 16 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኘው የ‹‹ቡልቡላ የተቀናጀ አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርክ›› ከእነዚህ የተቀናጁ የግብርና ምርቶች ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ ፓርኮች መካከል አንዱ ነው:: ፓርኩ በሚያዝያ ወር 2013 ዓ.ም በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ዶ/ር የተመረቀ ሲሆን፣ የአትክልትና ፍራፍሬ፣ የወተት፣ የማር፣ የስጋና የእንቁላል ምርቶችን የሚያቀነባብሩ አምራቾች የሚሠማሩበት የኢንዱስትሪ ፓርክ ነው::

በ13 ቢሊዮን ብር ወጪ በ271 ሄክታር መሬት ላይ የተገነባው ይህ ኢንዱስትሪ ፓርክ፣ ከአካባቢው አርሶ አደሮች ጋር የገበያ ትስስር መፍጠር የሚያስችሉ ስድስት የገጠር ሽግግር ማዕከላትም አሉት። በሻሸመኔ፣ መቂ፣ ዶዶላ፣ ባሌ ሮቤ፣ ኢተያ እና አለንጪቲ የሚገኙት እነዚህ ማዕከላት፣ የመሠረተ ልማት ግንባታዎች የተከናወኑላቸው ሲሆን፣ ዋና ተግባራቸው የአርሶ አደሩን ምርት በጥራትና በብዛት ሰብስቦ ለፓርኩ አምራቾች ማቅረብ ነው:: ወደ ፓርኩ የሚገቡት ባለሀብቶች ከሽግግር ማዕከላቱ ጋር በሚፈጥሩት ትስስር አርሶ አደሩን ጨምሮ የአካባቢው ኅብረተሰብ ተጠቃሚ ይሆናል::

**አሁን ላይ በኢንዱስትሪ ፓርኩ አምስት ኩባንያዎች ግንባታዎችን እያከናወኑ ይገኛሉ። ሦስት ፕሮጀክቶች ደግሞ (የምግብ ዘይት፣ የጥቁር አዝሙድ ዘይትና የእንስሳት መኖ) ማምረት ጀምረዋል**

የኦሮሚያ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ኮርፖሬሽን ዋና ሥራ አስፈፃሚ ሰናይት መብሬ ፓርኩ በቅርቡ በፌዴራል መንግስትና በኦሮሚያ ክልል ባለስልጣናት በተጎበኘበት ወቅት እንደሚገልፁት፣ 276 ቢሊዮን ብር ካፒታል ያስመዘገቡ 42 ባለሀብቶች ወደ ቡልቡላ የተቀናጀ አግሮ-ኢንዱስትሪ ፓርክ ገብተው ለማምረት ከኦሮሚያ ክልል ኢንዱስትሪ ፓርኮች ኮርፖሬሽን ጋር ስምምነት ፈጽመዋል። ከነዚህም መካከል 35 ባለሀብቶች መሬት ወስደው በተለያዩ የሥራ ደረጃዎች ላይ ይገኛሉ። ፕሮጀክቶቹ በሙሉ አቅማቸው ማምረት ሲጀምሩ ለ16ሺህ 100 ዜጎች የሥራ እድል እንደሚፈጥሩም ይጠበቃል። አሁን ላይ በኢንዱስትሪ ፓርኩ አምስት ኩባንያዎች ግንባታዎችን እያከናወኑ ይገኛሉ። ሦስት ፕሮጀክቶች (የምግብ ዘይት፣ የጥቁር አዝሙድ ዘይትና የእንስሳት መኖ) ደግሞ ማምረት ጀምረዋል::

እንደዋና ሥራ አስፈፃሚዋ ገለፃ፣ ወደ ፓርኩ የገቡ ባለሀብቶች በግብርና ምርቶች ማቀነባበር ሥራ ላይ ለመሠማራት የሚያስችሏቸውን የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች እያከናወኑ ይገኛሉ:: ባለሀብቶቹ የሚሠማሩባቸው የአግሮ-ፕሮሰሲንግ (ግብርና ማቀነባበር) ዘርፎች የማርና ሰም፣ የምግብ ዘይት፣ የአትክልትና ፍራፍሬ (ቲማቲም፣ ድንች፣ ጭማቂ… )፣ የቡና፣ የአቮካዶ ዘይት፣ የስጋ፣ የወተት፣ የቅመማ ቅመም፣ የእንስሳት መኖ፣ የፓስታና ማካሮኒ፣ የህፃናት ምግቦች ማምረትና ማቀነባበር ሥራዎች ናቸው:: ሌሎቹ ድርጅቶች ደግሞ መሬት ተረክበው የባንክ ብድር ለማግኘት እየተንቀሳቀሱ ይገኛሉ:: አንዳንዶቹም የባንክ ብድር ተፈቅዶላቸው ማሽን ማስገባት ጀምረዋል::

‹‹ኢንዱስትሪ ፓርኩ የመንገድ፣ የመብራት፣ የቴሌኮም፣ የውሃ፣ የደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ እና የአንድ ማዕከል አገልግሎት መሠረተ ልማቶች የተሟሉለት ነው:: ማራኪ ገፅታን የተላበሰና ውብ ተፈጥሮ ባለው አካባቢ ላይ የሚገኝ በመሆኑ የግብርና ምርቶችን ከማቀነባበር በተጨማሪ ወደፊት እንደ ቱሪዝም መዳረሻ ሊያገለግል ይችላል:: ፓርኩ የኢኮኖሚ ምሰሶ የሆኑ ዘርፎችን አስተባብሮ የያዘ በመሆኑ ፋይዳው ላቅ ያለ ነው›› ሲሉ ያብራራሉ::

የተቀናጁ አግሮ-ኢንዱስትሪ ፓርኮች የአርሶ አደሮችን ተጠቃሚነት ለማሳደግ እና ኢንዱስትሪያላይዜሽንን እውን ለማድረግ ትልቅ ሚና እንዳላቸው የሚናገሩት ዋና ሥራ አስፈፃሚዋ፣ ባለሀብቶች በኢንዱስትሪ ፓርኮቹ ውስጥ ያሉትን እድሎች በመጠቀም ወደ ፓርኮቹ ገብተው በኢንቨስትመንት ተግባራት ላይ መሰማራት እንደሚኖርባቸው ይናገራሉ::

የቡልቡላ የተቀናጀ አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርክ የግብርውን ዘርፍ ለማሳደግ ታልሞ የተገነባ በመሆኑ ለምርት ሥራው የሚጠቀመው ግብዓት የሀገር ውስጥ የግብርና ምርቶችን ነው:: በፓርኩ አካባቢ ያለው ማኅበረሰብ አርሶ አደር ነው:: የፓርኩ አምራቾች የሚጠቀሙት ጥሬ እቃ የአካባቢውን የግብርና ምርት ነው:: አርሶ አደሩ ግብርናውን በማዘመንና አምራችነቱን በመጨመር ለምግብና ለገበያ ከሚያውለው ምርት በተጨማሪ ለኢንዱስትሪ ግብዓት የሚሆን ትርፍ ምርት እንዲያመርት እየተሠራ ነው:: በቀጣይ አምራቾች በማር፣ በስጋ፣ በዶሮ፣ በወተት፣ በጥራጥሬ፣ በዘይትና በሌሎች ዘርፎች ወደ ሥራ ሲገቡ አርሶ አደሩ ይበልጥ ተጠቃሚ ይሆናል:: ከዚህ በተጨማሪም ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርት በመተካት የአካባቢው ኅብረተሰብ የገበያ እድል እንዲያገኝም ያደርጋል::

የ ‹‹አብዮት ቸርነት ኩባንያ›› ሥራ አስኪያጅ አቶ አብዮት ቸርነት፣ ኩባንያቸው ወደ ቡልቡላ የተቀናጀ አግሮ-ኢንዱስትሪ ፓርክ ገብቶ ጥራጥሬ፣ አቮካዶና የጥቁር አዝሙድ ዘይት ወደ አውሮፓና ቻይና ለመላክ የማሽን ተከላ ሥራዎችን እያከናወነ እንደሚገኝ ይገልፃሉ::

እሳቸው እንደሚሉት፣ ኩባንያው በፓርኩ ውስጥ በ2500 ካሬ ሜትር ላይ ያረፈ ፋብሪካ እየገነባ ሲሆን፣ የፋብሪካው ግንባታ ከ80 በመቶ በላይ ተጠናቋል:: ፋብሪካው በ2017 ዓ.ም በቀን ሦስት ሺ ሊትር ዘይት ለማምረት አቅዷል፤ ፈጣን የብድር አሠራር ከተመቻቸለት ደግሞ በቀን 10 ሺህ ሊትር ዘይት የሚያመርቱ ማሽኖችን የመትከል ፍላጎት አለው::

‹‹የምርት ግብዓቶችን ከአካባቢው አርሶ አደር ስለምንገዛ እና የአካባቢው ነዋሪ በፋብሪካው ግንባታ ላይ ተቀጥሮ እየሠራ በመሆኑ ወደ ፓርኩ መግባታችን የገበያ ትስስርና የሥራ እድል እንድንፈጥር አስችሎናል:: በሥራ ላይ ሲያጋጥሙ የነበሩት ችግሮች ከኦሮሚያ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ጋር በመተባበር መፍትሄ አግኝተዋል:: በቀጣይም ሥራችንን በማስፋፋት ተጨማሪ የሥራ እድሎችን የመፍጠር እቅድ አለን›› ይላሉ:: ባለሀብቶች ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ገብተው በፓርኮቹ ውስጥ ያለውን እድል እንዲጠቀሙም አቶ አብዮት ይመክራሉ::

‹‹ቲኬ ቢዝነስ ግሩፕ›› በቡልቡላ የተቀናጀ አግሮ-ኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ ከገቡ ድርጅቶች መካከል ምርት ማምረት የጀመረ ኩባንያ ነው:: የድርጅቱ ሥራ አስፈፃሚና የቦርድ ሊቀ መንበር ሃጂ ቶፊቅ ከድር ድርጅቱ በፓርኩ ውስጥ የሚያከናውናቸውን ግንባታዎች በአራት ወራት ውስጥ እንደሚያጠናቅቅ ይናገራሉ:: ግንባታቸው ሲጠናቀቅም ከአንድ ሺ በላይ ለሚሆኑ ዜጎች ሥራ ይፈጥራሉ:: በኩባንያው የምርት ግብዓቶችን በቀጥታ ከአርሶ አደሩ ለማግኘት ከአካባቢው አርሶ አደሮች ጋር ትስስር እየፈጠረ እንደሆነ ይገልፃሉ::

የ ‹‹ዩኒክ ትሬዲንግ›› ኩባንያ ባለቤትና ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ መሐመድ ኢድሪስ በበኩላቸው፣ ወደ ኢንዱትሪ ፓርኩ ገብተው በመሥራታቸው ብዙ ጥቅሞችን እንዳገኙ ይገልጻሉ፤ ኢንዱስትሪ ፓርኩ የተሻለ የመሠረተ ልማት እና የግብዓት አቅርቦት እንዳለው ጠቅሰው፣ ባለሀብቶች ወደ ፓርኩ እንዲገቡና በኢንቨስትመንት ተግባራት ላይ እንዲሠማሩ ተሞክሯቸውን ይናገራሉ:: ‹‹ኢንዱስትሪ ፓርኩ በጣም ምቹ ነው:: መሠረተ ልማቶች ተሟልተውለታል:: ከአዲስ አበባ ቅርብ ነው:: የምርት ግብዓቶችንም ከቅርብ ማግኘት ይችላል:: ሥራውን ስንጀምር በአምስት ሺህ ካሬ ሜትር ላይ ነበር፣ አሁን ወደ 10ሺህ ካሬ ሜትር እያሳደግነው ነው:: ባለሀብቶች ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኩ ቢገቡ ተጠቃሚ ይሆናሉ›› ይላሉ::

የሀገሪቱን የምጣኔ ሀብት መዋቅር ከእርሻ መር ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ ለማሸጋገር የሚያግዙ በርካታ መልካም አጋጣሚዎችና እድሎች አሉ:: ይሁን እንጂ እነዚህን መልካም አጋጣሚዎች በመጠቀም የኢኮኖሚውን መዋቅራዊ ሽግግር ለማሳካት የተከናወኑ ተግባራት ሀገሪቱ ካላት አቅምና ፍላጎት ጋር ተመጣጣኝ አይደሉም:: ኢትዮጵያ በኢንዱስትሪ ያላትን አቅም በመጠቀምና ከዚሁ ዘርፍ የሚገኘውን ገቢ በማሳደግ ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ የምታደርገውን መዋቅራዊ የምጣኔ ሀብት ሽግግር ለማሳካት አምራች ዘርፉ አሁን ካለው አፈፃፀም በብዙ እጥፍ እንዲጨምርና እንዲሻሻል ማድረግ ያስፈልጋል::

የአምራች ዘርፉ እድገት ሊሻሻል የሚችለው ከኢንቨስትመንት መስፋፋት ጋር ተያይዞ ነው:: የኢንዱስትሪ ፓርኮች ደግሞ የአንድ ማዕከል አገልግሎትን ተግባራዊ በማድረግ ለኢንቨስትመንት መስፋፋት ምቹ ሁኔታዎችን የሚፈጥሩ ናቸው:: ስለሆነም መዋቅራዊ የምጣኔ ሀብት ሽግግሩን ለማሳካት የኢንዱስትሪ ፓርኮችን አፈፃፀም ማሻሻል ይገባል:: ይህም ባለሀብቶች ወደ ፓርኮቹ ገብተው ለማምረት የሚያስችሏቸውን የመሠረተ ልማት ግብዓቶች፣ የሠለጠነ የሰው ኃይልና የፋይናንስ አቅርቦት ማሟላትን እንደሚያካትት ሊታወቅ ይገባል::

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ጎሜ

# ግዛትና ደስታ፤ ግዞትና ዋይታ

**ደቤ ከደጃች.ውቤ**

ግዛት እና ግዞት በአፋዊ (ድምፁ) ቃሉ እና በፊደሉ አብዛኛው ተመሳሳይ ቢሆኑም ቅሉ የተወሰኑ የሚያለያዩዋቸው ፍቺዎች አሉ :: ያው የተወሰኑ የሚያመሳስሏቸው ፊደሎቻቸውና ድምጾቻቸው ትርጓሜዎቻቸው ጭምር መሆኑ ሳይዘነጋ::

ግዛትና ግዞት በዘመናቸው ሁነኛ ቃላት እንዳልነበሩ ዛሬ መናኛ ሆነው ቀሩ:: ጃጁ፣ አረጁ፤ በእኛ ደግሞ ካረጁ አይበጁ የሚባል ነገር አለ:: ቃላቶቹ እምብዛም አገልግሎት ላይ ሲውሉ አይሰሙም ፣ አይነበቡም :: በነቢብም (theory) በገቢርም (practice) ጠፉ ወይም ቅርስ ቃላት፤ አልያም ቅሪተ ቃላት ሆነው ሊሆን ይችላል ብለን እንገምት:: መገመት ፣ መላ መምታት እንጂ ማምታታት አንችልም:: የቀረውን ለስነ ልሳን ምሁራን እንተወዋቀለን :: (እዚህ ላይ ግዛት ሲባል፤ መግዛት መሸመት የሚለውን ፍቺ ሳይካተት መሆኑ ነው ታዲያ) ያው ግን ቃላቶቹ ከከበርቴው ሥርዓት ጋር ወድቀው የቀሩ ቃላቶች ይመስላሉ:: ዴሞክራሲያዊ ፣ አፋዊም አልያም ብዕራዊም መብታችሁን ተጠቅማችሁ የበዝባዥ ርዝራዥ ቃላቶች በሉዋቸው::

ግዛትን የአማርኛ መዝገበ ቃላት ሲፈታው የተወሰነ የአስተዳደር ክልል ይለዋል:: በእንግሊዝኛ State አቻው ነው :: ዩናይትድ ስቴትስ አሜሪካ ሲባል የተባበሩት የአሜሪካ ግዛቶች መሆኑ ይታወቃል:: ገዛ ሲባልም አስተዳዳሪ፣ መሪ ወይም ባለሥልጣን ፣ መራ፣ አስተዳደር፣ አፈራ አበጀ በገንዘቡ ወዳጅ ገዛ ማለትም ነው:: ገዥ የሚለው ቃልም የበላይ አስተዳዳሪ፣ ባለሥልጣን የሚል ብያኔ አለው ፤ በጥንቱ ዘመን ሀገር ገዢ ይባል ነበር:: አስተዳዳሪ መሪ ለማለት :: በዘመናችን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ አስተዳዳሪ የብሔራዊ ባንክ ገዢ በሚል ስያሜ ይጠራሉ::

ምዕራባውያን የአፍሪካንና የሌሎች አህጉሮችን ቅኝ በመግዛት ሰዎችን እንደ ባርያ በመሸጥ፣ ቀጥሎም ሀብት ንብረት በመመዝበር ወደ ሀገራቸው ያግዙ ነበር :: ለቅኝ ገዥው ሀገር የያዘው የሰው መሬት ግዛት ሲሆን፤ ለቅኝ ተገዥው ሀገር ደግሞ የገዛ ሀገሩ ምድሩ ግዞት የሆነበት ማለት ነው:: ቅኝ ገዥው በያዘው መሬት በሚበዘብዘው ጉልበት በሚመዘብረው ሀብት ወዘተ ይዝናናበታል :: ቅኝ ተገዥው ዜጋ ደግሞ ዕትብቱ በተቀበረት ሀገሩ ጉልበቱና ሀብቱ ሲበዘበዝ ያዝንበታል::

በሌላ አባባል ቅኝ ገዥዎች በሰው ግዛት ሲያጌጡበት፤ ቅኝ ተገዥዎች ግን ግዛታቸው ግዞታቸው ይሆንና ይቀጡበታል፤ይቀጠቀጡበታል:: ለዚህ ነው ግዛትና ደስታ ግዞትና ዋይታ ያልነው:: እናም በግዛት ይዝናኑበታል ፣ይሞላቀቁበታል ፣ በግዞት ደግሞ፤ ያዝኑበታል ፣ ይሳቀቁበታል:: በዘመናችን በሀብት የበለጸጉት ምዕራባውያን የሌሎች ሀገሮችን መሬት ይዘው ጉልበት እየበዘበዙ የማዕድን ሀብቶች በቁፋሮ በማስወጣት፤ ባካበቱት ሀብት መሆኑ የአደባባይ ሚስጥር ነው::

በፈሊጣዊ አነጋገርም ‹‹ግዛቱን ጠቅልሎ ያዘ›› ሲባል ሁሉንም ቦታዎች ተቆጣጥሮ ያዘ ማለት ነው:: በቀድሞ ዘመን በጦር፣ በዘመናችን ደግሞ በብር (ኢንቨስተር ) መሬትን እንደመያዝ እንበለው :: ልዩነቱ የቀድሞው ዘመን ግዛት በጦር በግድ የሚያዝ ሲሆን በዘመናችን ግን ባለ ሀብቱ ሀብት ንብረት ለማፍራት ለዜጎች የሥራ እድል ለመስጠት ግዛቱ መሬቱ በብር በውድ የሚያዝ ነው:: ወደው ፈቅደው መንግሥትም ፈቅዶበት :: እዚህ ላይ አንድ ሀገር ለሰዎች ግዛትም ግዞትም የሚሆንበት አመክንዮ እንዳለ ማስታወስ ያሻል:: ቅኝ ለሚገዛው ሀገር ግዛቱ ሲሆንለት ቅኝ ለተያዘው ተወላጅ ሀገሩ ግዞቱ ይሆንበታል::

በሀገራችን በንጉሡ ዘመን የነበረው አስተዳደር ጠቅላይ ግዛት የሚባል ስያሜ ይጠራ ነበር:: ደረጃው በወታደራዊ ዘመን እንደነበረው ክፍለ ሀገር እና ከዘመናችን ክልል ጋር አቻ ነበር ማለት ይቻላል:: አቻ ነው ያልኩት የሥልጣን ደረጃቸውን ሳይሆን የክልል አስተዳደራቸውን መሆኑን እንድታውቁልኝ እሻለሁ:: ይሁን እንጂ አስተዳደሩን ሁሉ ሲያጣጥሉ ሲያብጠለጥሉ የሚውሉ ጽንፈኛ ሚዲያዎች ‹‹ያም ዘውዳዊ ይሄም ዘውጋዊ ›› የሚሉ አሉ:: አንዳንዶቹ ሲናገሩም ያም የዘውድ ሐረግ ፣ይሄም የዘር ሐረግ ስለሚሳሳቡ፤ መሳ ለመሳ ናቸው ይላሉ:: ዝም ከተባሉ ዘውዳዊ እና ወታደራዊና ዴሞክራሲያዊ አገዛዝ ተመሳሳይ ናቸው ሊሉን ነው:: እነሱ ምንም ቢሉም እኛ ግን የሚበጀን ዴሞክራሲ ነው::ሞናርኪ፣ አናርኪና ቢሮክራሲን ወደዛ ጣሉልን::

> **በሀገራችን በንጉሡ ዘመን የነበረው አስተዳደር ጠቅላይ ግዛት የሚባል ስያሜ ይጠራ ነበር:: ደረጃው በወታደራዊ ዘመን እንደነበረው ክፍለ ሀገር እና ከዘመናችን ክልል ጋር አቻ ነበር ማለት ይቻላል**

በንጉሡ ዘመን የነበረው ጠቅላይ ግዛት በሥሩ አውራጃዎችና ወረዳዎችን ያካተተ ነበር:: ግዛት የሚለውን ቃል አንዳንድ መዝገበ ቃላቶች ወረዳ ፣አውራጃ፣ ቀበሌ ይዞታ ርስት ጉልት መንግሥት መክ 6፥2 ሕዝ 29 ፥18 በሚል ይፈቱታል:: በደርግ ዘመን የነበረው የክፍለ ሀገር አስተዳደር በውስጡ አውራጃዎች፣ ወረዳዎችና ቀበሌዎች እንደነበሩት ይታወሳል::

በዘመናችን ያለው አገዛዝ ደግሞ ወይም አስተዳደር በክልል ተከፋፍሎ በሥር በሥሩ የዞኖችና ወረዳዎችን አስተዳደር የሚያካትት ነው:: የቀበሌዎች አስተዳደር በወረዳ ሥር እንዲዋቀር ተደረገ :: ማለትም አራት አምስት ቀበሌዎች በአንድ ወረዳ ሥር እንዲዋቀሩ ተደርገው ተጨፈለቁ:: ያው ቀበሌ ተቀበረ እንበለው :: የት ነው የተቀበረው ? እንዳትሉ ብቻ:: ነፍስ ይማር ማለት ግን መብታችሁ ነው::

የደስታ ተክለወልድ መዝገበ ቃላት ግዞት የሚለውን ቃል ሥርወ ቃሉ ጋዘ የሚለው ነው:: ብያኔው ሁለት ዓይነት ነው :: ተጋዘ ሲባል በግዞት ተወሰደ ማለት ሲሆን በሌላ ብያኔውም አንድ እቃ ከቦታ ወደ ቦታ ተወሰደ፣ ወይም ተጓጓዘ ይለዋል:: አጋዘ ሲባልም እቃን ከቦታ ቦታ ወሰደ ወይም አጓጓዘ ማለት ነው:: የቁም እሥር ሲባልም ሳይታሰር የተጋዘ፣ ከዚህ አትለፍ የተባለ ሰው ነው ሲል መዝገበ ቃላቱ ይገልፃል::

በሌላኛው ብያኔ ስንመጣ ግዞት የሚለውን ቃል አንድን ሰው ከሚኖርበት አካባቢ አንስቶ ወደ ሌላ አካባቢ በመውሰድ በዚያው ቦታ ብቻ ተወስኖ እንዲቆይ የሚደረግበት የእስራት ዓይነት ነው:: አሁን ግዞት ተብሎ የሚታወቅ የእስራት ዓይነት የለም :: ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትም ለዚህ ዓይነት ኢፍትሐዊ እስራት ክፍተት አይሰጥም:: ግዞተኛ ማለትም በግዞት ያለ ሰው ማለት ነው:: ተጋዘ ሲባል በግዞት እንዲቀመጥ ተደረገ :: አጋዘ በተመሳሳይ በግዞት አስቀመጠ ማለት ነው :: አንዳንድ ብያኔዎችም ግዞት የሚለውን ቃል (ግእዝት) ፤ ሽረት እስራት ቅጣት ውርደት :: ኢሳ 42፥7 ማቴ 5፥25 ግዞተኛ የተጋዘ ፣ የተሸፈነ፣ የታሰረ እስረኛ ግዞተኝነት እሥረኛነት በሚል ይፈቱታል:: መጽሐፍ ቅዱስም በግዞት ውስጥ ለነበሩት ነፍሳት ነፃነትን ሰበከላቸው ይላል::

የተለያዩ የአማርኛ መዝገበ ቃላቶች ለማየት እንደሞከርኩት ግዞት የሚለውን ቃል እንደ እስራት አድርገው ብቻ ነው ያስቀመጡት:: ነገር ግን በነገሥታቱ ዘመን በነበረው አገዛዝ መሠረት አቅራቢያቸው ያለ ሹመኛ፤ ንጉሡ ካልጣማቸው፣ አልያም በዙፋኔ ላይ ሴራ ይሸርባል፣ አልጋዬን ለመገልበጥ ያስባል ብለው የሚጠራጠሩ ከሆነ፣ ወይም ዐይነ ጥላው ከከበዳቸው ነገሥታቱ ካሉበት ራቅ ወዳለ ግዛት አልያም ወደ ጠረፍ አካባቢ በግዛት አስተዳዳሪነት በሹመት ይልኩታል:: አንዳንድ መጽሐፎች ግን በነገሥታቱ ራቅ ብሎ ወደ ጠረፍ አካባቢዎች እንዲያስተዳድር የተደረገ ግለሰብ ወይም ሹመኛ አስተዳዳሪ ፤ በነፃነት ቢያስተዳድርም ዓላማው ግን ንጉሡ ሹመኛውን ከቤተመንግሥታቸው ራቅ ለማድረግ የሚሰጥ ሹመትን፤ ግዞት ነው ይሉታል :: በወቅቱ ሥረ ታሪኩን የሚያውቁ በግዞት መልክ ተሾሙ እያሉ ይጽፉ ነበር:: ሲብስ ደግሞ በአቅራቢያቸው ከፉኛ የሚያዩት ሹመኛ ካለ ወደ ግዞት ይወስዱታል:: በሹመት መልክ ሳይሆን በእስራት ማለት ነው:: የት እንደታሠረ ግን የሚያውቁት ንጉሡና ጋሻ ጃግሬዎቻቸው ብቻ ናቸው::

ከዚሁ ጋር የተያያዘ ከቃላቱ የሚመሳሰል ግዝት የሚባል ቃል አለ:: ግዝት ማለት፣ መገዘት፣ መ□ገዘት ( ማለትም ገዘተ ፣ተገዘተ ፤ ሲጠብቅ ሲላላ) ዓይነት ፍቺዎች ማለትም ገዘቱት፣ ተገዘተ ዓይነት ብያኔዎች:: ነገርን ነገር ያነሳዋልና አላና ዞጋ ግዝትና ግዞት የሚል መጽሐፍ አላቸው :: መጽሐፉ ስለ መጫና ቱሉማ መረዳጃ ማኅበር ታሪክ የሚያትት ነው:: መጫና ቱለማ መረዳጃ ማኅበር ሆኖ በ1955 ዓ.ም በኦሮሞ ቋንቋ ተናጋሪዎች ቢመሠረትም በ1959 በንጉሡ መንግሥት እገዳ ተጣለበት:: ደርግ ሲተካም ማኅበሩን ሊመሠረት አልቻለም:: የደርግ አመራሮችም ማኅበሩን የጎሪጥ እያዩት ስለነበር በድጋሚ ተመሥርቶ መቀጠል አልቻለም:: ለማኅበራዊ ዓላማ የተመሠረተውን ማኅበር ሲገፉት ሲገፉት ወደ ፖለቲካው ከተቱት:: ደርግ ሲወድቅ በድጋሚ መረዳጃ ማኅበሩ በ1984 ቢመሠረትም እንደገና በ1996 ታገደ::

ግዝት መሃላ ፣ክልከላ፣ ውግዥ፣ ርግማን ማለት ነው:: በቀደሙት ዘመናት ቃላቶቹን ከሃይማኖት ያፈነገጠን ሃሳዊ መምህር ወይም መናፍቅን ለማግለል፤ ሲጠቀሙበት የሚሰጡት ስያሜ ነው :: ማውገዝ ፤ አወገዘ፣ ተወገዘ ይባላል:: ምንም እንኳን መገዘት ብዙም ከጽሁፍ እየጠፋ ቢሄድም ፤ በዘመናችን የዓለም ሀገሮችን ያስተሳሰረው የፖለቲካ ርዕዮተ ዓለም፣ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነቱ ወዘተ የበለጠ በመጠንከሩ በሀገሮች መካከል ግንኙነት ሲሻከር ዲፕሎማሲያዊ ፣ፖለቲካዊ፣ ምጣኔ ሀብታዊ ማዕቀብ በመጣልና ርዳታና ብድር በመከልከል ግንኙነቱን ለማሻሻል ይጥራሉ:: ‹‹የተገዘተች ነፍስ፤ የተለጎመች ፈረስ›› የሚለው ምሳሌያዊ ብሂልም ስለመገዘት፣ መወገዝ የሚነገረን ነገር አለ:: እናም ማዕቀብ ግዞት ከሚለው ቃል ተቀራራቢ ይመስላል::

ማዕቀብ ማገድ፣ መታገድ፣ ታገደ ፣ መገደብ፣ ገደብ ማለት ነው:: ( adoption of sanction ,embargo, prohibit ) በብዛት ያደጉት ሀገሮች ታዳጊ ሀገሮችን እኛ የምናደርገው ደግፉ፤ ከእኛ ውሳኔ አትለፉ ፣ የምንተነፍሰውን ተንፍሱ፣ የምንለውን በሉ፣ የሚሉት ሀገርና አመራር ችላ ሲላቸው እንዲደግፋቸው ለማድረግ የሚያደርጉበት ምጣኔ ሀብታዊና ፖለቲካዊ ጫና ነው:: ይህም ላይ ከጠቀስነው ማውገዝ ፣ግዝት ከሚሉት ቃላት ጋር ይመሳሰላል:: ግዝት ሲባል በብዛት ግለሰብ አልያም ቡድን ተኮር ናቸው :: በብዛት ማዕቀብ የሚለው ግን በሀገሮች ላይ የሚደረግ ምጣኔ ሀብታዊና ፖለቲካዊ እንዲሁም ዲፖሎማሲያዊ ጫና አልያም ተፅዕኖ መሆኑ ነው ልዩነቱ::

ስፖርትና መዝናኛ

# የዘመን ጥበብ

## የጉለሌው ሰካራም

ሙሉጌታ ብርሃኑ

በ1941 ዓ.ም ነበር በኢትዮጵያ የመጀመሪያ የሆነው አጭር ልቦለድ የተጻፈው:: ልቦለዱም "የጉለሌው ሰካራም" ነበር:: ደራሲ ተመስገን ገብሬ አስቀድሞ ተነስቶ ጻፈው። በወቅቱም ተአምር አያልቅ...አጃኢብ! ተባለለት። ታሪኩ የአንድ ተራ የጉለሌ ሰካራም ታሪክ ቢመስልም ከባህር ውሃው መሀከል አንባቢውንም እራሱን በመፈለግ ቀዘፋ ውስጥ እንዲንቦራጨቅ አድርጎታል። ደግሞም እንዲህ ዓይነቱ ቅልብጭ ቁልጭ ያለውን ልቦለድ አንብቦ አያውቅምና አዲስ ዓይነት ጥፍጥናም ነበረው።

በየአንባቢው ሁሉ "የጉለሌው ሰካራም!... የጉለሌው ሰካራም!" ተባለ። "የቱ የጉለሌው ሰካራም?" አለ አንዱም። " ያ ተበጀ ነዋ!" ደግሞ እንደገና "ተበጅስ ማነው?" ይላል ሌላውም። ሁሉም አጠያይቆ የደረሰበት ነገር ቢኖር ተበጀ በጉለሌ ውስጥ የታወቀ ዶሮ ነጋዴና ታዋቂ ሰካራም መሆኑ ነው። ጥያቄም አያልቅ "ተበጀ ዶሮ ነጋዴ?" ኧረ ወዲያ!...

"...የታወቀ ዶሮ ነጋዴ ማነው ብለው ከገፈርሳ እስከ ደጃዝማች ይገዙ ሰፈር ለጠየቁ ሰዎች፤ ተበጀ ሰካራሙ ተበጀ ዶሮ ነጋዴው፤ ተበጀ ነው ብለው ይነግሯቸዋል:: የሕይወቱ ታሪክ ፍፁም ገድል ነው:: ጢም ያለው ሽማግሌ ሰው ነው:: ራሱን ጠጉር ውሃ ወይም መቀስ ነክቶት አያውቅም:: ማለዳ አይናገርም:: በጠርሙስ የከመረውን ከጠጣ በኋላ ሲራገም ወይም ሲሳደብ ሲፎክር ወይም ሲያቅራራ ድምፁ ከፈረንጅ ውሻ ድምፅ ይወፍራል:: ቢያውቀውም ባያውቀውም ላገኘው ሁሉ ማታ ሰላምታ ይሰጣል:: ቢያውቀውም ባያውቀውም ካገኘው ሁሉ ጋር ማታ ይስቃል:: ቢያውቀውም ባያውቀውም የሰላምታው አይነት እንደ ወታደር ወይም እንደ ሲቪል ቢሆን ለእርሱ እንደተመቸው ነው" እያለ የሚነግረን እውነታ የተበጀ የብቻው አይደለም። እዚህ ውስጥ የብዙ ሰካራሞች አንድ ዓይነት እውነት አለ:: ተበጀ ግን ከዚህም ሌላ አለው::

"...በፀባዩ ከተባለለት የባሰ ሰካራም ይሁን ወይም የጉለሌ ባህር ዛፍ ውስጥ ወጥቶ እንደ አዲስ እንግዳ ሰው ሆኖ ለአዲስ አበባ ታይቷል:: ከዱሮ የእንጨት ጉምሩክ አጠገብ ወደ ምሥራቅ ሲል ካለው ወንዝ ማዶ ድልድዩን ወደ ምሥራቅ ተሻግሮ መጀመሪያ የሚገኘው አነስተኛ ሳር ክዳን ቤት የተበጀ ቤት ነው።" ይለናል:: ተበጀ ሁሌም ይጠጣል:: ዝም ብሎም እንደጠጣ ነው:: ግን እንደ አብዛኛዎቹ ሰካራሞች የገንዘብ ችግር የለበትም:: እንዲያውም ባለጠጋ ነው ይለናል:: ከምንም በላይ ግን መድፈኛ ሰካራም ነው::

ታዲያ በስካር ውስጥ ብርሌውን ጨብጦ ጠጁን ከማንቃረር፣ መለኪያውን ይዞ አረቄና ውስኪውን ከማንዶቅዶቅ በስተቀር ምንስ ይኖርና? እንል ይሆናል። ብንልም ኩነኔ አይሆንብንም። በሰካራሙ ተበጀ ሕይወት ውስጥ ግን እልፍ ደግነቶችና የፍቅር መስዋዕትነቶች እፊቱ መሳ ለመሳ ቆመው በእንባ ይራጫሉ። "በዚያ በቤቱ በዚያ በጉለሌ በሠፈሩ ኖረ:: እንጨቱን ተሸክሞ አፈሩን ቆፍሮ ቤቱን የሠራው እርሱ ነው:: ዋጋ ከፍሎ አስከድኖታል:: ተበጀን ኩራት ተሰማው:: ቆይቶ ደግሞ አይኖቹ እንባ አዘሉ:: በጉንጩም የእንባ ዘለላ ወረደው:: በግራ እጁ መዳፍ ከጉንጩ የተንከባለለውን እንባ ጨፈለቀው:: ...ሊነገር በማይችል ደስታ ልቡ ተለውሳል:: ዝናብ ያባረራቸውም ከቤቱ ጥግ ሊጠለሉ ይችላሉ:: ቤት የእግዚአብሄር ነውና ውሽንፍር እንዳያገኛቸው ከቤት ውስጥ ዝናቡ እስኪያባራ ይቆያሉ" በማለት ነበር ተበጀ ቤቱን በመሥራቱ ደስ ያለው።

"ሰካራም ቤት አይሠራም፤ ቢሠራም...." ቢልም ብሂሉ ተበጀ ግን ቤት ሠራ። በእርግጥ በጊዜ አይገባም ነበር። ሰካራም ሆኖ ሳለ ቤት የመሥራቱ ነገር ጸሀፊው አንዲት የፈለጋት ምልከታ ነበረችው። ሰካራሙን ተበጀን በአልኮል መለኪያው ለክተውት ቢያልፉና ባያውቁት ችግሩ የቀጂው እንጂ የተበጀ አይደለም። እንዴት? ካሉ የተበጀ የሚታየው ስካርና ሰካራምነቱን ይሁን እንጂ እንደሰው አስቦ ሰው ሠብዓዊ በመሆን ማንስ ደርሶበት? የሚወግር ድንጋዩን እንጂ መች ውስጡን ይመለከትና... ሰካራሙ ተበጀ፣ የጉለሌው ሰካራም እራሱን ሲገድል ይኖራል እንጂ ለሰውማ ሟች ነው። ያቺን ደሳሳ ጎጆውን ሲያቆም እንኳን ደስ ያለው ለራሱ አልነበረም። ታዲያ ከሰካራሙ ተበጀ ሌላ በጉለሌ መንደር ውስጥ እንደዚያ ያሰበ ማን ነበር? ማንም። ምግባሩ እንጂ ልቡ የእግዜር ማደሪያ ነበረች።

"የጉለሌው ሰካራም" በሀገራችን የመጀመሪያው አጭር ልቦለድ አይደለም ብለው ደፍረው የሚናገሩ የሉም። የመጀመሪያውማ እሱው ራሱ ነው በማለት ከነማስረጃው ፈርጠም ብለው የሚመሰክሩለት ግን አያሌ ናቸው። ለአብነትም አስፋው ዳምጤ እና ዘሪሁን አስፋው ተጠቃሽ ነቃሾቹ ናቸው። በዚህም አሉ በዚያ የተመስገን ገብሬ "የጉለሌው ሰካራም" የአጭር ልቦለዶች እንነቻ ነው። እሱን ያነበበና የተመለከተም ነበር ቀጣዩን የምናብ ምጣድ እያሟሸ ሌላ ሰበከታም የልቦለድ እንጀራ ያበላን። ከቡሀቃው እየተቀዳ ሲጋገር ተሰንብቶ አሁን የአጫጭር ልቦለዶቹ መሶብ ጢም ስላለ እንጎቻውን የዶሮ ፍርፋሪ አናደርገውም። በኩርነቱን ተቀብሎ የሚገባውን ዕውቅና መስጠት እዚያ አካባቢ ለነበሩ ለየትኛዎቹም አጫጭር ልቦለዶች ያለንን ቦታ አያጎድለውም። ለዚህ ታላቅ የሥነ ጽሁፍ ጀብዱ ጸሀፊው ተመስገን ገብሬ ዳጎስ ያለ ክብርን ላቅ ከላቀ ምስጋና ጋር ልንቸረው ግድ ይለናል።

እንግዲህ የጉለሌው ሰካራም ተበጀ እንደሆን ነገረ ሥራው አያልቅም። ጥንባዣም ሌቱም ነግቶ የሚነጋ አይደለም። ቢነጋ እንኳን ለአንድ ግብግብና ትርምስ ነው። ተበጀ የመሰለውንና ውስጡ የሚያዘውን ሕይወት ያለጭንቅ ይኖራል። በእርሱ የሕይወት ጎጆ ዙሪያ ተጠግጥገው በሀሜት ወሬ የሚጨነቁበት የመንደሩ ሰዎች ናቸው። በዕድርና በዕቁቡ ቢሰባሰቡ፣ ቡና አፍልተው ከጎረቤት ቢጠራሩ ያለ ተበጀ የወሬ ቡና ቁርስ ሲኒው አይነሳላቸውም:: ቡናውም አይጠጣላቸውም::

ትናንት፣ ከትናንት በስቲያና ዛሬም ያዩትን የስካር ጀብዱ እየተረኩ ማውካካት ነው። ስለ ስካሩና ሁኔታው የሚናገር ይኑር እንጂ አፉን ከፍቶ የሚያደምጠውስ አሸን ነው። በሰካራሙ ደካማ ጎን ሾልኮ ትኩስ ደሙን እያስመለከተ ቀልደኛና ጨዋታ አዋቂ በመሆን ተወዳጅነትን ለማግኘት የሚጥረው ሰው ብዙ ነው። እየሰከረ ከሚወድቀው ተበጀ በላይ የተበጀን አወዳደቅ እያሳየ ካዳማዊን በሳቅ ገድሎ አፈሩን በተበጀ ላይ ይመልሰዋል። ተበጀ ምስኪኑ የጉለሌ ሰካራምስ? እሱማ በየሰው ልብና ቤት ውስጥ በቁም ሞቶ በቀልድ አፈር ያለበሱት ከንቱ ነዋሪ ነው::

በሕይወት እየኖረ እንዳለ እንደ አንድ የመንደሩ ነዋሪ ማንም እርሱን ከቁብ ቆጥሮ ለቁም ነገር ባይፈልገውም እርሱ ግን ለአንዲት ነብሱም ሳይራራ ፈጽሞ ያልጠበቁትን ታላቅ ግብር ፈጽሞ ይገኛል። ግን ይኼም ቢሆን ለማንም ከቁም ነገር የሚቆጠርለት ነገር አይደለም። እጁ አመድ አፋሽ ሥራውም ሳቅን ቀስቃሽ የፌዝ ጠርሙስ ሆኖ ይቀራል። እራሱ ወድቆ የሚያጣጥረው ሰው እንኳን፤ ተበጀ እየወደቀ እንዲያስቀው እንጂ ተነስቶ እንዲሸከመው የሚፈልግ አይመስልም። የተበጀ ልብ እንደ ብርሌው ሁሉ አንስተው ባፈረጡት ቁጥር እንክትክቱ የሚወጣ ቢሆን ኖሮ የሚሞተው ገና ያኔ በመጀመሪያ በሰከረበት ዕለት ይሆን ነበር። ግን እርሱም የዋዛ ሰካራም አይደለም። ልቡን እንጂ ጆሮውን አይከፍትላቸውም። እንዲሁ እንደልቡ ሆኖ እየኖረ ስሙ ከሰፈር አምልጦ መላውን አዲስ አበባን አካለላት። በየትኛውም ሰፈር ከማንም በላይ የጉለሌው ሰካራም ታዋቂ ነው። ሰው እንዴትስ በስካር እንዲህ ዝነኛ ይሆናል? ሰው በስኬቱ ብቻም ሳይሆን በውድቀቱም ዝነኛ ሟች ለመሆን እንደሚበቃ ይነግረናል። ምክንያቱም ጥሩ ነገሮችን ለመስማትና ለመናገር ከምናሳድደው በላይ ልብና ጆሮዎቻችን በመጥፎ ዜናዎች ፍቅር የተነደፉ በመሆናቸው ነው።

ለማየት የምንፈልገው ተበጀን ሳይሆን የጉለሌውን ሰካራም ስለሆነም ግርድ ማንነቱን ከፍሬው፣ ፍሬውንም ከግርዱ ነጥሎ ለማየትም ሆነ ለመቀበል አይቻለንም። በዚህ ምክንያትም እንደሰው ካለው ማንነትና ተሰጥኦ ቢያንስ አንዱን እንኳን ሳይሰጠንና ሳንቀበለው ደርሶ አፈር ይቀማዋል። "ጉለሌ ተኝቷልና ከዚሁ ከባሕር ዛፍ ሥር ቁጭ ብዬ ብጠጣ የሚታዘበኝ የለም" አለና አሰበ:: እውነቱን ነው:: ጉለሌስ ተኝቶ ነበር ነገር ግን አሁን እርሱ ጠጥቶ የሰከረ እንደሆነ ጉለሌን ሊቀሰቅሰው ነው እርሱ ከጠጣ በጉለሌ ማን ይተኛል?"

ሰዎችስ እኛን የሚፈልጉት ለምንድነው? ወዳጅነታችን የተገመደበትን ሀረግ የተመዘዘውስ ከወዴት ነው? ጥያቄው ለተበጀ ቢሆን ኖሮ ምናልባትም "ኧረ ወዲያ ደግሞ ስለእነርሱ ምን አገባኝና...እኔ ተበጀ ከወዴት እንደመዘዝኩት እንጂ ከወዴት አባታቸው እንደመዘዙት ለማወቅ ዴንታም የለኝ!" የሚል ይመስለኛል። ቅሉ ግን ወደደም ጠላም የእርሱ መፈለግና ወዳጅነቱ የሚቀዳበት ስፍራ ከጨዋታና ከቧልት ከበርቻቻው መንደር ነው።




የእርሱ ወዳጆች ተብለው ሊቆጠሩ የሚችሉት የጠጅ ቤቱ አጫፋሪዎቹ ብቻ ናቸው። እነርሱም ቢሆኑ ከመሀከላቸው በመተመዘዘው የወዳጅነት ቀለበት ውስጥ አንድ ስውር መሃላ ያለ ይመስላል። እንዲህ የሚል..."በኛና በአንተ መሀከል ያለው ወዳጅነት እስከ እድሜ ልክ መቆረጫችን ድረስ በእዚህ የጠጅ ቤት አግዳሜ ወንበሮች ፊት ብቻ ይሁን። ከዚህ ቃልኪዳን ያፈተለከም የፍቅር ማተባችንን በጥሷልና በሌት በማዕልቱ የቅዠት ዲን በላዩ ይውረድበት" ይኼኔ ብርሌዎቹ ተነስተው የጭብጨባ ኳኳታቸውን ተገጫጭተው አሰሙ። ይህን የአንድነት ማሰሪያ የሆናቸውን ልጥ መሃላ በአፋቸው አውጥተው አይበሉት እንጂ ልባቸው የሚያውቀው እውነታ ግን ይኼው ነው። ከጠጅ ቤቱ ከተለዩ በኋላ ተበጀ ትዝ የማይላቸው ሙት ነው::

"ወደ ውጭ እንደ እርም ወርውሮት የነበረውን የመጠጥ ጠርሙስ ሁሉ በጨለማው ዳብሶ አንድ በአንድ ለቃቀማቸው:: አንዱን ግን ቀና አደረገና ከአፍንጫው አስጠግቶ አሸተተው:: በጠርሙሱ ቅርፅ የመጠጡን አይነት አወቀው:: ዊስኪ ነበርና ስለዚህ ነው ሰው እንዳይሰማ ቀስ ብሎ ሳቀ:: የጠርሙሱን ግማሽ ከጠጣ በኋላ ግን በአፉ ቡሽ ቢወትፍበት ለሳቁ መጠን የለውም::

...

ቀጥሎ ከእግሩ በታች የወደቀውን ጠርሙስ እየቆጠረ ይህን ሁሉ እንደጠጣሁት አላምንምና በጉለሌ አፈርሳታ ይደረግልኝ እነናቄ እነተሰማ አጎቴም ይጠጣሉ አለ::"

በዚህ አጭር የልቦለድ ታሪክ ውስጥ ደራሲው ተመስገን ገብሬ ስለምንስ ነው እያወራን ያለው? "ስለሰካራሙ ተበጀ እንጂ ሌላ ስለምን ሊሆን?" እያልን ጥያቄውን በጥያቄ ብናዳፍነው ስህተት ላይሆን ይችላል። ትክክለኛ እውነት ግን አይደለም። ስለ ሚያወራው ነገር ስሙ ስለ ጉለሌው ሰካራም ይሁን እንጂ ወርቁን ግን በፍለጋ ካልሆነ በቀር በዋዛ አናገኘውም። ከበስተጀርባው ሊነግረን የሚፈልገው አንድ ነገር እንዳለ መሀል መሀል ላይ አስታኮ ጣል የሚያደርጋቸው ቃላት ይጠቁሙናል። ሳይንሳዊ እውነታዎችን ከፍልስፍናው ጋር ጨምቆ አንድ የተለየ ቅመማ ሲያካሂድ ይታየናል።

ተበጀ እንደ ጉለሌው ሰካራምነቱ ሕይወቱ የድሎት አነበረችም። ሚስት ለማግባት ፈልጎ የጠየቃቸው ብዙ ሴቶች ምራቅ ተፍተው ተመናቅረውበታል። ትዳሩ እንኳን ቀርቶ ለቤቱ ገረድ ፈልጎ እንኳን አጥቷል። በሰንበቴና በእድር ማህበሩ እንኳን ንቀው ነፍሱን አርክሰዋታል። ታዲያ ለምንስ ይጠጣል? ካላችሁ ደግሞ "ተበጀ ለመስከር ይጠጣል። ደስ ያለው እንዲመስለው ይጠጣል። ብስጭቱን የሚረሳ መስሎት ይጠጣል" በማለት የሚነግረን ነገር ዞሮ ቀለበት ይሠራል። የዚህ ችግር ቁልፉ ቦታ ሰካራም በመሆኑ... ብለን አንዘጋውም። ምክንያቶቹ መጠጥን፣ መጠጥም ስካርን፣ ስካርም ሌላ ሲያጎርፍበት እንመለከታለን። በስካሩ ጢንቢራው ከመዞሩ የተነሳ መንገድ ላይ እንደወደቀ አድሮ ያውቃል። በወደቀበትም አውቶሞቢል እግሩን ድጦት አልፏል። እስር ቤት ውስጥ ገብቶ መግባቱን እንኳን ያወቀው ጠዋት ሲነጋ ነው። በእነዚህ ሁሉ ትርምሶች ውስጥ እየሆነም መጠጣቱን አያቆምም። እናም ተበጀ ከዚያ እንደራስ ቅሉ ከበቀለበት ሱስ ይወጣል ብሎ ማሰብ ከንቱ ድካም ይመስላል። ጸሀፊው ግን አንዳች ተአምር ለመሥራት እንደቀጠለ ነበር።

ደራሲውም በስተመጨረሻ አንድ ነገር አስቀመጠ:: ተበጀ በአንድ ዓመት፣ ከዘጠኝ ወር፣ ከዘጠኝ ቀንም በኋላ የሆነበት ይህ ነበር፤ "...አንዱ ሐኪም ከጉልበቱ ይቆረጥ አለ:: ሌላው ግን ሁለተኛ እንዳይሰክር ከቂጡ አስጠግቼ እቆርጠዋለሁ አለና ከቂጡ አስጠግቶ ቆረጠው:: የተቆረጠውን እግሩን ከፊቱ መዝናኛችሁ አስታቅፉት ብሎ አስታማሚዎችን አዘዘ:: እግሩን ከፊቱ መዘኑትና አሥር ኪሎ የሆነው እግርህ ይኸውልህ ታቀፈው ብለው አስታቀፉት:: በዚህ ጊዜ በአጥንት የተጣሉት ውሾች በላዩ ላይ ተረፈረፉበትና በድንጋጤ ከእንቅልፉ ነቃ:: ይህ ሁሉ የደረሰበት በሕልሙ እንደነበር ማወቅ አቃተው:: ከአልጋው ላይ ወረደና ገረዱን ወይዘሮ ጥሩነሽን ከመኝታቸው ቀስቅሶ እየጮኸና እየተንዘረዘረ ስንት እግር ነው ያለኝ ብሎ ጠየቃቸው:: ወይዘሮ ጥሩነሽም "ድሮ ስንት እግር ነበረዎ ጌታ?"

...

ተበጀ እግሩን አጎንብሶ ለመሳም ሞከረና ራቀው:: ወደ ሰማይ እያየ መጠጥ ማለት ለእኔ ሞት ማለት ነው አለ:: ጊዜውም ሌሊት ነበር:: እንደዚህ የሚሉበት ሌሊት ያልፋል ብለው ወይዘሮ ጥሩነሽ መለሱለት" በማለት ያሳርግልናል። ደራሲው በመጨረሻ የተበጀን የህልም ቅዠት የተናገረበት መንገድ እንዴት አድርገን በምን ቃላት ልናደንቀው እንደምንችል ይጠፉናል። "እነሆ ተበጀም ሱሱን አቆመ። ከዕለታት በአንዱም ቀን በህልሙ ሲጠጣ ታየው። በህልሙም ሐኪሞቹ እግሩን ቆርጠው ሲሰጡትም ተመለከተ" አላለንም። ቢለን ኖሮ ስሜታችንን እስከ ጫፍ ድረስ ቋጥሮ የያዘውን ውበት ባልተመለከትን ነበር። መጠጥ ያቆመበትን የጊዜ ርዝመት፣ ዓመትና ወሩን ሲያስቆጥረን እንኳን የነገረን ለዘብ አድርጎ ነበር። እንዲህ በማድረጉም እርገጠኛ ሆነን መጨረሻውን እንዳንገምተው አደረገን። በልቦለዱ ውስጥ ስለ ተበጀ ትረካውን ጀምሮ እስኪጨርስልን ድረስ ከሀ_ፐ በእረቂቅ የአዕምሮ ጨዋታ ውስጥ እንድንቆይ አድርጎ ተረከው። የጉለሌው ሰካራምም ከመጀመሪያም የመጀመሪያው ሆነ::

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## ለነገዋ ሴት ዛሬ

**አስናቀ ፀጋዬ**

ሴቶች በሕይወታቸው ልዩ ልዩ ችግሮች ይገጥማቸዋል:: እነዚህ ችግሮች ማኅበራዊ አልያም ኢኮኖሚያዊ ሊሆኑ ይችላሉ:: ኑሯቸውን ለማሸነፍ ሲሉ ወደተለያዩ ዓረብ ሀገራት ተሰደው ስንት ደክመው የሠሩበት ሳይከፈላቸው ባዶ እጃቸውን የሚመለሱ ሴቶች ጥቂት አይደሉም:: በቤተሰብና በተለያዩ ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ምክንያት ሳይፈልጉ ኑሯቸውን በሴተኛ አዳሪነት የሚገፉም ብዙ ናቸው:: እጅ አጥሯቸው በየጎዳናው ወድቀው ምፅዋት የሚለምኑ ሴቶች ቁጥርም ቀላል የሚባል አይደለም::

ለእነዚህ ሴቶች በተለያዩ ጊዜያት ድጋፍ ሲደረግ የቆየ ቢሆንም ወደ አንድ ማዕከል አስገብቶ የተሐድሶና ክህሎት ሥልጠና በመስጠት ወደ ሥራ የሚሰማሩበትን መንገድ ማመቻቸት የተቻለውን ግን በዚህ ዘመን ይመስላል:: ይህም እውን የሆነው በነገዋ ሴቶች ተሐድሶና ክህሎት ማበልፀጊያ ማዕከል ነው::

የነገዋ ሴቶች ተሐድሶና ክህሎት ማበልፀጊያ ማዕከል ዋና ዳይሬክተር ሂርጳሳ ጫላ (ዶ/ር) እንደሚናገሩት፣ ማዕከሉ በአስራ አንድ ወራት ውስጥ ደረጃውን በጠበቀ መልኩ ተገንብቶ የተለያዩ አገልግሎቶችን እየሰጠ ይገኛል:: ወደማዕከሉ የሚመጡ ሴቶች አራት መሠረታዊ ነገሮችን ያለፉ ሊሆኑ ይችላሉ:: የመጀመሪያዎቹ የጎዳና ላይ ሕይወት ይመሩ የነበሩ ናቸው:: ሁለተኛዎቹ በኢኮኖሚ ራሳቸውን ያልቻሉ በየቤቱ ያሉ ጥገኛ የሆኑ ወረዳቸው እነዚህ ሴቶች መታገዝ አለባቸው ብሎ የለያቸው ናቸው::

ሦስተኛዎቹ ሴተኛ አዳሪ የነበሩና በዚህ ሥራ ራሳቸውን ሲያስተዳድሩ የነበሩ ሲሆኑ አራተኛዎቹ ደግሞ ውጪ ሀገር ሄደው ሳይሳካላቸው የተመለሱ ናቸው:: ከአስራ አምስት እስከ አርባ ባለው እድሜ መካከል ያሉ ሴቶች ናቸው ወደ ማዕከሉ የሚቀላቀሉት:: ከሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር አንስቶ እስከታችኛው ድረስ ባለው የወረዳ መዋቅር መሠረት ሴቶቹ ተመርጠው ይመጣሉ::

ሴቶች ወደ ማዕከሉ ሲገቡ በቅድሚያ በማዕከሉ ለመቆየት ፍቃደኝነታቸው ይጠየቃል:: ፍቃደኝነታቸው ከተረጋገጠ በኋላ የጤና ምርመራ ይደረግላቸዋል:: ለዚህም በማዕከሉ ደረጃውን የጠበቀ ክሊኒክ ተዘጋጅቷል:: ምርመራው አንድም ቀደም ብለው ሕክምና ሲከታተሉ የነበሩ ሴቶች ወደ ማዕከሉ ከገቡ በኋላ ሕክምናቸው እንዳይቋረጥ ያደርጋል:: በሌላ በኩል ደግሞ ቀደም ሲል ያልተመረመሩና ራሳቸውን ያላወቁ ከሆነ በምርመራ ያለባቸውን የጤና ችግር ለመለየትና ሕክምና ለማግኘት ያስችላቸዋል::



**ማዕከሉ አቅሙን ማሳደግ ከቻለ በአንድ ግዜ 2 ሺ ሴቶችን ተቀብሎ የማስተናገድ አቅም አለው፤**

ፍቃደኝነታቸው ተረጋግጦ የሕክምና ምርመራ ካገኙ በኋላ ሴቶቹ በርካታ አገልግሎቶችን በማዕከሉ ያገኛሉ:: ከነዚህ አገልግሎቶች ውስጥ አንደኛው የሕክምና አገልግሎት ሲሆን ከማዕከሉ አቅም በላይ የሆኑ የጤና ችግሮች ሲያጋጥሙ ከጥሩነሽ ቤጂንግ ሆስፒታል ጋር በመሆን ተጨማሪ ሕክምና እንዲያገኙ ይደረጋል:: በሁለተኛ ደረጃ ሴቶቹ በማዕከሉ የምግብ አገልግሎት ያገኛሉ:: ሦስተኛ ደግሞ የተሟላ የማደሪያ አገልግሎት ያገኛሉ:: ሴቶቹ ከዚህ ቀደም የነበሩበት ሕይወት ጥሩ ስላልነበር መሠረታዊ ፍላጎቶቻቸው በማዕከሉ በበቂ ሁኔታ እንዲሟሉ ይደረጋል::

እነዚህ መሠረታዊ ፍላጎቶች ከተሟሉላቸው በኋላ ወደ ሥልጠና ከመሄዳቸው በፊት ለሥልጠናው ራሳቸውን እንዲያዘጋጁና በፊት ከነበሩበት ሕይወት ወጥተው ወደራሳቸው ቀልብ እንዲመለሱ ተከታታይነት ያላቸው የሥነ ልቦና፣ ማይንድ ሴት፣ የሕይወት ክህሎት ሥልጠኖች ይሰጣቸዋል:: እነዚህን የተሐድሶ ሥልጠናዎች ካጠናቀቁ በኋላ ወደ ክህሎት ሥልጠና እንዲገቡ ይደረጋል:: በማዕከሉ በርካታ የክህሎት ሥልጠናዎች አሉ:: ሴቶቹ ወደነዚህ የክህሎት ሥልጠናዎች የሚገቡትም የሚፈልጉትን ሙያ መርጠው ነው::

ለምሳሌ የጨርቃ ጨርቅ፣ ልብስ ስፌት፣ ጥልፍና የሹራብ ሥራ ሥልጠናዎች አሉ:: እነዚህን ሥልጠናዎች በሚገባ ይሠለጥናሉ፤ ይሠራሉ:: በተመሳሳይ በሥነ ውበትና የፀጉር ሥራም ሥልጠናዎችን ይወስዳሉ:: የቧንቧ፣ ኤሌክትሪክና የከተማ ግብርና ማለትም በከብት ማደለብ፣ በወተት ላሞች፣ ዶሮ ሥጋና የእንቁላል ተዋፅዖ ሥራዎችም ሴቶቹ በተጨማሪነት የሚያገኟቸው ሥልጠናዎች ናቸው:: የሕፃናት እንክብካቤ፣ የምግብ ዝግጅት፣ በቤት አያያዝ፣ ልብስ ንፅሕና አጠባበቅ ዙሪያም ሥልጠና ያገኛሉ:: ሴቶቹ ወደማዕከሉ ከገቡ አራት ወር የሞላቸው ሲሆን ሥልጠናውን ከሦስት እስከ ስድስት ወር ባለው ግዜ ውስጥ አጠናቀው ይወጣሉ ተብሎ ይጠበቃል::

ዋና ዳይሬክተሩ እንደሚሉት፣ ቀደም ብለው ወደ ማዕከሉ የገቡት 500 ሴቶች ናቸው:: ከነዚህ ውስጥ የተወሰኑት ወደተለያዩ እርዳታ ድርጅቶች ተወስደዋል:: አሁን ሥልጠና ላይ ያሉት በቂ ሥልጠና እንዲያገኙ እየተደረገ ነው:: እነዚህ ሴቶች ትናንትና ሕይወታቸው ጥሩ እንዳልሆነ ይታወቃል:: ከዚህ አንፃር ሴቶቹ ሥልጠናውን ከተከታተሉ በኋላ ዝምብለው እንዲበተኑና ወደነበረው ሕይወታቸው እንደሚመለሱ አይደረግም:: በዚህ ላይም የከተማ አስተዳደሩ በሁለት መልኩ ትልቅ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ ይገኛል::

አንደኛው የሥራ ዕድል ፈጠራ ማመቻቸት ሲሆን ከተለያዩ ሴክተር መሥሪያ ቤቶች ጋር ንግግር እየተካሄደ ነው:: ሁለተኛው ከተለያዩ ባለሃብቶችና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር ማስተሳሰር ሥራ እየተሠራ ነው:: ስለዚህ ሴቶቹ ከማዕከሉ ከወጡ በኋላ ሥራ ሠርተው ገቢ የሚያገኙበት መንገድ ይመቻቻል:: በአሁኑ ዙርም ሴቶቹ ሥልጠናውን አጠናቀው በሙያቸው ሥራ እንዲያገኙ እየተሠራ ነው::

እንዲህ አይነት ማዕከል ገንብቶ ሴቶችን በተሐድሶና ክህሎት ማሠልጠንና ወደ ሥራ ማሰማራት በሀገር አቀፍ ደረጃ የመጀመሪያ ልምድ ነው:: ክልሎችም መጥተው ልምድ እየወሰዱበት ይገኛሉ:: ምክንያቱም ክልሎች እዛው ዜጎችን በእንዲህ አይነቱ ማዕከል መያዝ ከቻሉ ለችግር ተጋላጭ የሆኑ ሴቶችን ሕይወት መታደግ ይቻላል:: ስለዚህ በቀጣይ ማዕከሉ አቅሙን በደምብ ማሳደግ ከቻለ አንድ ግዜ 2 ሺ ሴቶችን ተቀብሎ ማስተናገድ ይችላል:: ለዚህ ግን በሂደት ማዕከሉ ልምድ እየወሰደና ራሱን እያጠነከረ መሄድ ይኖርበታል::

ሴቶቹ ወደ ማዕከሉ ከገቡ በኋላ ከዚህ በፊት የነበራቸው የሰውነት ሁኔታ በእጅጉ ተቀይሯል:: ከአመለካከት፣ ከአስተሳሰብ፣ ከጤናና ከብዙ ማኅበራዊ አቅጣጫ የጎደላቸው ነበሩ:: ወደ ማዕከሉ ከመጡ ወዲህ ግን ይህ ሁሉ ተቀይሯል:: ሴቶች መሠረታዊ ነገሮች ከተሟሉላቸው፣ ማግኘት የሚገባቸውን ትምህርት ካገኙ የትኛውንም አይነት ሥራ የመሥራት አቅምና ብቃት እንዳላቸው ወደ ማዕከሉ ከገቡት ሴቶች ማረጋገጥ ተችሏል::

# ዓለም አቀፍ



## ለዶናልድ ትራምፕ ጤንነት የሚጸልዩት የሂንዱ አማኞች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

በሕንድ ዋና ከተማ የሚገኙ የሂንዱ እምነት ተከታዮች ለቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ዶናልድ ትራምፕ ለ7 ቀናት የሚቆይ የጸሎት ሥነሥርዓት ጀምረዋል።

“ሂንዱ ሲና” በመባል የሚታወቁት እነዚህ ቡድኖች ትራምፕ ፖለቲካውን ከተቀላቀሉበት 2016 ጀምሮ በየዓመቱ የልደት ቀኑን አስታውሰው ያከብራሉ።

ከሰሞኑ በቀድሞው ፕሬዚዳንት ላይ የተቃጣውን የግድያ ሙከራ የሰሙት አማኞቹ “የኃይል እና ጥበቃ ጌታ” በሚል በሚጠሩት “ባግላሙኪ” ከተሰኘው የሂንዱ አምላክ ምስል ከፍ ብሎ ረጂም ዕድሜ ለትራምፕ የሚል ጽሑፍ ያረፈባቸውን የዶናልድ ትራምፕ ፎቶዎችን በመስቀል ሃይማኖታዊ ሥርዓትን አከናውነዋል።

የጸሎቱ መሪው የአምልኮ ሥርዓቱን ባከናወኑበት ወቅት አምላካቸው ለትራምፕ ጥበቃ እና ደኅንነትን እንዲያወርድለት ጠይቀዋል ሲል ሮይተርስ ነው ያስነበበው።

ዛሬ እንደተጀመረ የተሰማው የአምልኮ እና ጸሎት ሥነሥርዓቱ የትራምፕ ደኅንነት እና ጤንነት ላይ በማተኮር ለቀጣዮቹ ስድስት ቀናት ይዘልቃል ተብሏል።

የቀድሞው ፕሬዚዳንት ወደ አሜሪካ ፖለቲካ ብቅ ካሉበት ወቅት ጀምሮ በአንድ ላይ በመሰባሰብ ልደታቸውን የሚያከብሩት አማኞች ኬክ፣ ፊኛዎችን እና የድግስ ኮፍያዎችን በመጠቀም አሜሪካውያን ልደቶችን በሚያከብሩበት መንገድ የትራምፕን ልደት ሲያከብሩ ቆይተዋል፡፡

ከየትኛውም የፖለቲካ አመለካከት ጋር ግንኙነት እንደሌላቸው የሚናገሩት አማኞቹ ለሂንዱ ማኅበረሰብ ደኅንነት እና እድገት ብቻ ነው የምንሠራው ይላሉ።

200 ሚሊዮን የሚጠጉ የእስልምና እምነት ተከታዮች በሚኖሩባት ሕንድ የሂንዱ እምነት ተከታዮች በሙስሊሞች እና በመስጂዶች ላይ ተደጋጋሚ ጥቃቶችን በመፈጸም ይታወቃሉ።

የሂንዱ ብሔርተኛ እንደሆነ የሚነገርለት የናሪንድራ ሞዲ ባሃራቲያ ጃንታ ፓርቲ ሥልጣን ከያዘ ጀምሮ በሙስሊሞች ላይ የሚደርስ ጥቃት እና ወንጀሎች መጨመራቸው ይነገራል።

## የሃውቲ ታጣቂዎች የደቀኑት ስጋት

የሃውቲ ታጣቂዎች በቀይ ባሕር አካባቢ የደቀኑት ስጋት በአጠቃላይ የዓለም ንግድ ሥርዓት ላይ እክል ፈጥሯል፡

ግዙፉ የባሕር ሎጂስቲክ አገልግሎት ማርስክ አፍሪካ፣ እስያ እና አውሮፓ በዚህ ችግር ምክንያት እየተፈተኑ እንደሚገኙ ድርጅቱ ተናግሯል፡፡



በእስራኤልና ሐማስ መካከል ጦርነት መቀስቀሱን ተከትሎ ከአሜሪካና እስራኤል ጋር ግንኙነት ባላቸው የንግድ መርከቦች ላይ ተደጋጋሚ ጥቃቶችን የፈጸሙት ሀውቲዎች፤ እስራኤል ከጋዛ እስከምትወጣ ድረስ ጥቃት ማድረሳቸውን እንደሚቀጥሉ መዛታቸውን ተከትሎ በአካባቢው የሚንቀሳቀሱ የንግድ መርቦች የደኅንነት ስጋት አጥልቶባቸዋል፡፡

በቀጣናው ለደኅንነት አስተማማኝ ሁኔታ ባለመኖሩ አማራጭ መተላለፊያዎችን ለመጠቀም ተገደናል ያለው ማርስክ ይህም ውጭዎችን እንዲጨምር በማድረጉ በሸቀጦች ዋጋ ላይ ንረት እንዲፈጠር ምክንያት መሆኑን ነው ያነሳው፡፡

ቀደም ባለው ጊዜ ወደ አውሮፓ በሚያሻግረው ስዊዝ ቦይ እና ወደ ባብ ኤል መንደብ መተላለፊያ ለመድረስ በሚደረገው ጉዞ ላይ ስጋቶች የነበሩ ሲሆን አሁን ላይ ወደ ሩቅ ምሥራቅ እና እስያ መተላለፊያዎች ላይ ተመሳሳይ እክሎች እንደሚያጋጥሙት ነው የመርከብ ድርጅቱ ያስታወቀው፡፡

በዚህ የተነሳም የመርከቦቹን የመጫን አቅም ከ15 እስከ 20 በመቶ እንዲቀንስ በማድረግ የሀውቲዎችን ጥቃት ሽሽት ተጨማሪ ጊዜ እና ወጪ በሚጠይቀው አፍሪካን ኬፕ በተባለ መተላለፊያ በመጠቀም ላይ እንደሚገኝ ተናግሯል፡፡

ወደ መካከለኛው ምሥራቅ እና አፍሪካ ዋነኛ የምርት ምንጭ እንደሆነ በሚነገርለት እስያ እየተስፋፋ የመጣው የደኅንነት ስጋት በቀጣይ በንግድ ሥርዓቱ ላይ ከፍተኛ ችግር ከማስከተሉ በፊት መፍትሔ እንዲበጅለት መጠየቁን ሮይተርስ አስነብቧል፡፡

የዓለም 30 በመቶ የንግድ ኮንቴነሮች በሚተላለፉበት ቀይ ባሕር ካሳለፍነው መጋቢት ወር ጀምሮ በባብ ኤል መንደብ እና በስዊዝ ካናል የሚተላለፉ መርከቦች በግማሽ ቀንሰዋል፡፡

በነዚህ ሁለት መተላለፊያዎች በዓመት ከ30ሺ - 50 ሺ መርከቦች ይተላለፋሉ፤ 12 በመቶ የዓለም ንግድ ፣ 15 በመቶ የዓለም ነዳጅ ምርት ፣ የእስያ እና አውሮፓ 40 በመቶ ንግድ በነዚህ መስመሮች የሚተላለፍ ነው፡፡

በአጠቃላይ ሁለቱ አሕጉሮች ብቻ እስከ 700 ቢሊዮን ዶላር ድረስ የሚወጣ የንግድ ሸቀጦቻቸውን ስጋት ላይ በወደቀው መስመር ያሳልፋሉ፡፡

# ወቅታዊ

# “ለውጡ ለሲዳማ ሕዝብ ከፍተኛ ትሩፋት ...

ከገጽ 8 የዞረ

**አዲስ ዘመን፡- በክልሉ የመስኖ ልማት ሥራ ምን ያህል ትኩረት ተሰጥቶት እየተሠራ ነው? በተሠራው ሥራስ ምን ያህል ተጨባጭ ውጤት መጥቷል?**

**አቶ ደስታ፡-** በአረንጓዴ ኢኮኖሚ ማዕቀፍ ውስጥ በዝናብ እጥረትና በድርቅ የማይበገር ኢኮኖሚ ተግባራዊ በማድረግ ቀጣይነት ያለውና አስተማማኝ እድገት ለማስመዝገብ ታስቦ እየተሠራ ነው። ከዚህ አንጻር ግብርናውን በማዘመንና ትራንስፎርም በማድረግ ክረምት፣ ከበጋ በዓመት ሶስትና ሁለት ጊዜ ማምረት የሚቻልበትን እድል ለመፍጠር ሰፋፊ ዘመናዊ የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ተሠርተው ወደ ሥራ ገብተዋል። እንዲሁም በመሠራት ላይ ያሉ አሉ። በተሠራው ሥራም ተጨባጭ ለውጥ መጥቷል።

ይህ ሲባል ሲዳማ እንደክልል ከመቋቋሙ በፊት በዘመናዊ መስኖ ይለማ የነበረው ከ500 ሄክታር መሬት የማይበልጥ ነበር። ክልል ከተሆነ በኋላ በክልሉ መንግሥት ብቻ ወንዝ በመጥለፍና በከርሰ ምድር ውሃ 4,500 ሄክታር መሬት በዘመናዊ መስኖ ለምቷል። ከዚህ በተጨማሪ የፌዴራል መንግሥት የግዳቦ ግድብ የመስኖ ልማት ፕሮጀክትን ገንብቶ ወደ ሥራ አስገብቷል። በዚህ ፕሮጀክት ብቻ 3,000 ሄክታር መሬት በዘመናዊ መስኖ ለምቷል።

በጥቅሉ ክልል ከመሆኑ በፊት በዘመናዊ መስኖ ይለማ ከነበረው 500 ሄክታር መሬት፤ አሁን ላይ ወደ 7,500 ሄክታር መሬት ማሳደግ ተችሏል። በዚህም በክልሉ በድምሩ 67 ሺህ ሄክታር መሬት በዘመናዊና ባሕላዊ መስኖ ለምቷል። በዚህ መልኩ የተገኘውን ውጤት አጠናክረን ከቀጠልን በአንድ አምስት ዓመት ውስጥ ሰፋፊ የመስኖ ልማት መሠረተ ልማቶችን በመዘርጋት አብዛኛውን የማህበረሰብ ክፍል ተጠቃሚ ማድረግ እንችላለን። ይህም ከዝናብ ጥገኝነት የተላቀቀ ግብርናን እውን በማድረግ ክረምት ከበጋ አምርቶ በምግብ እራስን ለመቻል፣ ገበያን ለማረጋጋት፣ ተጨማሪ ሀብት ለመፍጠርና ከድህነት ለመውጣት ያስችላል።

**አዲስ ዘመን፡- ሲዳማ በአንጻራዊነት ጥሩ ሠላምና መረጋጋት የሰፈነበት ነው። ይህ እንዴት ሊመጣ ቻለ? ሠላምና መረጋጋቱ ለክልሉ ኢንቨስትመንትና ቱሪስት ፍሰት እድገት እየተጫወተ ያለው ሚና ምን ይመስላል?**

**አቶ ደስታ፡-** “ትንፋሽና ሠላም ጣዕሙ በሰላም ጊዜ አይታወቅም” ይባላል። የሠላም ጣዕሙ የሚታወቀው ሠላም ሲጠፋ ነው። ስለዚህ የሠላም ትርጉሙ ገብቶን ሠላም ለማረጋገጥ በትኩረት እየሠራን ነው። የሕዝቡ የቆየ ባህልና እሴት የራሱ የሆነ አስተዋጽኦ አበርክቷል። በዚህም ክልል ከተሆነ በኋላ በሲዳማ ውስጥ እስካሁን የሰላም ጥያቄ ተነስቶ አያውቅም። ምክንያቱም የወጣቱ ጥያቄ የሥራ ዕድል ነው። ህብረተሰቡ የሚፈልገው ልማት ነው። ከዚህ አኳያ ወጣቱ ተደራጅቶ የሚሠራበትን ምቹ ሁኔታ በመፍጠርና ግብዓት በማሟላት ዛሬ ላይ ወጣቱ በሥራ ተጠምዷል። የህብረተሰቡን የዘመናት የልማት ጥያቄ በአጭር ዓመታት ውስጥ በአጥጋቢ ሁኔታ መመለስ ተችሏል። ስለዚህ ድንጋይ የሚወረውር፣ መንገድ የሚዘጋ የለም። ሕዝቡ ለዚህ ፊትና እድል አይሰጥም።

እንዲሁም ህብረተሰቡ ከፀጥታ ኃይሉ ጋር ተቀናጅቶ ለሠላሙ ዘብ ቁሞ እየሠራ ይገኛል። ህብረተሰቡ የራሱን ሠላም እራሱ በመጠበቅ በሠላም ወጥቶ እየገባ ነው። በዚህ ሁኔታ ሕዝቡ ተጠቃሚ ሆኗል። ሲዳማ ውስጥ ከሰላም አንፃር ሁሉም በአንድ ልብ መካሪና ተናጋሪ ነው። ሠላምን በማስፈን እረገድ ወጣቶች፣ ሴቶቹ፣ ሽማግሌዎች፣ የኃይማኖት ተቋማት፣... ድርሻ ድርሻ አላቸው። በዚህ አጋጣሚ ሕዝቡን፣ በዘርፉ ትኩረት ሰጥተው እየሠሩ ያሉ የፀጥታ አመራሮችና አባላቶችን እጅግ በጣም ላመሰግናቸው እፈልጋለሁ።

እንደሚታወቀው ቱሪስት ኮሽታ አይወድም። ሠላም ባልተጠበቀበት ቦታ ቱሪስት ዝር አይልም። ሠላም በመጠበቁ በክልሉ የቱሪስት ፍሰቱ እየጨመረ ነው። በተለይ የሀገር ውስጥ ቱሪስት ፍሰት እጅግ ጨምሯል። ለኮንፈረንስ ቱሪዝምና ለጉባኤዎች፣ ... የክልሉ ዋና ከተማ ሀዋሳ ተመራጭ ናት። ቅዳሜና እሁድ ከየትኛውም አቅጣጫ ወደ ከተማዋ ለመዝናናት ብዛት ያላቸው እንግዶች ይመጣሉ። በዚህም ከቱሪዝሙ የከተማው ማኅበረሰብ በከፍተኛ ደረጃ እየተጠቀመ ነው። በተመሳሳይ በዘርፉ የገጠሩ ማኅበረሰብ ተጠቃሚ እንዲሆን የቱሪስት መዳረሻ ቦታዎችን የማልማትና የማስዋብ፣ መሠረተ ልማት የማሟላት፣ አገልግሎት አሰጣጡን የማዘመን እንዲሁም ክልሉ ያለውን የቱሪዝም ሀብት በስፋት የማስተዋወቅ ሥራ እየተከናወነ ነው።

ሌላው አንድ አልሚ ኢንቨስት ከማድረጉ በፊት የራሱ መስፈርቶች አሉት። የመጀመሪያው ሠላም ነው። ቀጥሎ ኢንቨስት የሚያደርግበት ማኅበረሰብ ባሕል “ተባብሮ የሚሠራ ነው ወይስ ቆሞ የሚያይ ነው፤ ኢንቨስትመንቱን እንደራሱ ንብረት የሚንከባከብ ነው ወይስ ዘራፊ፣ አውዳሚ ነው” የሚለውን ያጠናል። ስለዚህ በቢሊዮንና ሚሊዮን ሀብት ይዞ የሚመጣው አልሚ እምነት ሊያድርበት ይገባል። በመሆኑም አልሚዎች እምነት ጥለው ወደ ክልሉ መጥተው መዋለነዋያቸውን እንዲያፈሱ የሚያስችል ሥራ ከፀጥታና ሠላም አንጻር ተሠርቷል።

በዚህም በየዓመቱ በርካታ የኢንቨስትመንት ፍላጎቶችን እያስተናገድን ነው። ቀደም ብለው የገቡትንም የማበረታታት ሥራ በትኩረት ይከናወናል። ከዚህ ባሻገር በርካታ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ሼልፋችን ላይ ይገኛሉ። ሆኖም በዝግጅት ጉድለት ባለው ልክ የኢንቨስትመንት ፍላጎቱን አላስተናገድንም። በቀጣይ ያለውን ፍላጎት ለማስተናገድ የኢንዱስትሪ ኮሪደር እያዘጋጀን ነው።

የኢንዱስትሪ ኮሪደር ልማቱን በስፋት ለማከናወን፤ ቀደም ብሎ ለአልሚዎች የተሰጡ ቦታዎች “ምን ያህል እየለሙ ነው?” የሚለውን ኦዲት አድርገናል። በኦዲቱም ሳይለሙ ታጥረው የተቀመጡ በርካታ መሬቶች መኖራቸው ተረጋግጧል። ከዚህ አንጻር በማስጠንቀቂያ እንዲያለሙ የማበረታታት ሥራ ተሠርቷል። ነገር ግን በተሰጣቸው ማስጠንቀቂያና ማበረታቻ መሠረት ወደ ልማት ባለመግባታቸው የሚነጠቁ በሃዋሳ ከተማ ብቻ ሰባት የኢንቨስትመንት ቦታዎች ተለይተዋል። በዚህ መልኩ ካስተካከልን በኋላ አዳዲስ ለኢንዱስትሪ አመቺ አካባቢዎችን የበለጠ ለማደራጀት እየሠራን እንገኛለን።

**አዲስ ዘመን፡- የቀድሞው የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል አሁን ላይ ወደ አራት ክልል ተከፋፍሏል። ይህንን ተከትሎ ፍትሃዊ የሀብት ክፍል ለማድረግ የሽግግር ማዕቀፍ ተዘጋጅቶ ትግበራ ላይ ነው። የሀብት ክፍፍል ሂደቱ በሰላም እንዲጠናቀቅና በክልሉ የሚገኙ ሁሉም የማህበረሰብ ክፍሎች በሠላም እንዲኖሩ ከማድረግ አኳያ ምን ተሠርቷል?**

**አቶ ደስታ፡-** ቀድሞ ክልል ሆኖ የወጣው ሲዳማ ነው። ያኔ ሲዳማ ክልል ሆኖ ሲወጣ የደቡብ ክልል እጣፈንታ አልተወሰነም ነበር። በዚህም ደቡብ ክልልና ሲዳማ ክልል በአንድ ከተማ የታጠቀ ሠራዊት ይዘው ለሶስት ዓመት በሠላም ተቀምጠዋል። ይህ በብዙ አካባቢ የሚቻል አይመስለኝም። ብዙ ግጭት ይፈጠር ነበር። ብዙ የሚያጋጩ ጉዳዮችም ነበሩ። ለአብነት ሲዳማ ቀድሞ ክልል ሆኖ ሲወጣ፤ የክልሉ ርዕሰ መስተዳድርና የፓርቲ ጽህፈት ቤት ኃላፊ መቀመጫ ተብሎ የተሰጠው፤ አነስተኛ ህንፃ ነው።

ነገር ግን ቀድሞ የደቡብ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ቢሮ የነበረበት ህንፃ እያለ፤ “አነስተኛ ህንፃ ተሰጥቶን ስንወጣ፤ ድርሻችን ይሄ ብቻ አይደለም፤ ድርሻችን ስጡን” ብለን አስወጥተን መግባት እንችል ነበር። ያላፈናቀልነው ለማስከን፣ ለማረጋጋት ነው። ምክንያቱም ያኔ ቢያንስ ሲዳማ ጥያቄው ተመልሶለታል። የደቡብ ግን እጣፋንታው አለየለትም ነበር። በዚህ ላይ ግፊት ሲታከልበት ምን ሊፈጠር እንደሚችል መገመት ቀላል ነው። ያ ሕዝብ የኛ ሕዝብ ነው። አብሮ የመኖር፣ የመብላት፣ የመጠጣት... ወዘተ የሕዝቦች የቆየ ትሥሥር አለ። ስለዚህ የዛ ሕዝብ አለመረጋጋት ጣሱ ለሀገር ነው። ሀገር ደግሞ በጋራ የምንገነባው ነው። የነበረው ጤናማ ግንኙነት እንዳይሻከር ከፍተኛ መስዋትነት ተከፍሏል። ብዙ ነገሮችን ግምት ውስጥ በማስገባት ሲዳማ ለሦስት ዓመት፤ ዝቅ ብሎ አገልግሏል ብዬነው የማስበው።

በኋላ ላይ ደቡብ ክልልም የራሳቸውን ምርጫ ወስነው ወደ ሦስት ክልል ተከፋፍለዋል። ይህንን ተከትሎ ሃዋሳ የነበረው የጋራ ቤት ሲፈርስ፤ የሀብት ክፍፍሉን በሠላማዊ መንገድ ለመቋጨት መረጃ ላይ የተመሠረተ ድርድርና ውይይት ሲደረግ ቆይቷል። በመጨረሻም “አንተ ትብስ አንቺ” በሚል መርህ የሀብት ክፍፍሉ በስምምነት ወደ መቋጨት ተደርሷል።

በአሁኑ ጊዜ ተንቀሳቃሽ ንብረቶችን በሚመለከት ኮሚቴ ተቋቁሞ በተደረገ ክፍፍል፤ ተሽከርካሪዎችን ጨምሮ ሌሎች ተንቀሳቃሽ ንብረቶችን ሁሉም የየድርሻውን ይዞ ሂዷል። ጥቂት ቀሪ የተንጠባጠቡ ጉዳዮች ካሉ እየታየ በጋራ ውይይትና ውሳኔ፤ እልባት ያገኛል።

ሌላው ህንፃን በሚመለከት ደግሞ፤ ደቡብ ክልል፣ ክልል ከሆነ እና መቀመጫውን ሃዋሳ ከተማ ካደረገ በኋላ በሀዋሳ ከተማ በጋራ የተገነቡ ንብረቶች ማዕቀፍ ውስጥ ያሉ አሉ። እነዚህ ህንፃዎች ተቆጥረው ተይዘው፤ “የቱ ወዴት ይሂድ?” የሚል ምክክር ተደርጓል። በዚህም በተመሳሳይ “አንተ ትብስ አንቺ” በሚል በሰጥቶ መቀበል መርህና መቻቻል ህንፃዎቹ ምን መሆን እንዳለባቸው እጣ ፋንታቸው ተወስኗል። የሲዳማ ድርሻውን ተለይቶ ተሰጥቶታል። ነገር ግን ሲዳማ “ይገባኛል” የማይላቸው፤ ለተቀሩ ለሦስቱ ክልሎች የደረሷቸው ህንፃዎች ሀዋሳ ከተማ ውስጥ አሉ። እነዚህን ህንፃዎች እንደራሳችን ንብረት እየጠበቅንና እየተንከባከብን ለባለቤቶቹ ማስረከብ ነው። ስናስረክብም ከሙሉ ሰነዱ፣ መብቱ፣ ... ወዘተ ጋር ነው የሚሆነው።

ህንፃዎቹ ግምት ዋጋ ስለወጣላቸው፤ “ያስፈልገናል” ብለን የምናስበው ህንፃ ካለ፤ የሚያጨቃጭቅ ምንም ነገር የለውም የወጣላትን ዋጋ ግምት ከፍለን ህንፃውን ገዝቶ የሲዳማ ማድረግ ነው። የተከፋፈሉ ክልሎች ህንፃውን ሸጠው ገንዘብ ይዘው መሄድ ስለሚፈልጉ፤ አቅሙ ካለን ገዝተን የራሳችን ስለምናደርግበት አግባብ ተነጋግረን ተስማምተናል። ምክንያቱም በየክልል ርዕሰ መዲናቸው ግንባታ ለማከናወን ገንዘብ ያስፈልጋቸዋል። ከዛ ውጭ የንብረታቸው ደህንነትና መብት ተጠብቆ ሁሉም ባለቤት ንብረቱን ለኛ ጥሎ በሠላም ይገለገልበታል።

በጥቅሉ የሽግግራችንና የንብረት ክፍፍላችን ሂደት፤ መሰል ሂደት ለሚገጥማቸው ተምሳሌት በሚሆን መልኩ፤ ፍጹም ኮሽታ በሌለበት በሠላማዊ መንገድ ተጠናቋል። ሁሉም ወደየመረጠበት ማዕከሉ ንብረቱን ይዞ ሂዷል። እያንዳንዱ ክልል ንብረቱ ተለይቶ ተሰጥቶት እያስተዳደረ ነው። ሲዳማ ክልልም የራሱን ንብረት በፈለገው መንገድ የሚያስተዳድርበት ደረጃ ላይ ይገኛል። ሌላው ከክልሎቹ ሕዝቦች ጋር ጤናማ ግንኙነት አለን። ይህ መልካም ወንድማማችነት ተጠናክሮ ይቀጥላል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የሲዳማ ሕዝብ እንደ “አፊኒ” ያሉ ግጭትን በሠላማዊ መንገድ ለመፍታት የሚያስችሉ የበለፀገ ባሕልና እሴቶች ባለቤት ነው። እንደ “አፊኒ” ያሉ ባሕላዊ እሴቶች ለሀገራዊ ምክክር ሂደቱ ስኬት የድርሻቸውን እንዲወጡ እንደክልል ምን እየተሠራ ነው?**

**አቶ ደስታ፡-** አጠቃላይ ሀገራችን ከጊዜ ወደ ጊዜ ከችግር እየወጣች ነው የሚል እምነት አለኝ። ነገር ግን አሁንም ተግባቦት ያልፈጠርንባቸው በርካታ ጉዳዮች አሉ። ከትናንት የወረስናቸው፤ በኛ ጊዜም የተፈጠሩ ውስብስብ ችግሮች አሉ። ይህንን ውስብስብ ችግር ልንፈታው የምንችለው ቁጭ ብለን በተረጋጋ ሁኔታ በመመካከር ነው። መንግሥት ይህንን ከግምት ውስጥ በማስገባት ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን አቋቁሞ፤ የምክክር ዕድል አመቻችቷል። ኮሚሽኑም የአጀንዳ፣ የተሳታፊ ልየታ ... ወዘተ ሥራዎችን እያገባደደ ይገኛል። በጥቂት ጊዜ ውስጥ ለአለመግባባት መነሻ የሆኑ አጀንዳዎች ለውይይት በጠረጴዛ ዙሪያ ይቀርባሉ ብዬ አስባለሁ። በዚህ የምክክር ሂደትም የተለያዩ ርዕዮት ዓለምና አመለካከት ያላቸው የፖለቲካ ፓርቲዎችም ይሳተፋሉ። እንዲሁም የሃይማኖት ተቋማት፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ ምሑራን፣ ... ወዘተ ተሳታፊ ናቸው።

እንደሀገር አላግባቡ ያሉ አጀንዳዎችን በብቃት ሊያቀርቡ የሚችሉ አካላት ሁሉ የሚሳተፉበት ነው። ስለዚህ ሀገራዊ ምክክር መድረኩን በሰከነ ሁኔታ ከተጠቀምንበት ለችግሮቻችን መነሻ የሆኑ ጉዳዮችን አንዴ ፋይላቸውን ዘግተን የምናልፍበት ነው። ይህም ኢትዮጵያ የሁላችን ሆና፤ ሁላችነም በጋራ አልምተን ለሁላችነም የተመቸች ሀገር ለመፍጠር ያስችለናል። ሀገራችንን በጋራ የምናበለፅግበት ዕድል ይፈጠራል።

ከዚህ አኳያ ለምክክር ሂደቱ ስኬታማነት ደግሞ እንደ “አፊኒ” ያሉ ግጭትና አለመግባባትን በሠላማዊና በሰከነ መንገድ ለመፍታት የሚያስችሉ ባሕልና እሴቶች ሚናቸው ከፍተኛ ነው። የሲዳማ ሕዝብ እስካሁን ተረጋግቶ፣ አንድነቱን ጠብቆ እንደ ማኅበረሰብ ተጠናክሮ ዛሬ ላይ የደረሰው “በአፊኒ” ባሕላዊ እሴቱ ነው። ለአብነት ምድር ላይ ከባዱ የሰው ሞት ወይም ደም መፋሰስ ነው። በሲዳማ ባሕል አንድ ሰው ተገድሎ ቢገኝ የሟች ቤተሰብ አስከሬኑን ጨርቅ እንኳን ቢጠፋ ቅጠል አልብሶ “አፊኒ” ይላል። “አፊኒ” ማለት ምን እንደሆነ፤ ምን እንደተከሰተ፤ አያችሁ፣ ሰማችሁ ወይ እንደማለት ነው። ከችግሮች በላይ ሆኖ መሻገርን የሚያመላክት ነው። “አፊኒ” ከተባለ በኋላ የሟችና የገዳይ ቤተሰብ ቢገናኙ እንኳን መረጋጋት ነው እንጂ አካኪ ዘራፍ አይባልም። በተለይ ሽማግሌ የሟች ቤተሰቦች፤ የገዳይ ቤተሰብ እንዳይጎዳ ይከላከላሉ።


በሌላ በኩል ደግሞ “አፊኒ” ከተባለ በኋላ ሁሉም ለችግሩ የመፍትሔ ሀሳብ ለማፍለቅ እንዲሳተፍ ዓውድ ይፈጥራል። በዚህ ማዕቀፍ ሁሉም ተረጋግቶ ከእርምጃ ይልቅ በሰከነ መንገድ ስለሆነው ነገር ወደ ማስረዳትና ወደ መመርመር ይገባል። ወደ ንግግር ወይም ማስረዳት ከተገባ በኋላ መግባባት፣ መተማመን... ይመጣል። በዛ ደረጃ ቢቻል ወዲያውኑ ካልሆነ በይደር፣ በቀጠሮ እየተወያዩ ከባድ የሆነ ችግርን ይፈታሉ። ስለዚህ “አፊኒ” በሲዳማ ሕዝብ ውስጥ ለሚፈጠሩ አለመግባባቶች የመፍትሔ ቁልፍ የሆነ ሥርዓት ነው። ይህን ሥርዓት እንደ ክልል በሚደረገው ሀገራዊ ምክክር ሂደት በስፋት እንደግብዓት እንጠቀምበታለን።

አሁን ላይ እንደሀገር የመጣው ዕድል ተመሳሳይ ነው። ብንነጋገር ብዙ መፍትሔ አለ። ነገር ግን አንዳንድ የኢትዮጵያ ችግርና መከራ እንዳያልቅ የሚፈልጉ አካላት፤ “እንመካከር” መባሉን የሚያብጠለጥሉ አሉ። እንነጋገር መጥፎ አይደለም። በቁርሾ፣ በቂም፣ በትርክት ... ወዘተ ተነሳስቶ መገዳደሉ ነው መጥፎው። በመሆኑም በኃይለኝነትና በእልህ የፈለግነውን እናሳካለን የሚለው አያዋጣም። በዚህ መንገድ ስንት ሺ ዓመታትን በጋራ መጥተናል። እየተጨራረስን ነው የመጣነው። ውጤቱም ቢሆን በድህነት ውስጥ ነው ያቆየን። ከዚህ በኋላ ይብቃን ልንል ይገባል። ለችግሮቻችን መነሻ የሆኑ ጉዳዮችን በመነጋገር መፍትሔ እንፈልግላቸው። ለመጪው ትውልድ የተሻለ ሕይወት የምናስብ ከሆነ፤ “በዳይ፣ ተበዳይ” ብለን በየጊዜው የምንጨቃጨቅበትን ያለፈውን ፋይል በእርቅና በይቅርታ ልንዘጋው ይገባል። ለአብነት ከኛ ሀገር በላይ በሕንድ ሀገር ብዙ ብሔር ብሔረሰቦች በአንድ ሀገር ተዋቅረው በፍቅር ይኖራሉ። ሀገራቸውንም ይጠብቃሉ። ብልፅግናንም አረጋግጠዋል። እኛም ያለችን ሀገር አንድ ናት። በፍቅር ልንኖርባት ይገባል። ከድህነት አዙሪት ወጥተን የበለጸገች ኢትዮጵያ ለመጪው ትውልድ ልናስረክብ ይገባል።

**አዲስ ዘመን:- ውድ ጊዜዎን ሰውተው ይህን ሰፋ ያለ ቃለምልልስ ስለሰጡን እናመሰግናለን።**

**አቶ ደስታ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

# ስፖርት



## ሩጫና ቱሪዝም በአርባ ምንጭ

ብርሃን ፈይሳ



ፎቶ- ሃዱሽ አብርሃ

በአርባምንጭ የመጀመሪያ በሆነው ታላቁ ሩጫ ላይ 2 ሺ700 የሚሆኑ ሰዎች ተሳትፈዋል፣

ስፖርትና ተፈጥሮ ከፍተኛ ቁርኝት ያላቸው እንደመሆኑ ለጤናማ ስፖርታዊ እንቅስቃሴ የአካባቢ ጥበቃ ሥራ በእጅጉ አስፈላጊ መሆኑ አያጠያይቅም:: በዚህም ምክንያት ዘመናዊነትና ሰው ሰራሽ ችግር ተፈጥሮ ፈቷን ያዞረባቸው ሀገራት አትሌቶች እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ሀገራትን ለልምምድ ይመርጣሉ:: ዓለም አቀፍ ውድድሮችን ሲያዘጋጁም የተበከለ አየርን በቴክኖሎጂ በመታገዝ ከተፈጥሯዊው ሁኔታ ጋር በማላመድ ሥራ ይጠመዳሉ::

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በኢትዮጵያ ተፈጥሮንና ስፖርትን ለማስተሳሰር ጥረት እየተደረገ ይገኛል:: በተፈጥሮ ከታደሉ አካባቢዎች አንዱ በሆነው አርባምንጭ ስፖርትና ቱሪዝምን ያዋሃደ የጎዳና ላይ የሩጫ ውድድር ከቀናት በፊት ተካሂዷል::

ስፖርት ቱሪዝም ላይ ከፍተኛ አትኩሮት ሰጥቶ በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኘው የኢፌዴሪ ቱሪዝም ሚኒስቴር ዓላማውን የአካባቢ ጥበቃ ላይ ያደረገ የሩጫ ውድድር ከታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ እና ሳፋሪኮም ጋር በመሆን አካሂዷል:: ከዚህ ቀደም በሃዋሳ ሃይቅ ዳርቻ እንዲሁም የአትሌቶች መፍለቂያ በሆነችው በቆጂ የአካባቢውን ነዋሪ ያሳተፈና ዓላማውንም ስፖርት ቱሪዝምን ማጠናከር እንዲሁም የሀገር ውስጥ ቱሪዝምን ማጎልበት የሆነ መሰል የሩጫ ውድድር መከናወኑ የሚታወስ ነው:: አሁን ደግሞ መዳረሻውን በተፈጥሮ ሀብት የታደለችውን አርባ ምንጭ ከተማን በማድረግ ነዋሪውን ያሳተፈ የጎዳና ላይ ሩጫ ተከናውኗል::

‹‹አርባምንጭን አረንጓዴ አድርጎ ማስቀጠል›› የሚል መሪ ሃሳብን ያነገበው ሩጫ፤ የአካባቢ ጥበቃ ላይ ያተኮረ መርሃግብር የፕላስቲክ ምርት በመቀነስ፣ እጽዋትን በመትከል እና አየርን ሊበክል የሚችል ነገርን በማስወገድ ነፋሻማ ሩጫን ለማካሄድ በሚል በተሳታፊው ከተማዋን በማጽዳት በተራቆተ አካባቢ ችግኝ ተተክሏል:: ከዚህ ባለፈ ከአዲስ አበባ የተጓዙ 60 የሚሆኑ የሩጫ ተሳታፊዎች የዶርዜ አካባቢ ጉብኝት እንዲሁም የእግር ጉዞን አካሂደዋል:: በርካታ የከተማዋ ነዋሪዎች የተሳተፉበት የ 7 ኪሎ ሜትር የሩጫ ውድድርም የህጻናት ሩጫን ተከትሎ ተከናውኗል:: በአርባምንጭ የመጀመሪያ በሆነው ታላቁ ሩጫ ላይ 2 ሺ700 የሚሆኑ ሰዎች የተካፈሉ ሲሆን፤ ከደቡብ ክልል የተውጣጡ አትሌቶችም የሩጫው አካል ነበሩ::

በዚህም መሠረት መክሊት መኮንን፣ እስራኤል አባተ እና ፋሲካ አየለ በወንዶች እንዲሁም መልካም አጓጉ፣ ታዘበች ተዘራ እና ድንቅነሽ ኦርሳንጎ በሴቶች የሩጫው አሸናፊዎች በመሆን የሜዳሊያ እንዲሁም የማበረታቻ ገንዘብ ሽልማት ተበርክቶላቸዋል:: የሩጫው ተሳታፊዎች ደግሞ ሻለቃ ኃይሌ ገብረስላሴ የፈረመበት የምስክር ወረቀት ተሰጥቷቸዋል::

የሩጫ ውድድሩን በሚመለከትም የኢፌዴሪ ቱሪዝም ሚኒስትር ዴኤታ አቶ አክሊሉ ታደሰ፤ ሚኒስቴሩ ስፖርት ቱሪዝም ላይ በትኩረት እየሠራ መሆኑን ጠቅሰዋል:: የአርባ ምንጭ ከተማና አካባቢዋም የቱሪዝም መስህብ በሆኑ ተፈጥሯዊና ባህላዊ እሴት ባለቤት እንደመሆኑ፤ በስፖርቱ ዘንድ ትልቅ አውድን ከፈጠረው ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ በመሆን የተዘጋጀ ሩጫ ነው:: ከአዲስ አበባ ባለፈ የሩጫ መርሃ ግብሮችን በክልሎችም በማስፋፋት እየሮጡ ሀገር መጎብኘት የሚቻልበትን ሁኔታ ያለመ ሲሆን፤ ጎን ለጎንም በአካባቢ ጥበቃ ዐሻራውንም አሳርፏል::

ኦሊምፒክን ጨምሮ የተለያዩ ስፖርታዊ ውድድሮችን ሀገራት ተፈጥሮና ታሪካቸውን በመሸጥ ተጠቃሚ ከሚሆኑባቸው በርካታ እድሎች መካከል አንዱ የስፖርት ቱሪዝም ነው:: በመሆኑም መንግሥት ለዚህ ዘርፍ፣ ለሀገር ውስጥ ቱሪዝም እንዲሁም ኮንፍረንስ ቱሪዝም ልዩ ትኩረት የሰጠ ሲሆን፤ በስፖርት ሀገርን ለማስተዋወቅም እየተሠራ ነው:: ታሪካዊ፣ ባህላዊና ተፈጥሯዊ ሀብት በታደለው አርባምንጭና አካባቢውም ‹‹እየጎበኘን፣ እየተዝናናን በሩጫ ጤናችንን እየጠበቅን የሀገራችንን ገጽታ እንሸጣለን›› በሚል ሩጫው እንደሚካሄድም ሚኒስትር ዴኤታው አብራርተዋል::

የአርባምንጭ ከተማ ከንቲባ አቶ ገዛኸኝ ጋሞ በበኩላቸው፤ የሩጫው መሪ ሃሳብ የሆነው ‹‹አርባምንጭን አረንጓዴ አድርጎ ማስቀጠል›› የከተማዋን የተፈጥሮ መስህብ በማጠናከር ረገድ ከፍተኛ ሚና ያለው መሆኑን ገልፀዋል:: የከተማዋ ውበት የሆነውና በአካባቢው የሚገኘው ጥብቅ ደን፣ የከተማዋ መጠሪያ ለመሆን የቻሉት ምንጮች፣ ሃይቆች እና አጠቃላይ ተፈጥሯዊ ሀብቷን በቱሪዝም መስህብነት ለማስቀጠል የአካባቢ ጥበቃ መሠረታዊ ነው:: ሩጫም ያልተበረዘውን የአካባቢውን ማህበራዊ አኗኗር እንዲሁም ሰላምም ይበልጥ አጉልቶ የሚያሳይ ነው:: ሩጫውን ተከትሎ ወደከተማዋ የሚጓዘውን ቱሪስት በመቀበል እንዲሁም በሩጫው መካሄድም የከተማዋ ነዋሪ እጅግ ደስተኛ እንደሆነም ገልጸዋል::

ከ10 ዓመታት በኋላ በድጋሚ ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ በከተማዋ ውድድር ያዘጋጀ ሲሆን፤ ይህንን ተከትሎም ድጋፍ ላደረጉ አካላት በታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ የኦፕሬሽን ዳይሬክተር ዳግም ተሾመ ምስጋናቸውን ገልጸዋል:: ውድድሩ ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ በየዓመቱ ከሚያካሂዳቸው ሩጫዎች መካከል አንዱ ሆኖ የሚቀጥልም ይሆናል:: ለዚህም በከተማዋ የሚገኙ ወጣቶችን አሠልጥኖ አዘጋጅቷል::


### ኦሮሚያ ክልል

በከሳሽ አቶ ድሪባ ንጉሱ እና ተከሳሽ ደሳለኝ ጋዲሳ መካከል ያለውን ክርክር አስመልክቶ ተከሳሽ መከሰሱን አውቆ በ15/11/2016 ዓ.ም በ3፡00 ላይ እንዲቀርቡ ካልቻሉ ክርክሩ በሌሉበት የሚቀጥል መሆኑን የለገጣፎ ለገዳዲ ክፍለ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት አዟል፡፡

**በሸገር ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት**

በከሳሽ አንበሳ ኢንሹራንስ ኩባንያ ቢሾፍቱ ቅርንጫፍ እና በተከሳሽ ATMG ኤሌክትሮ መካኒካል ኢንጂኔሪንግ መካከል ያለውን የውል ክርክር አስመልክቶ መከሰሳችሁን አውቃችሁ መልሳችሁን በጽሁፍ አዘጋጅታችሁ በቀጠሮ ቀን 15/11/2016 4፡00 ሰዓት ላይ 3ኛ ፍትሐብሔር ችሎት እንድትቀርቡ ሆኖ የጽሁፍ መልሳችሁን የማታቀርቡ ከሆነ በጽሁፍ መልስ የመስጠት መብታችሁ ታልፎ ክርክሩ ተካይዶ ውሳኔ የሚሰጥ መሆኑን የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አዟል፡፡

**የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት**

### አዲስ አበባ አስተዳደር

በከሳሽ/ሾች ፊጣ ገደፋ እና በተከሳሽ/ሾች እነ መኩሪያ ተክሉ መካከል ስላለው የፍ/ብሔር ክስ ጉዳይ ተከሳሽ/ሾች አቶ መኩሪያ ተክሉ በ19/11/2016 ዓ.ም ለሆነው ቀጠሮ ከጠዋቱ 3፡30 ሰዓት ፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ኮ/ቀ ምድብ 3ኛ ልዩ ልዩ ችሎት እንዲቀርቡ እንገልፃለን፡፡

**የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**

### ማስታወቂያ

አመልካች አይኒ አጢቅ አህመድ በቀበሌ 07 ክልል ውስጥ የሚገኘው የመኖሪያ ቤት ካርታ ቁጥር 162 የሆነ ይዞታ ማረጋገጫ /ቀሪ ካርታ/ የጠፋ ስለሆነ በምትኩ ለመስጠት ይህንኑ ካርታ በእዳ ይገኛዋለሁ የሚል ካለ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ በወጣ በ30 ቀናት ውስጥ ይቅረብ፡፡

**የድሬዳዋ አስተዳደር የይዞታ ማህደራት አስ/ር መረጃና ዲጂታላይዜሽን ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር**

### የሐራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ

በፍ/ባለመብት ወ/ሮ ሰዓድ ዩሱፍ እና በፍ/ባለዕዳ አቶ መኮንን ይመር መካከል ስላለው የፍርድ አፈጻጸም ጉዳይ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 105950 በ5/2/2016 ዓ.ም እና በመ/ቁ 108281 በ9/4/2016 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት በቀድሞ ኮ/ቀ/ክ/ከተማ በአሁኑ አዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 13 ውስጥ የሚገኝ የቤ.ቁ MKB46-04/1843 ሳይት ህንፃ ቁጥር 846 በካርታ ቁጥር 631/06212/00 ባለ ሶስት መኝታ የሆነው ኮንዶሚኒየም ቤት ፍ/ድ ያረፈበት ይዞታ መለያ ቁጥር AA000091300009460411843 በመኮንን ይመር አየለ ስም የተመዘገበ ካርታ ያለው የቤቱ ስፋት 64.04 ካ/ሜ ቤት የሐራጅ ሽያጭ መነሻ ዋጋ ብር 2,050,368.68(ሁለት ሚሊዮን ሃምሳ ሺ ሶስት መቶ ስልሳ ስምንት ብር ከስልሳ ስምንት ሳንቲም) ሆኖ የትራንዛክሽን ታክስ ገዥ የሚከፍል መሆኑ ታውቆ ነሀሴ 15 ቀን 2016 ዓ/ም በሐራጅ ይሸጣል፡፡ የተጫራቾች ምዝገባ በ4፡30 ሰዓት ተጀምሮ የቀረቡ ተጫራቾች ተመዝግበው እንደተጠናቀቀ ወዲያዉኑ ጨረታው የሚካሄድ ይሆናል፡፡

የሐራጁ ሽያጭ የሚካሄደው በፌደራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት የጨረታ አዳራሽ ውስጥ ሲሆን፣ ንብረቱን ተጫርተው ለመግዛት የሚፈልጉ ተጫራቾች ከጨረታው ቀደም ብሎ ባሉት አራት የሥራ ቀናት ውስጥ ባለመብቱ ለማስጎብኘት በሚመርጧቸው ሶስት የስራ ቀናት በፌ/ፍ/ቤቶች ፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት ሐራጅ ክፍል ድረስ ከጠዋቱ በ3፡30 ጀምሮ በመገኘትና ባለመብቱ በሚያቀርበው ትራንስፖርት ንብረቱን ባለበት ቦታ ድረስ በመውሰድ መጎብኘት የሚችሉ ሲሆን፤እያንዳንዱ ተጫራች በሚጫረትበት ወቅት የንብረቱን ግምት 1/4 ኛውን በንግድ ባንክ በተረጋገጠ c.P.O ማስያዝ ይኖርበታል፡፡ ከ1/4ኛ አስበልጦም ሆነ አሳንሶ C.P.O የሚያመጣ ተጫራች በጨረታው አይካፈልም፡፡

በጨረታው አሸናፊ የሆነው ግለሰብ አሸናፊ የሆነበትን ገንዘብ በአጠቃላይ ጨረታውን ከአሸነፈበት ቀን ጀምሮ በፍ/አ/ዳ/ስም C.P.O አሰርተው በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በተከፈተ አሰርቶ ሙሉ ገንዘቡን በ15 ቀናት ውስጥ ገቢ ማድረግ አለበት የፍ/አ/ዳይሬክቶሬት ንብረቱን በህጋዊ መንገድ በሀራጅ ስለመሸጡ ለሚመለከተው አካል ማስረጃ ከመፃፍ ባለፈ ስም የማዛወር ግዴታ የሌለበት መሆኑን እንገልፃለን።

**በፌ/ፍ/ቤቶች ፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት**